# የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ

## (በአፋር ክልል በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች)


በ

አብርሃም ገ/ዮሐንስ



ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ

ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት



ጥር 2003

# የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ

(በአፋር ክልል በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች)

በ
አብርሃም ገ/ዮሐንስ

ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ
ድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

ለአማርኛ ማስተማር (TeAm) ኤም.ኤ ዲግሪ
በከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ጥር 2003 ዓ.ም.

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

## የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ (በአፋር ክልል በተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች)

በ


አብርሃም ገ/ዮሐንስ

ቋንቋዎች ጥናት ተቋም


የፈታኝ ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |
| ፈታኝ | ፊርማ |

# ምስጋና

ጥናቱ ተጀምሮ ለፍጻሜ እስኪበቃ ድረስ የጥናቱን ረቂቅ በማንበብና ቅርጽ በማስያዝ ሙያዊ ድጋፋቸው ሳልተለየኝ አማካሪዬና መምህሬ ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል ያለኝ አክብሮትና ልባዊ ምስጋና ወደር የለውም።

ለጥናቴ ግማሽ ኃይል የሆነኝን የሞራል ማበረታቻ በመስጠት፣ አስፈላጊ የተባለውን የሐሳብና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ከጎኔ ያልተለዩኝ ጓደኞቼን፣ ካህሳይ ሃይሉ፣ ተስፋዬ ሞላ፣ በላይነህ ኃይሌ፣ አማረ ቶሸመ፣ ጥላሁን ከበደ እና በጎሰው የሽዋስ ከልብ አመሰግናለሁ።

አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ የአፋር ክልል ትምህርት ቢሮ ኃላፊ፣ የተጠኚ ትምህርት ቤቶች መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም በሠመራ ዩኒቨርሲቲ መምህር ለሆነው ለአቶ ቶማስ ዳኛቸው ልባዊ ምስጋና ይገባቸዋል።

ከልጅነት እስከ ዕውቀት ቤተሰባዊ ፍቅራቸው ለማሳየት ድጋፋቸው ለዚህ ያበቃኝ ለአባቴ ለአቶ ገ/ዮሐንስ ብርሃን፣ ለእናቴ ወ/ሮ አኸዛ ሽፋረ ውለታቸው ታላቅ ነው። እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ቆይታዬ እናታዊ እንክብካቤያቸውን ሳልተለየኝ ለወ/ሮ ኤልሳቤጥ ከበደ እና ለቤተሰባቸው ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

የቦታ ርቀት ሳይገድባቸው ወንድማዊ ፍቅራቸውን ብቻ ሳይሆን ምክራቸውንና ድጋፋቸውን በመለገስ በየጊዜው ከባሕር ማዶ ስልክ በመደወል የሚያበረታቱኝ ወንድሞቼ መሐሪ ገ/ዮሐንስ፣ ገብረእግዚአብሄር ገ/ዮሐንስና ተክለ ደስታ ታላቅ ባለውለታዬ ናቸውና ባሉበት ልባዊ ምስጋናዬ ይድረሳቸው።

ይህ ጥናት በዚህ መልኩ ተጽፎ እንዲቀርብ በጥንቃቄ በመተየብ ለተባበረችኝ አርማዬን አደራ ምስጋና ላቅ ያለ ነው።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ....................................................................................................... I

አጠቃሎ ....................................................................................................... II

ማውጫ ....................................................................................................... III

የሠንጠረዦች ዝርዝር ....................................................................................... IV

ምዕራፍ አንድ - መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................................... 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ......................................................................................... 3

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ ...................................................................................... 4

1.4 የጥናቱ ገደብ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

ምዕራፍ ሁለት - የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

2.1 የንግግር ክሂል ምንነትና ባሕርያት ................................................................ 6

2.2 ንግግር ክሂል የማስተማር ዓላማ ................................................................... 8

2.3 የንግግር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 9

2.4 ተግባቦታዊ አቀራረብ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ያለው ድርሻ . . . . 10

2.5 የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሥነ-ጽሑፍ ሚና . . . . . . . . . . . . . . . 11

2.6 የንግግር ክሂልን መማሪያ ተግባራት ...................................................... 12

2.7 የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች . . . . . . . 17

2.8 የንግግር ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 18

2.9 ንግግርን የመማር/ማስተማር መርሖች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 19

2.10 ንግግርን የመማር ችግሮች እና መፍትሔው .......................................... 20

2.11 በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና . . . . . . . . . . . . 22

ምዕራፍ ሦስት - የአጠናን ዘዴ

3.1. የጥናቱ ክንውን ........................... 23

3.2. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ ........................... 23

3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ........................... 23

3.2.2. የተጠኚ የክፍል ደረጃና የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ ....... 24

3.2.2.1. የተጠኚ የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ........................... 24

3.2.2.2. የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ ........................... 24

3.2.3. የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................... 25

3.2.3.1. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ........................... 25

3.2.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........................... 25

3.3. መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ........................... 27

3.3.1. የማስተማሪያ መረጃ መሣሪያዎች ........................... 27

3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ ........................... 27

3.3.3. የጽሑፍ መጠይቆች ........................... 28

3.4. የመረጃ አተናተን ........................... 29

ምዕራፍ አራት- የመረጃና የጥናቱ ውጤት ትንተና

4.1. የመረጃ አተናተን ........................... 30

4.1.1. ከማስተማሪያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................... 30

4.1.2. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................... 33

4.1.3. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................... 48

4.1.3.1. ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................... 48

4.1.3.2. ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ........................... 62

4.2. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........................... 73

4.2.1. ንግግርን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች ........................... 73

4.2.2. ንግግርን የማስተማር ሥነ-ዘዴ ትግበራ ........................... 74

ምዕራፍ አምስት - ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

5.1. ማጠቃለያ ........................... 77
5.2. የመፍትሔ ሐሳብ ........................... 79
ሙዳዩ ቃላት
ዋቢ ጽሑፎች
የአባሪዎች ዝርዝር
አባሪ "አንድ" የንግግር ትምህርት ክንውን ምልከታ መከታተያሠንጠረዥ ........................... ሀ
አባሪ "ሁለት" ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ........................... መ
አባሪ "ሦስት"ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ........................... በ

# የሠንጠረዦች ማውጫ


ሠንጠረዥ ገጽ

1 በጥናቱ የተካተቱ ትምህርት ቤቶች ስም፣ የሚገኙበት ወረዳና ከተማ ሠንጠረዥ ..... 25

2 የተማሪዎቹንም ሆነ የመምህራኑን ናሙና አመራረጥ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........... 27

3 በመማሪያ መጽሐፉ የቀረበው የንግግር ክሂል ይዘቶች የሚያሳይ ሠንጠረዥ .............. 31

4 በመርሐ-ትምህርቱ የቀረበው የንግግር ክሂል ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ይዘቶች፣ ክንውኖች፣ የግምገማ ነጥቦች ብዛት የሚያሳይሠንጠረዥ ........................................ 32

5 ከመምህሩ መምሪያ የተገኙ የንግግር ክሂል ትምህርትን አቀራረብ የሚያሳ ሠንጠረዥ33

6 በመርሀ-ትምህርትና በመማሪያ መጽሐፍ የቀረቡትን የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብዛትና ስርጭት የሚያሳይ ሠንጠረዥ .............................................. 33

7 የመምህሩ የንግግር ክሂል ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፤ ... 35

8 የመምህሩ የዕለቱ የንግግር ትምህርት ልምምድ አቀራረብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ....... 38

9 የንግግር ትምህርት በልምምድ ተግባር ወቅት የመምህሩ ሚና የሚያሳይ ሠንጠረዥ 41

10 ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ መምህሩ ያመቻቸበት ሁኔታ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........................................................................ 45

11 የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ተራክቦ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ............... 47

12 ለትግበራ የቀረቡ መልመጃዎችን ምንጭ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ ................................................................ 48

13 የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መረጃ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........................................ 50

14 ስለ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ በተመለከተ መምህራን ያላቸው ግንዛቤ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ................................................................ 52

15 የንግግር ክሂል ትምህርት እየተሰጠው ያለውን ትኩረት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ....... 53

16 የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን ትምህርት አቀራረብ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........... 55

17 ተማሪዎች የንግግር ተግባራትን እንዲለማመዱ የመምህሩን ሚና የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........................................................................ 58

18 ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ የመምህሩ ሚና የሚያሳይ ሠንጠረዥ ...... 61
19 የተማሪዎችን ናሙና አመራረጥ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........................................ 63
20 የተማሪዎችን የንግግር ክሂል የመማር ፍላጎት የሚያሳይ ሠንጠረዥ .................... 64
20.1 የተማሪዎችን የንግግር ክሂል የመማር ፍላጎት የሚያሳይ ሠንጠረዥ ................ 64
21 በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍል ሁኔታ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ............................ 65
22 የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት የመምህሩና
የተማሪዎች መስተጋብር (Interaction) የሚያሳይ ሠንጠረዥ ................................ 66
23 የንግግር ክሂል የመማር-ማስተማር ትግበራ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ......................... 68
24 መምህሩ የትምህርት መረጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚያሳይ ሠንጠረዥ ........... 71
25 በክፍል ውስጥ የመምህሩ ምጋቤ-ምላስ አሰጣጥ የሚያሳይ ሠንጠረዥ .................. 72
26 ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የመምህሩ
ድርሻ የሚያሳይሠንጠረዥ ................................................................................ 73

# አጠቃሎ

የቋንቋ ክሂሎች የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንውን በተገቢው መንገድ ከተከናወነ የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ለማሳካትና በተማሪዎች ላይ የተፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው።

የጥናቱ ዓላማም የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና ትግበራ ከዘመናዊው ጋር ተጣጥሞ በክፍል ውስጥ መቅረብ አለመቅረቡን መገምገም ነው። በዚህም መሠረት በዋናነት በመምህራን ላይ ትኩረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ምልከታ ተከናውነዋል። በደጋፊነትም መምህራንና ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ለኢ-አፈፊት ተማሪዎች አሉታዊ ተፅእኖ እንደሚያሳድር በማመን በማስተማሪያ መሣሪያዎች ላይም ምርመራ እና ትንተና ተካሂደዋል።

በአፋር ክልል ከሚገኙት 24 የመንግሥት ከአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ሦስት፣ ከሦስቱ ትምህርት ቤቶች ዘጠኝ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በኢላማዊ ናሙና አማካይነት ተመርጠዋል። የሦስቱ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራንና ከየትምህርት ቤቶቹ የተመረጡ 60 የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርገዋል።

ከምልከታ፣ ከጽሑፍ መጠይቆችና ከማስተማሪያ መሣሪያዎች ከተገኙት መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ አብዛኛዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማሩን ሂደት በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ እንዲታገዝ አለመሞከራቸውን፣ በቋንቋው ተጠቅመው በንግግር ሐሳባቸውን በነጻ የሚገልጹበትን ሁኔታ አለማመቻቸታቸውን፣ የንግግር ማስተማሪያ ደረጃዎችን በተገቢው መንገድ አለማከናወናቸውን፣ በተጨማሪም ከመማሪያ መጽሐፉ ጎን ለጎን የተማሪዎችን ፍላጎት ሊያነሳሳ የሚችል ተግባር በጥንቃቄ አለመመረጡ፣ የዕለቱን የንግግር ክሂል ትምህርት ርእስ ጉዳይ ግልጽ በሆነና በማይረሳ መልኩ አለመቅረቡ፣ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል ዕድል አለመስጠቱ እና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ለማበረታታት የተሻለ ሙከራ አለመደረጉ፣ በመጨረሻም የመማር-ማስተማሩን ሂደት ክሂሉን ለማዳበር ያሉበትን ችግሮች ለማቃለል የሚያስችሉ የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል።

# ምዕራፍ አንድ

## መግቢያ

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ መማር-ማስተማር እንቅስቃሴ ከተጀመረ አያሌ ዘመናት ያስቆጠረ ቢሆንም እስከ ዛሬ ድረስ በመስኩ ያሉ ምሁራን የማስተማሪያ ዘዴውን፣ የማስተማርያ መሣሪያውንና መርጃውን ከተለያዩ የቋንቋ ንድፈ ሐሳባዊ ትውረቶች ጋር በማጣመር የተሻለ የመማር- ማስተማር መስተጋብርን ለመፍጠር በመጣር ላይ ይገኛሉ፡፡ የዚህ የቋንቋ  ትምህርት አቀራረብም በሁለት ተከፍሎ ክሂሎችንና የዕውቀት ዘርፎችን በማዳበር ላይ አትኩሮ በሀገራችን በተቀረጸው የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ በመካተት እየተሠራበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡ እነዚህ አቀራረቦችም አንድን የቋንቋ ተማሪ ከቋንቋ ትምህርት አንፃር የተሟላ የአጠቃቀምና የቋንቋ ሥርዓት ዕውቀትን ያስጨብጡታል ተብለው የታሰቡ በመሆናቸው በቋንቋ መማር-ማስተማር እንቅስቃሴው ውስጥ ሰፊ ሽፋን ተሰጥቶዋቸው ይገኛሉ፡፡

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ ተማሪው ታላሚውን የቋንቋ ሥርዓትና አጠቃቀም ወይም ዕውቀትና ክህሎት ዐውቆ በቋንቋው መግባባት እንዲችል ማድረግ ነው፡፡ በመማር-ማስተማር ሂደት የሚጠበቀው ግብ በታላሚው ቋንቋ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማዳበር እንዲሁም የሥነ ልሳንና የሥነ ጽሑፍ መሠረታዊ ዕውቀትን ማስጨበጥ ነው፡፡

የአንድ የቋንቋ መምህር ዋናው ትኩረት ተማሪዎችን ስለቋንቋው መዋቅር ክፍሎች ማሳወቅ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው የተለያዩ ክሂሎችን በመገልገል ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ተገቢ የሆኑ ስልቶችን በመጠቀም ችሎታቸውን እንዲያሳድጉ መርዳት መሆን አለበት (Byrne 1976:1)፡፡ ስለሆነም የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ክንዋኔ ከፍተኛ ጥንቃቄ እና ዝግጅት ማድረግን፣ እንዲሁም በዘመናዊ ዘዴዎች መጠቀምን የሚጠይቅ በመሆኑ የቋንቋ ትምህርት ባለሙያዎች ከፍተኛ እገዛ ሊያደርጉበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ሆኖ እያለ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማሪያ መጻሕፍት ሆነ በመርሐ ትምህርት ውስጥ የክፍል ውስጥ የክሂሎች ማስተማር ሥነ ዘዴ ተግባር ትኩረት ሳይሰጠው ቆይተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች የማዳመጥና የማንበብ ልምዳቸውም፣ የመናገርና የመጻፍ ችሎታቸውም ደካማ የሆነ የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሁለተኛ ደረጃ፣ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች የሚገቡትም በትምህርታቸው ላይ ከፍተኛ ጫና እንደሚፈጥርባቸው ይገመታል፡፡

የንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ ትግበራ ብቻ ሳይሆን ንግግር በቋንቋው ክፍል ውስጥ በአብዛኛቸው ምሁራን ዘንድ ትኩረት የተነፈገው መሆኑን Mc Donough (1993:115) ይገልፃሉ፡፡ Brown and Yule (1983:1) ይህንን ሲያጠናክሩ፣ ቋንቋን ማስተማር የጽሑፍ ቋንቋን እንደማስተማር ተደርጎ ስለሚወሰድ የቋንቋ መምህሩም ለተማሪዎች በጣም ጠቃሚነት ያላቸውን የጽሕፈት ሞዴሎች በመምረጥና ወደ ክፍል በማምጣት ተማሪዎች እንዲሠሯቸው ያዝዝ እንደነበር በመግለጽ፣ በአንፃሩ ደግሞ ለንግግር ክሂል ዝቅተኛ ግምት ሲሰጠው እንደቆየ አስረድተዋል፡፡

እንደ Bygate (1987:Vii) አባባል፣ የንግግር ክሂል በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና፣ ተማሪዎችን በማንኛውም ተግባቦታዊ እንቅስቃሴያቸው በራሳቸው ተማምነው ጥሩ የሆነ ማሕበራዊ ግንኙነት የሚፈጥሩበት በመሆኑ በክፍል ውስጥ ዘመናዊ ስልቶችን ተጠቅሞ ማስተማሩ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው ይላሉ፡፡

Harmer (1991) በበኩላቸው የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት ተማሪዎች ራሳቸውን የመግለጽ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ስለሆነ የቋንቋውን ትምህርት ዋነኛ አካል በመሆን በተገቢው መንገድ ሊሰጥ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ስለዚህ የንግግር ክሂልን የማስተማር ሥነ ዘዴ በክፍል ውስጥ ያለው ሂደት በተለይ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ችሎታ የማዳበሩ ሁኔታ በጥናት ቢረጋገጥ ለወደፊቱ ለንግግርም ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ክሂሎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ስለንግግር ክሂል የክፍል ውስጥ አቀራረብ፣ መምህራን ያላቸውን አመለካከትና የማስተማሪ ዘዴ ምርጫቸው ምን እንደሚመስል የሚሉትን ነጥቦች ለማወቅ አጥኚው ጥናቱን ለማካሄድ ተነሳስቷል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ በአፋር ክልል የሚገኙ የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማርያ ሥነዘዴዎችውና አተገባበራቸው ምን እንደሚመስልና የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የተመረጡ ይዘቶችን የትምህርት ሂደቱን መከናወን አለመከናወናቸው፣ የመፍትሔ ሐሳብ ማግኘት እንዳለበት ለመጠቆም ነው። በመሆኑም ጥናቱ በሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች ዙሪያ እንዲያጠነጥን ሆኗል፤

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የሚያስተምሩበትን የትምህርቱ አቀራረብ መለየት፣
2. መምህራን እንደሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች ለንግግር ክሂል ትምህርት ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩ መሆኑን መለየት፣
3. ተማሪዎች የንግግር ክሂል ትምህርትን የሚማሩበት ሁኔታ ክሂሉን ሊያስጨብጣቸው የሚችል መሆኑን መገምገም፣
4. መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርትን ሲያቀርቡ አስፈላጊ የሆኑ ሂደቶችን ተከትለው በማስተማር በኩል ግንዛቤያቸው ምን እንደሚመስል መገምገም፣
5. በክሂል ትምህርት አቀራረብ ላይ አሉታዊ ተፅእና የሚያሳድሩና ሊታረሙ የሚገባቸውን ተላውጦዎች (Variables) ነቅሶ በማውጣት መፍትሔ መሻት ናቸው።

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ከቋንቋ ክሂሎች ውስጥ አንዱ የሆነውን የንግግር ክሂል በክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴውና አተገባበሩ በጥናት አስደግፎ ማቅረቡ ጠቃሚነቱ የጎላ ነው፡፡ በመሆኑም የንግግር ትምህርት አተገባበር ዘመናዊውን የመማር-ማስተማር አቀራረብ፣ ሥነዘዴ እና ስልት የተከተለ መሆኑን መፈተሽ አስፈላጊ ጉዳይ ነው፡፡ በተጨማሪም ጥሩ የንግግር የመማር-ማስተማር ሁኔታ በክፍል ውስጥ አለመኖሩ በተለይ ደግሞ በኢ-አፊ-ፊት ተናጋሪዎች ዘንድ አንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከማሳካት አንፃር የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅእኖ ቀላል አይደለም፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ተገቢውን ንግግር እያደረጉ እንቅፋት ይፈጥርባቸዋል፡፡ ስለዚህ መምህራን ከወቅቱ የክፍል ውስጥ የክሂሎች የማስተማር ዘዴ ትግበራ ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂላቸውን ለማዳበር የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የቋንቋ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ ምን ያህል ነው? የሚለውን ጥያቄ መፈተሽ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ጥቅሞች ይኖሩታል፤

- ንግግርንም ሆነ ሌሎች ክሂሎች በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ዘመናዊ የቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ አቀራረብ ደካማና ጠንካራ ጎን ተገምግሞ አስፈላጊው መፍትሔ እንዳለበት ለማመልከት፤
- ንግግርን ለማስተማር በመርሐ ትምህርቱም ሆነ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች ክሂሉን ለማዳበር ያላቸውን ጠቀሜታ ለማመልከት፣
- መርሐ ትምህርቱ፣ መማሪያ መጻሕፍቱ እና ሌሎች መረጃ መሣሪያዎች ንግግርን በክፍል ውስጥ ለማስተምር አመቺ በሆነ መንገድ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲዘጋጁ፤
- መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርትን ሲያቀርቡ አስፈላጊ የሆኑ ሂደቶችን ተከትለው በማስተማር በኩል ግንዛቤያቸው ምን እንደሚመስል ለመገንዘብ፤
- በመስኩ ለሚደረጉ ሌሎች ጥናቶች መነሻና አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ገደብ

የጥናቱዋና ዓላማ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውስጥ ያለውን የክፍል ውስት የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር መገምገም ሲሆን በተጨማሪም ተማሪዎች በንግግር ሀሳባቸውን የመግለጽ ችሎታ እንዲያዳብሩ ያበረከተውን አዎንታዊና አሉታዊ አስተዋጽኦዎች ይመለከታል። ስለዚህም ጥናቱ በንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማርያ ዘዴ ምርጫና ትግበራ እንጂ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል የመማር ስልት፣ የንበት ትምህርት፣ ወዘተ. ላይ ትኩረት አያደርግም።

በዚህ ጥናት ውስጥ ተተኳሪ የሚሆኑት በ2003 ዓ.ም. በአፋር ክልል ዞን አንድ ውስጥ የሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (5-8) ትምህርት ቤቶች ይሆናሉ። ተጠኚዎቹም በዞኑ ከሚገኙ ወረዳዎች በናሙናነት የሚመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ የ8ኛ ክፍል መምህራን ሲሆኑ፣ ከመምህራኑ መካከል የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ ባላቸውና የቅርብ ጊዜ የሥራ ልምድ ባላቸው መምህራን ይሆናል።

የጥናቱ ርእስም "የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና የትምህርቱ አቀራረብ" ነው። ጥናቱ በአፋር ክልል ካሉት ዞኖች መካከል በዞን አንድ ሲሆን፣ በዞኑ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች መካከልም በናሙና የሚመረጡ ሦስት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ይሆናሉ።

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

## 2.1. የንግግር ክሂል ምንነትና ባሕርያት

የንግግር ክሂል ለቃላዊ ተግባቦት ከሚያስፈልጉት የቋንቋ ችሎታዎች አንዱ ነው፡፡ በማዳመጥ ሐሳብን መቀበል እንደሚቻል ሁሉ ለተደመጠው ምላሽ ለመስጠትና መልእክት ለማስተላለፍ ደግሞ መናገር ያስፈልጋል፡፡ እንደ ሐሳብ መቀበያው ክሂል ሁሉ (ማዳመጥ) መልእክት ማፍለቂያና ማስተላለፊያውም (መናገር) በመማር ይዳብራል፡፡ የንግግር ምንነትን አስመልክተው ሰፋ (1995:15)፣ Harmer (1991)ን ጠቅሰው እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

> ንግግር በተፈጥራአዊ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ ከቤተሰብና ከአከባቢ የሚማሩት ክሂል ነው፡፡ ክሂሉ ለተግባራዊ አገልግሎት ሲውል የትክክለኛነትን የርቱዕነት ባህርያት ማሟላት አለበት፡፡ የትክክለኛነት ባህሪው ከድምጾች አጠራር፣ ከቃላት አመራረጥና አሰዳደር ጋር ሲያያዝ የርቱዕነት ባህሪው ደግሞ የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ መልእክትን ያለመሰናክል ከመግለፅ ጋር ይዛመዳል፡፡ ለዚህ ተግባቦታዊ ተግባር ሲያገለግልም ከተናጋሪው የተለያዩ ተግባሮችና ችሎታዎች ያስፈልጋል፡፡

እነዚህ ችሎታዎች የተላበሰ እንደበተ-ርቱእ ተናጋሪ ለመሆን ክሂሉን መማር የግድ ያስፈልጋል፡፡ የመማሩ አስፈላጊነት እንዴትነትና ክነውኑ በትኩረት እንድንመርጥ ያደርገናል፡፡ በንግግር የተሟላ መልእክት ለማስተላለፍ የሰዋስው ዕውቀት ብቻ ሳይሆን ማሕበራዊ ሕጎችን፣ የዲስኩር ደንቦችንና የብልሃት ዕውቀትን ይጠይቃል Celce-Murcia (1991፡125) ፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ማሪው (1998:139) ንግግር ክሂልን እንደሚከተለው ይገልጹታል፤

> ንግግር ክሂል የሁለት ችሎታዎች ጥምረት ውጤት እንደሆነም ይታመናል. የማህበራዊና ስነ-ልሳናዊ፡፡ ክሂሉን ለማዳበር የቋንቋውን መዋቅራዊ ክፍልና ማህበራዊ አጠቃቀም አጣምሮ መለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት እንዳለው ሁሉ ማህበራዊ (አጠቃቀም) ስርዓትም አለው፡፡ ማህበራዊ ስርዓቱ በመዋቅራዊ ስርዓቱ ላይ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል፡፡

የንግግር ክሂል የተለያዩ ቃላዊ ፍሰቶችን ልናፈልቅበት የምንችል ሲሆን፣ ሐሳባችንን፣ ስሜታችንን እና ምኞታችንን የምንገልጽበት እንዲሁም ከሰዎች ጋር ከስምምነት ላይ የምደርስበት፣ ችግሮችን የምንፈታበት፣ ማሕበራዊ ህይወት የምንመሠርትበትና ጓደኛ ልናፈልቅበት የምንችልበት፣ በአጠቃላይ ተግባቦታዊ ተግባራትን የምናከናውንበት ዓይነተኛ መሣሪያ ነው (Mc Donough and shaw 1993:153; Bygate 1987: Vll)፡፡ የቃል ተግባቦት የሚካሄደው በተናጋሪውና በአድማጩ መካከል ባለው መስተጋብር ሲሆን የአፍላቂና የተቀባይ ክሂልን ግንዛቤ በከፍተኛ ደረጃ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም ማዳመጥና መናገር ተደጋጋፊና በእጅጉ የተቆራኙ ክሂሎች መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የቃል ተግባቦት ባሕርይ መስተጋብራዊ ተግባርን (interactional function) ተጠቅመው ተማሪዎች የራሳቸውን ባህል፣ ልምድ እና ዕውቀት መሠረት በማድረግ የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲፈጥሩና ማሕበራዊ ግንኙነታቸውንም እንዲያጠናክሩ ማድረግ ነው፡፡ በሌላ በኩል በመረጃ ልውውጥ ተግባር (transactional function) አንድን መረጃ ወደ ተፈለገው አካል ለማስተላለፍ ያመቻቸው ዘንድ እንዲጠቀሙበት ያግዛቸዋል (Nunan 1989:27)፡፡

ንግግር የሰው ልጅ መግባቢያ በሆነው ቋንቋ ሐሳብን የመግለጽ፣ መልእክትን የማስተላለፍ ተግባር ነው፡፡ በተፈጥሯአዊ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመዳ ሂደትም ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ ከቤተሰብና ከአከባቢ የሚማሩት ክሂል ነው፡፡ ክሂሉ ለተግባቦታዊ አገልግሎት ሲውል የትክክለኛነትና የርቱዕነት ባሕርያትን ማሟላት አለበት፡፡ የትክክለኛነት ባህሪው ከድምጾች አጠራር፣ ከቃላት አመራረጥና አሰዳደር ጋር ሲያያዝ የርቱዕነት ባህሪው ደግሞ የሀሳብ ፍሰትን ጠብቆ መልእክትን በትክክል ከመግለጽ ጋር ይዛመዳል፡፡ ለዚህ ተግባቦታዊ ተግባር ሲያገለግልም ከተናጋሪው የተለያዩ ችሎታዎች ይጠይቃል፡፡ ከነዚህ ችሎታዎች ውስጥ ለተጋለጡበት ዐውድ ተገቢ የሆኑ አብርሂያጅ (ተጣማሪ) ቃላት መርጦ መጠቀም፣ ቃላቱ የተዋቀሩበትን ድምጾች በትክክል መጥራት፣ መልእክትን በትክክል ምልክቶች መወከል (encoding)፣ ሥርዓተ አጠራርንና የንግግር ሥርዓቶችን መጠበቅ፣ ወዘተ. የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህን ችሎታዎች የተላበሰ አንደበተ- ርቱዕ ተናጋሪ ለመሆን ክሂሉን መማር የግድ ይሆናል፡፡ የመማሩ አስፈላጊነት በበኩሉ የመማሩን እንደትንትና ክንውን በትኩረት እንድንመርጥ ያደርገናል፡፡

Celce- Murcia (1991:125) በበኩላቸው፣ በንግግር የተሞላ መልዕክት ለማስተላለፍ የሠዋስው ዕውቀት (Grammatical Competence) ብቻ ሳይሆን የማሕበራዊ ሕጐችን (Socio cultural competence)፣ የዲስኩር ደንቦችንና (Discourse Rules) የብልሃት ዕእውቀት (Strategic Competence) እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ።

ማረው (1998:139) እንደሚሉት፣ የመናገር ክሂል ሊዳብር የሚችለው ሕጎችን በማስተማር ወይም በመንገር ሳይሆን እንደማንኛውም ክሂል በተግባራዊ ተሳትፎ ብቻ ነው። ተማሪዎች እየጻፉ የመጻፍ ክሂላቸውን እንደሚያዳብሩ ሁሉ እየተናገሩም የመናገር ክሂላቸውን ማዳበር አለባቸው።

## 2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን የማስተማር ዓላማ

ከአፍላቂ ክሂሎች ውስጥ የሚመደበውን የንግግር ክሂል የማስተማር ዓላማ ተማሪዎችን ጥሩ ተናጋሪ ለማድረግ ነው። Byme (1987:8) እንደሚሉት፣ መምህሩ ውሱን ንግግርን፣ ልቅ ወይም ነፃ ንግግርን ጎን ለጎን በማካሄድ የተማሪዎችን ችሎታ ከፍ ማድረግ ይቻላል። በተጨማሪም የንግግር ክሂል የሚከተሉት የማስተማር ንዑስ ዓላማዎች አሉት፤

1. የቋንቋውን ድምፀልሳንዊ ባሕርያት አድማጭ ሊረዳ በሚችልበት መንገድ መጠቀም እዲችል፣
2. በንግግር ሂደት ሐሳብን በቅደም ተከተል አዋቅረው ማፍለቅ እንዲችሉ፣
3. መስተጋብራዊ በሆኑ የተግባቦት ሂደቶች መሳተፍ እንዲችሉ፣
4. በውይይት ሂደት የተደረሰባቸውን ስምምነቶችና መደምደሚያዎች በቃል መዝግበው ማቅረብ እንዲች፣ ወዘተ. የሚሉት ናቸው።

በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎች የሚሳተፉበት የንግግር ተግባራት በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እርስ በራሳቸው ሐሳብ ለሐሳብ እንዲለዋወጡና በሂደትም የቋንቋውን ሥርዓት ጠንቅቀው እንዲረዱ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ተግባቦታዊ ተግባራት በልምምድና በአፍልቆት ደረጃ የሚመጡ ሲሆን ተማሪዎች

ከልክነት (accuracy) ወደ አፈ-ተክነት (fluency) ቀስበቀስ እንዲሸጋገሩ የምናደርግበት መሆኑን Byrne (1987፡10) ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ንግግርን የማስተማር ዓላማን ለማሳከት በዕውቀትና በክሂል መከከል ያለውን ልዩነት ማወቅ ጠቃሚ ነው። እንደ Bayget (1987:3) አባባል፣ በታላሚው ቋንቋ ለመግባባት የቋንቋውን የቃላት አደረጃጀትና የሰዋስው መዋቅሩን በተወሰነ መልኩ ጠቃሚ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ደግሞ በቋንቋው ለመገልገል የሚያበቃ ክሂል ያስፈልጋል በማለት ገልጸዋል።

## 2.3. የንግግር ክሂልን የመማር አስፈላጊነት

እንደ Harmer (1991:15) አገላለጽ፣ ንግግር ክሂል ከጽሑፍ በበለጠ መልኩ ሐሳባችንን ለመግለጽ፣ ለማስተላለፍ፣ ለማብራራት፣ ወዘተ. የምንጠቀምበት ክሂል ሲሆን፣ ከማዳመጥ ክሂል ቀጥሎ አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናጠፋው በዚሁ ክሂል መሆኑን ይገልጻሉ። ሰዎች ሁለተኛ ቋንቋቸውን ሲማሩ ማወቅና ይበልጥ መገልገል የሚፈልጉት በንግግር ነው። በመሆኑም በማንኛውም እንቅስቃሴያችን ውስጥ ሰፊ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ በተገቢው መንገድና ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ማስተማር ተገቢ ነው።

ተማሪዎች በቋንቋ ተጠቅመው ሀሳባቸውን መግለፅ እንዲችሉ ዘመናዊ በሆነ የክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ዘዴ ትምህርት ሊሠጣቸው ይገባል። በዚህም በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ያዳብሩ ዘንድ አስፈላጊው ሁሉ ሊደረግ ይገባል (Harmer 1991፡15)። በተጨማሪም፡-

- ተገቢ ቃላትን በተገቢው ቦታ መጠቀም እንዲችሉ፣
- ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ፣
- ሐሳብን በተጠየቃዊ ቅደም ተከተል ማቅረብን እንዲለማመዱ፣
- የንግግራቸውን ፍሰት ፈር እስይዘው ሐሳባቸውን እንዲገልጹ፣
- አስተያየቶችን በማስረጃ አስደግፈው ማቅረብ እንዲችሉ፣
- ግላዊ አመለካከታቸውን በንግግር ነፃ ሆነው እንዲገልጹ፣
- ኢ-መደበኛ የአነጋገር ስልት አስወግደው መደበኛ የአነጋገር ስልት እንዲጠቀሙ፣ ወዘተ.።

እንዲሁም የንግግር ክሂል የማስተማር ዓላማ ተማሪዎቹ ንበቱ የተስተካከለ፣ ማሕበራዊ ተቀባይነት ያለው ቋንቋ እንዲፈልጉ ማስቻል ነው። የንግግር ክሂል የተለያዩ ማሕበራዊና ትምህርታዊ ፋይዳዎች እንዳሉት (Harmer 1991: 72) ይጠቅሳሉ። ከነዚህ ውስጥም፤

- በርካታ የቋንቋ ዕውቀት ለመቅሰም ያስችላል፣
- በንባብና ጽሕፈት ክሂሎች እድገት ላይ አዎንታዊ አስተዋጽኦ ያመጣል፣
- ተማሪው የሚማረውን ቋንቋ ንበት (pronunciation)፣ ጫና(stress)፣ የጽምጾችን አወጣጥ(intonation) ለማወቅና፣ እና
- ከተሻለ ማሕበራዊ ደረጃ ላይ ለመድረስ ፋይዳዎች አሉት።

## 2.4. ተግባቦታዊ አቀራረብ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ያለው ድርሻ

በተግባቦታዊ አቀራረብ የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ አብዛኛው ጊዜ አገልግሎታዊም ሆነ ሥነልቦናዊ ዓላማው ከተማሪው ፍላጎትና ችሎታ የተለያዩ ተግባራትን ይቀርባሉ። በቡድን ወይም ጥንድ በመሆን እርስ በራሳቸው ሐሳብ ለሐሳባ እንዲለዋወጡ፣ ሌሎች የሚያስተላልፉትን ሐሳብ መረዳት እንዲችሉ፣ እንዲከራከሩ፣ ወዘተ. የሚያግዝ ነው። በዚሁም በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የመረጃ ልውውጥ በተገቢው ሁኔታ መካሄዱን ነው። ይህም የንግግር ክሂል ለማስተማር በከፍተኛ ደረጃ ሁኔታዎችን ያመቻቻል (Richards and Rodgers1986:71)። በተጨማሪም ምሁሩተግባራዊ አቀራረብ ለመናገር ክሂልን ለማዳበር ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ሲያብራሩ፤

- ጥሩ አድማጭ በመሆን ጥሩ ተናጋሪ መሆንን፣
- ከሰዎች ጋር ሀሳብ ለሀሳብ መለዋወጥን፣
- ሰዎች ሲጠይቁ አገናዝቦ መመለስን፣
- ጭውውት ማራኪ በሆነ መንገድ ማቅረብን፣
- በክርክር፣ በውይይት ላይ ከሰዎች ጋር ሐሳብ ለሐሳብ የመለዋወጥ፣ ወዘተ. ያካትታል።

## 2.5. የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሥነ-ጽሑፍ ሚና

የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ደራሲው ከአእምሮው በመጭመቅ ኪናዊ በሆነ መንገድ እውነትንና ውበትን አቀናጅቶ የሚያቀርባቸው ሥራዎች በመሆናቸው ተማሪዎችን የመሳብ፣ የማንገትና ስሜት የመቀስቀስ ኃይላቸው ከፍተኛ ነው (Lazar 1993:15)።

እንደ ምሁሯ አባባል በተለያዩ ልቦወለዶች ያሉ ምልልሶች፣ ውይይቶች፣ ታሪኮች፣ የመሳሰሉትን የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች የተማሪዎችን ቀልብ የመግዛት ኃይላቸው ከፍተኛ በመሆኑ የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም በሰፊው ከማሳደጋቸውም በላይ ስሜታቸውን በከፍተኛ ሁኔታ በመቀስቀስ የአብዛኛውን ተማሪ ተሳትፎ እንዲጨምር ያደርጋሉ።

እንደ Berhanu(1994፡217) ገለጻ፣ የሥነ-ጽሑፍ ሥራ ሳቢነት ያለው በመሆኑየተማሪዎችን ትኩረት ለመሠብሰብና ሐሳባቸውንና አመለካከታቸውን በራሳቸው ቋንቋ እንዲገልጹ ከማስቻሉም ባሻገር የሰዋስዋዊ መዋቅሩም ሆነ የቃላት ችሎታቸው እንዲያድግ በተሳካ ሁኔታ እገዛ ያደርጋል።

በመማር-ማስተማር ሂደት መምህሩ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን መሠረት በማድረግ ተግባቦታዊ ተግባራትን በከፍተኛ ሁኔታ ሊያከናውንበት ይችላል። ተማሪዎች በሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ላይ ሐሳብ እንዲሰጡ፣ ታሪኩን አጠር ባለ መልኩ እንዲያቀርቡ፣ የገጸ ባሕርያቱን ደግነት፣ ጨካኝነት፣ ወዘተ. በተመለከተ ገለጻ እንዲያደርጉ፣ ከታሪኩ ተነስተው የተለያዩ ጭውውቶችን እንዲሰሩ፣ ወዘተ. የሚሉትን ዋናዋና ነጥቦች በማንሳት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ሰፋ ያለ ንግግር እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቻላል።

የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን ተጠቅመው የታያቸውን ወይም በአእምሮአቸው የቀረጹትን ነገር እንዲሁም የተሰማቸውን ስሜት የሚገልጹበትን ሁኔታ በተለያየ መንገድ ማመቻቸት ይቻላል። በሥነ-ጽሑፍ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ነገሮች (መላፊጠራ፣ ሚና ነጠቃ፣ ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ውይይቶች ድራማና ተውኔቶች) ተጠቅመው ተማሪዎች ተገቢ ወደ ሆነው ተግባቦታዊ ንግግር መግባት እንዲችሉና የቋንቋ

ዕውቀትና ማሕበራዊ ዐውድን የመገንዘብ ብቃት እንዲያገኙ መንገድ ማመቻቸት እንደሚቻል Celce-Murcia (1991:337-345) ይገልጻሉ።

## 2.6. የንግግር ክሂልን መማሪያ ተግባራት

ንግግር በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ዓላማ በታላሚው ቋንቋ ቃላዊ ተግባቦት (Oral Communication) የማካሄድ ችሎታን ማዳበር ነው። ማለትም በተጋለጡበት ዐውድ በቀረበው ርእስ ጉዳይ ላይ የቋንቋውን ተናጋሪዎች ልማድ፣ ባህልና የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት የተከተለ ንግግር ማድረግ ነው። ለዚህ ዓላማ መሳካትም የቋንቋውን የንግግር ሥርዓት የሃሳብ መግለጫ ቃላቱ ጋር በቅንጅት መለማመድ ያስፈልጋል። የመለማመጃ ክንዋኔዎቹም የተለያዩ የመማሪያ ቴክኒኮችን በመጠቀም የሚከናወኑ በርእስ ጉዳይ (ይዘት) እና በክንውን ላይ ያተኮሩ ውይይቶች፣ ተራክቧዊ ንግግሮች፣ ተግባራት፣ ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ።

በእነዚህ ስልቶች ንግግርን ለማስተማር በውይይት፣ በክርክር፣ በምልልስ ወዘተ ተማሪዎቹ ለሚገኙበት ደረጃ የሚመጥኑ የመለማመጃ ክንውኖች መመረጥ ይኖርባቸዋል። የንግግር ክሂልን በውይይት ለመማር ከሚከናወኑት ተግባራት የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት።

***ሀ. ሥዕሎችን በንግግር መግለጽ፡-*** የመናገር ክሂልን በውይይት ለማስተማር በተለይም ለጀማሪ ተማሪዎች ውጤታማ የሆነው ስእላዊ መግለጫ ነው። በዚህ ስልት ለማስተማር በቅድሚያ ተማሪዎችን በቡድን መከፋፈል ያስፈልጋል። በጥንድና በቡድን ተመድበው ለተቀመጡት ተማሪዎች የተለያዩ ሥዕሎችን በማደልና በተወሰኑ ደቂቃዎች የሥዕሎቹን ይዘት የሚገልጹ ቃሎችን ወይም አረፍተ ነገሮችን እንዲመዘግቡ፣ የተመደበው ጊዜም እንዳለቀ ለጠቅላላው ተማሪ እንዲያቀርቡ በማድረግ ይከናወናል።

***ለ. ልዩነትን በንግግር መግለፅ፡-*** ይህ የመማርያ ስልት ተማሪዎችን በብጤ (በጥንድ) በመመደብና የተለያዩ ነገሮችን (ሥዕሎችን) በመስጠት በየግላቸው ካጠኑ በኃላ የአንዱ ከሌላው የሚለይባቸውን ባህሪያት በመናገር የሚለማመዱበት ነው። በጋራ ሆነው በያዙዋቸው ነገሮች ልዩነት ላይ ሲወያዩ የሚያነሷቸው ጥያቄዎችና የሚሰጧቸው

መልሶች ሃሳባቸውን ነፃ ሆነው እንዲገልጹ ያደርጓቸዋል፤ የመናገር ክሂላቸውንም ያዳብሩላቸዋል።

**ሐ. ተመሳሳይነትን መናገር፦** ተማሪዎች በመማር-ማስተማር ሂደት በቡድንና በጥንድ ተመድበው በጋራ የያዙዋቸውን ነገሮች የጋራ የሆኑ ተፈጥሯዊ ባሕርያት በንግግር በመግለጽ ክሂሉን የሚለማመዱበት ስልት ነው። በሂደቱም በቅድሚያ በየቡድናቸው እንዲቀመጡና የሚጋሯቸውን ነገሮችና ባሕርያት እንዲዘረዝሩ ግልጽ መምሪያ መስጠት ያስፈልጋል። መምህሩ መመሪያ ከመስጠት ውጭ ምንም ነገር ሊያቀርብላቸው አይገባም።

**መ. የገበያ ልውውጥን ማካሄድ፦** ተማሪዎችን ሻጭና ሸማች (ገገር) በመሆን መናገርን የሚለማመዱበት የገሃዱን ዓለም ዕውነታ በማስመሰል በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚፈጠር ዐውድ ነው።በመማሩ ሂደት ተማሪዎቹ ከፊሎቹ ጥያቄያቸውን በማቅረብ፣ ሌሎቹ ደግሞ በአብዛኛው በአሃዝ የሚገለጹ መልሶችን በመስጠትና የመላሽና የጠያቂን ሚና በመለዋወጥ በታላሚውን ቋንቋ ይናገራሉ።

**ሠ. ችግርን የመፍታት ተግባራት** (problem_solving Taskes)፦ ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር ሂደት በኃላፊነት ላይ ያለውን ሰው በመወከል ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ የምክር አገልግሎትን ለመስጠት፣ ውሳኔ ለመስጠት፣ ወዘተ. በታላሚው ቋንቋ የሚጠቀሙበትንና ንግግርን የሚለማመዱበት ክንውን ነው። የዚህ ዓይነቱ የመለማመጃ ክንውን ከተማሪዎቹ ደረጃ ልምድ ጋር ተገናዝቦ የሚቀርብ ነው። ልምምዱ ከመናገር ክሂል በተጨማሪ ማህበራዊ ችግሮችን ከራሳቸው ጉዳይ ጋራ እያይዘው መፍትሔ የመሻት ልምድን ያዳብርላቸዋል።

በተጨማሪም የንግግር ተግባራት አይነቶችን Brown and Youle (1983: 109) እንደሚከተለው አጠቃለው ገልጸውታል፤

ሀ. ቋሚ ግንኙነት ያላቸው ነገሮች (Static relationships)

- አንድን ነገር ወይም ፎቶ ግራፍ መግለጽ፤
- የተለያዩ ነገሮችን እንዴት እንደሚቀናጁ መመሪያ መስጠት ወይም መግለጽ፣
- አንድ ሰው አንድን ነገር እንዴት እንደሚያከናውን መመሪያ መስጠት፤

ለ. ተለዋዋጭ ግንኙነት ያላቸው (Dynamic relationships)

- ታሪክ መናገር፣
- የዓይን እማኝ ወይም ምስክርነት መስጠት፣

ሐ. ረቂቅ ግንኙነት ያላቸው (Abstract relationships)

- በአንድ ነገር ላይ አመለካከትን ወይም ሀሳብን መግለጽ፣
- የአንድን ነገር ድርጊት ግልጽ ማድረግ፣

ከላይ በጠቀስናቸው የንግግር ዓይነቶች ተመርኩዘን የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር በክፍል ውስጥ በተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም ይቻላል። ዋና ዋናዎቹ የሆኑት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

1. ሐሳብ ማመንጨት (Brainstorming)

ተማሪዎች በተወሰነ ርዕስ ላይ ተመርኩዘው ነገሮችን ከተለያዩ አቅጣጫዎች በማመላከት ብዙ ሐሳቦችን እንዲያፈልቁ የሚረዳቸው በመሆኑ የንግግር ውስጥ ክንውን ወቅት ተማሪዎች በግላቸው፣ በጥንድ፣ እንዲሁም በቡድን በመሆን ሐሳብ እንዲያፈልቁ ማድረግ ይቻላል። ተማሪዎች የተለያዩ ክንውኖችን በሚተገብሩበት ጊዜ የሚከተሉትን ማጤን ይኖርባቸዋል፤

- ርዕሱን በወረቀት ጫፍ ላይ መጻፍ፣
- ስለርዕሰ ጉዳዩ በአእምሯቸው የመጣላቸውን ነገር ሁሉ መናገር፣
- በቀረበው ሐሳብ ላይ ውይይት ማስተማር፣
- ለሰዋሰው አወቃቀሩ ሳይጨነቁ የተባለውን ነገር በአጭር ቃል ወይም ሐረግ መጻፍ፣
- ሁሉም የቡድኑ አባላት አስተያየት በመስጠት እንዲሳተፉ ማድረግ፣ እና
- በተግባሩ እንቅስቃሴ ላይ ከጥራት ይልቅ ብዛት ተፈላጊ እንደሆነ ማወቅ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለባቸው (Berhanu 1994:16)፣

2. ድራማዊ ተግባራት

Malay and Daff (1978:6) እንደሚገልጹት፣ ድራማዊ ተግባራት ተማሪዎች በተለያዩ የፈጠራ ዐውዶችን ተጠቅመው ተፈጥሮአዊ ችሎታቸውን ለማሳየት ለመከረጅ፣ ራሳቸውን ለመግለጽ፣ በምልልስ ወይም በጭውውት መልክ ለማቅረብ፣ ወዘተ. እድል

የሚያገኙበት ነው ብለዋል። በመሆኑም ድራማዊ ተግባራት የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ከማሳደግ አኳያ ያላቸው ጠቀሜታ ታውቆ በክፍል ውስጥ ማለማመድና መተግበር ቃላዊ ተግባርን በብቃት ለማስተማር ጠቃሚ ነው።

Byrne (1987:115) ድራማ በውስጡ ሦስት ዐበይት ነገሮችን እንደሚይዝ ሲያስቀምጡ Celce-Murcia (1991:338-341) ደግሞ ከሳቸው ብዙም ባልተለየ መንገድ ድራማ (Dramatization)፣ መሳ ፈጠራ (Improvisation) እና ሚና ነጠቃ (Role Play) በማለት ያስፍራሉ።

1. ድርጊታዊ እንቅስቃሴ (Mime)፡- ይህ ሁኔታ ቃላዊ ንግግር በሌሌበት ሁኔታ በድርጊት የታጀበ በመሆን አንድ ተማሪ የድርጊት እንቅስቃሴ በሚያደርግበት ጊዜ ሌሎች ተማሪዎች ምን ማለቱ እንደሆነ ገምተው እንዲናገሩ የሚያበረታታ ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎች ድርጊቱን በማየት በንግግር ሐሳባቸውን መግለጽ ያስችላቸዋል።

2. ሚና ጨዋታ (Role play)፡- ሚና ጨዋታ ተማሪዎች በራሳቸው ገጠመኝ ሆነ በሌሎች ነባራዊ ሁኔታዎች ላይ ተመርኩዘው የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ለክርክርና ለውይይት ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

3. ችግሮችን አፍልቆ በውይይት መፍታት (Simulation)፡- ተማሪዎች የተወሰኑ ችግሮችን በማንሳት ለችግሮቹ መፍትሔ ወይም ውሳኔ ለመስጠት የሚሞክሩበት ነው።

በአጠቃላይ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ከተፈለገ እጅግ በጣም ብዙ በሆኑ ዘዴዎች ልንጠቀም እንችላለን። በክፍል ውስጥ ከምንጠቀምባቸው ተግባራት መካከል የሚከተሉት ተጠቃሾች ይሆናሉ፤

- ጨዋታዎች፣
- ችግር-ፈቺ ተግባራት፣
- ታሪክ ምሥረታ (በሥዕሎች)፣
- የሐሳብ ልውውጥ፣

በፕሮጀክት ላይ የተመሠረቱ መስተጋብራዊ ተግባራት እንደሚከተለው ይቀርባሉ፤

- የተዋቀሩ ወይም የተደራጁ የጥያቄና መልስ ልውውጦች፣
- የዜና ዘገባዎችን በማዘጋጀትና በመቅዳት አስመስሎ መናገር፣
- ወይይቶችን በተወሰነ ርዕስ ላይ በማዘጋጀት፣
- የታዋቂ ሰዎችን ንግግር በመቅዳት አስመስሎ መናገር፣
- ቃለ-መጠይቅ ማዘጋጀትና ወደ ተግባር መተርጎም ወ.ዘ.ተ ናቸው፡፡

ከላይ የጠቀስናቸውን ተግባራት ተጠቅመን ተማሪዎች የታቀደ ንግግር እና ዝግጅት ያልተደረገበት ወይም የዱብእዳ ንግግር እዲያከናውኑ ማድረግ ይቻላል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የመናገር ክሂልን የሚያዳብሩ መልመጃዎች አቀራረብን አደረጃጀት በተመለከተ አለም(1995:25) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፤

- አስቀድመው እንዲዘጋጁበት በማድረግ በክፍል ውስጥ ጭውውቶችን እዲያቀርቡ የሚገፋፉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- ጆሮ አረፍተነገሮችን እየጨረሱ እንዲናገሩ የሚያደርጉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- በጓደኞቻቸው ፊት ቀልድ እንዲናገሩ የሚያደርጉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- ሌሎችን መስለው ንግግር እንዲያቀርቡ የሚያደርጉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- አስቀድመው እንዲዘጋጁበት በማድረግ በክፍል ውስጥ አጫጭር ትረካዎች እዲያቀርቡ የሚገፋፉ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- በቃል ማብራሪያ ለማቅረብ የሚያስችሉ የንግግር ክሂልን ማዳበሪያ መልመጃዎችን ማዘጋጀት፣
- የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበት መንገድ እንዲተኮረበት ማድረግ፣
- በክፍል ውስጥ ክርክርን ውይይት የሚያደርጉበትን መንገድ የሚያመቻቹ መልመጃዎችን ማቀናበር፡፡

## 2.7. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች

የንግግርን ክሂል ትምህርት ለማስተማር እንደ ዝግጅቱ ሁሉ አቀራረቡም ከፍተኛ ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው፡፡ ስለዚህ ንግግርን የማስተማር ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚከተለውን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው (Byrne 1976:3-4)፤

17

### 2.6.1. አቀራረብ (Presentation)

በዚህ ወቅት የመምህሩ ተግባር እንደ መረጃ አቀባይ (Informant) መሆን ነው፡፡ መምህሩ የተለያዩ አዳዲስ መረጃ መሳሪያዎን በመጠቀምና በተቻለ መጠን በታላሚው ቋንቋ የሚቀርበውን ተግባር ግልጽና በማይረሳ መልኩ ማቅረብ አለበት፡፡ በዚህ ደረጃ የንግግር ትምህርቱ በምልልስ መልክ ወይም በንባብ መልክ ሊቀርብ ይችላል፡፡

በምልልስ መልክ የሚቀርበው ነገር፣

- የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታ ሊያሳድግ የሚችል አግባብነት ያለው ቋንቋ፣
- አጭር መልስ የሚፈልግ ተስማሚ የሆነ ቋንቋ፣
- በእውነታው ዓለም ሊደረግ የሚችል እና የእውኑ ዓለም ሰዎች ሊያደርጉት የሚችሉና ከክፍል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝነት ያለው የንግግር ተግባር፣
- ምልልሱ ተማሪዎችን ወደ ልምምድ ተግባር ሊመራ የሚችል መሆን ይገባዋል፡፡

በሌላም በኩል በምንባብ መልኩ የሚቀርብ ነገር፣

- ርዕሱን ማስተዋወቅ፣
- ስለርዕሱ የተለያዩ መፃህፍት ያነበቡትን በፊልሞች፣ በቴሌቪዥንን፣ ወ.ዘ.ተ የተመለከቱትን መሰረት በማድረግ እንዲናገሩ ማበረታቻ ማድረግ ይቻላል፡፡

### 2.7.2. ልምምድ (Practice)

በልምምድ ወቅት አብዛኛውን ተግባር የሚያከናውኑት ተማሪዎች ናቸው፡፡ Byrne (1986: 34-52) በተጨማሪ እንደሚገልጹት፣ ይህ ደረጃ አስቀድሞ በቀረበው የትምህርት ዐውድ መሠረት በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸውን ለማዳበር የሚለማመዱት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፦

- ገምተው እንዲናገሩ የሚያስችሉ መልመጃዎች (ለምሳሌ በሥዕሉ ላይ ሊኖር የሚችለውን እንዲገምቱ ማድረግ)፣

- ክፍት ቦታውን እንዲሞሉና ጥያቄዎችን በማምጣት እርስ በራሳቸው ምላሽ እንዲሰጡ፣
- የጥያቄና መልስ ልምምድ እንዲያደርጉ በማበረታታት ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ በተገቢውና የንግግር ተግባር እንዲፈጽሙ ማድረግ ይቻላል።

18

2.7.3 አፍልቆት (Production)

በዚህ ደረጃ ማንኛውም የመናገር ዕድል ለተማሪዎች በመስጠት ቋንቋውን በራሳቸው እንዲጠቀሙበት (በነጻነት እንዲገልጹ) ማድረግ ነው። በአፍልቆት ደረጃ ዋናው ትኩረት ተማሪዎች በቀላሉ እና በነጻነት የሚግባቡትን ዐውድ መፍጠር እንዲሁም በጋራ የሚሰሩትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።

## 2.8. የንግግር ትምህርት ማቅረቢያ ስልቶች

የንግግር ክሂል ትምህርት ዓላማ ለማሳካት የመማር-ማስተማር ሂደት ያግዛሉ የተባሉትን ዘዴዎች በሦስት ይከፈላሉ (Celce-Murcia 1991:127-132)።

### ሀ. ሥነልሳናዊ ይዘት ያላቸው ትምህርቶች ልምምድ

በዚህ የትምህርት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ሞዴል ስነልሳናዊ ይዘት (linguistic contents) ያላቸው ቅርጾችና በመሳሰሉት ዘዴዎች መዋቅሮች በሥዕል፣ በቃለ መጠይቅ፣ በጨዋታና በመሳሰሉት ዘዴዎች በመጠቀም ተማሪው ይበልጥ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ በመፍጠር የንግግር ክሂልን ማሳደግ የሚቻልበት ነው (Nunan 1991:46)።

### ለ. የንግግር ችሎታን ለማዳበር የሚደረግ ልምምድ

ይህ ዘዴ በመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪውን በቀጥታ በማሳተፍ የንግግር ክሂሉን ለማዳበር በከፍተኛ ሁኔታ የሚረዳ ነው። በዚህ ጊዜ ርዕሱን መምህሩ ወይም ተማሪዎች ሊመርጡ የሚችሉበትን ሁኔታ በማመቻቸት በክርክር ወይም በውይይት መልክ እንዲያከናውኑት ማድረግ ይቻላል።

### ሐ. የተሳትፎ ክንውኖች

ይህን ስልት መምህሩ የተወሰኑ ቃላትን እንደመንደርደሪያ በመስጠትና የሚተኮርበትን ጉዳይ ወስኖ በቡድን በመከፋፈል የአጭር ጊዜ ውይይት አድርገው የደረሱበትን ነጥብ

ከምክንያታቸው ጋር እንዲያቀርቡ ይደረግበታል። ይህ የተሳትፎ ክንውን ተማሪዎች የቋንቋውን ተፈጥሮአዊ ዐውድ ተጠቅመው ተግባቦታዊ ተግባራትን ለማከናወን ይረዳቸዋል።

## 2.9. ንግግርን የመማር/ማስተማር መርሖች

19

እንደበተ-ርቱዕነት ወይም የመናገር ብቃት የሚዳብረው በመደበኛ የመማር-ማስተማር ሂደት ነው። የመማር-ማስተማሩ ሂደት በበኩሉ በዘፈቀደ የሚመራ ሳይሆን በመርህ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገበዋል። ክሂሉን ስናስተምር የሚከተሉትን መርሆች እንድንከተል (Ur 1996:25) ይመክራሉ፤

**ሀ. ተማሪዎች ብዙ እንዲናገሩ ዕድል መስጠት፡-** የመናገር ክሂል የሚዳብረው በመናገር በመሆኑ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የተመደበውን ጊዜ ንግግርን በመለማመድ እንጂ መምህሩ ስለንግግር የሚሰጠውን ገለጻ በማዳመጥ ማሳለፍ አይኖርባቸውም። በጥንድ፣ በአነስተኛ ቡድንና በጋራ የሚወያዩበትን፣ የሚከራከሩበትን ወዘተ... ክንውን በማቅረብ በቋንቋው የመናገር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ መለማመድ ይጠበቅባቸዋል።

**ለ. የተማሪዎች የንግግር ተሳትፎ ማመጣጠን፡-** ሁሉም ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት እኩል የመሳተፍ እድል ማግኘት አለባቸው። በክፍል ውስጥ የሚከናወነው የንግግር ልምምድ በተወሰኑ ፈቃደኛ ተማሪዎች ብቻ መሸፈን የለበትም። የመናገር እድሉ በተቻለ መጠን ለሁሉም እኩል መድረስ አለበት።

**ሐ. የተማሪዎችን ጥረትና ተሳትፎ ማበረታታት፡-** ክሂሉን ለማለማመድ የሚመረጠውን ርእሰ ጉዳይ ወይም የመናገሪያ ክንውን እውናዊና አስደሳች በማድረግ የተማሪዎቹን የመናገር ፍላጎት ማነሳሳት ለክሂሉ ማዳበር ፋይዳው የጎላ ነው። ለዚህም ተማሪዎቹ የሚያውቁትና ከገጠመኞቻቸው ጋር በማያያዝ የሚናገሩበትን ርእሰ ጉዳይ መምረጥና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። ተማሪዎችን ለንግግር ከሚያነሳሷቸው ነገሮች አንዱ የሚናገሩበት ጉዳይ ከደረጃቸው፣ ከፍላጎታቸውና ከአካባቢያቸው ሁኔታ ጋር የተሳሰረ መሆኑ ነው። በማያውቁት ጉዳይ ላይ እንዲናገሩ መደረጋቸው ለመናገር የሚኖራቸውን ተነሳሽነት ስለሚቀንስባቸው ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል (Harmer 1991:125)።

**መ. ደረጃውን በጠበቀ መደበኛ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ማለማመድ፡-** ንግግርን በመማር ተማሪዎቹ ማዳበር የሚጠበቅባቸው ተገቢ በሆነ፣ አድማጭ በቀላሉ በሚገነዘበውና በትክክለኛነቱ ተቀባይነት ባገኘው ቋንቋ ሃሳባቸውን የመግለጽ ችሎታን ነው፡፡ ይህን ችሎታ ለማዳበር በአደራጃጀቱ፣ ለዐውዱ ባለው ተገቢነት፣ ርእስ ጉዳይን በማስተሳሰፍ ብቃቱ ከተማሪዎቹ ከተማሪዎቹ ደረጃ ጋር በሚጣጣም ቋንቋ የሚገለጽ ክንውን ሊቀርብላቸውና በተደጋጋሚ ሊለማመዱ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ የመናገር ክሂልን ለማዳበር በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችን ማእከል ያደረጉ ተግባራት መቅረብና በተማሪዎቹ መከናወን አለባቸው፡፡ የመማር-ማስተማሩ ሂደትም ተማሪዎቹ መሪ ተዋናይ የሚሆኑበት፣ ክፍለ ጊዜው በሁሉም ተማሪዎች ተግባራዊና ተመጣጣኝ ተሳትፎ የሚሸፈንበት፣ ስለንግግር የሚማሩበት ሳይሆን መናገርን የሚለማመዱበት እንዲሆን ይጠበቃል (Harmer 1991:124) ፡፡

## 2.10. ንግግርን የመማር ችግሮች እና መፍትሔያቸው

የመናገር ክሂል የሚዳብረው በመናገር ነው፡፡ ለመናገርም የተማሪው ፈቃደኝነትና መደፋፈር መኖር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የመማር ሂደት ንግግርን እንዳይለማመዱ የሚያደርጉና የመማሩን ስኬታማነት የሚያደናቅፉ ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች መከሰታቸው አይቀርም፡፡ ችግሮቹ እና መፍትሔዎቹ Ur (1996:46) እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፤

**ሀ. ለመናገር መፍራት፡-** ንግግር በግል የሚከናወን ተግባር ሳይሆን ተናጋሪውን ለአድማጭ የሚያጋልጥ ነው፡፡ ስለዚህ በልምምድ ሂደት ከተማሪዎች ፊት ቆመው ለመናገር እንዲደፋፈሩና ፍርሃትን እንዲያስወግዱ ልምምዱን በጥንድና በአነስተኛ ቡድን መጀመር ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚከናወነው ልምምድ በተማሪዎች መካከል መቀራረብን ስለሚፈጥር ለመናገር አለመድፈርን ፣ እሳሳታለሁ ብሎ መፍራትንና በሠው ፊት ቆመው ለመናገር አለመፍቀድን ያስወግዳል፡፡ ስለዚህ በመማሩ ሂደት የቡድን ንግግርን መነሻ ማድረግ አለብን፡፡

**ለ. ዝምታን መምረጥ፡-** ተማሪዎች ዝምታን የሚመርጡበት ምክንያት ያደጉበት ባህል፣ እንዲናገሩበት የተመረጠው ርዕስ ጉዳይ አዲስነት፣ የሚገልጹትን ሀሳብ ማጣት ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት ክሂሉን ለማለማመጃነት የሚመረጡትን ክንውኖች ተማሪዎቹ የሚያውቋቸውና በቀላል ቋንቋ ሲገለፀጹ የሚችሉ ማድረግ ነው፡፡ መልመጃዎቹ የሚቀርቡባቸው ቃላትና የቋንቋ አጠቃቀም ከደረጃው ዝቅ ያሉ፣ የተማሪዎቹ ገጠመኝ መሠረት ያደረጉ፣ ቀደም ሲል በተማሩትና በሚያውቁት የቋንቋ ይዘትና አጠቃቀም ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው ዝምታውን ለማስወገድና ለመናገር ድፍረትን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

21

*ለምሣሌ፡-*

የገጠር ተማሪ የባንክ ሠራተኛ ሆኖ እንዲናገር ከማድረግ የገበሬን፣ የሀይማኖት መሪን ወዘተ ሚና ወክሎ እንዲናገር ማድረግ ይመረጣል፡፡

**ሐ. የተማሪዎችን ተሣትፎ አለመመጣጠን፡-** በተለያዩ ምክንያቶች ለንግግር መለማመጃ የሚቀርቡት ተግባራት ሁሉንም የማያሣትፍበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ ይህ የተሳትፎ አለመመጣጠን ለሁሉንም አለመድረስ የተወሰኑ ተማሪዎችን አድማጭ ብቻ ስለሚያደርግ በንግግር ችሎታ መዳበር ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ይህን ችግር ለማስወገድ ለመናገር የሚያነሳሱ ርዕስ ጉዳዩችን በመምረጥ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል የመሣተፍ እድል መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በልምምዱ ሂደትም ተገቢውን ክትትል ማድረግ፣ ሁሉንም እኩል ተሣትፎ እንዲያደርጉ ማበረታታትና አስፈላጊውን ምግበ-መረጃ (feadback) መስጠት ከቋንቋ መምህሩ ይጠበቃል፡፡

**መ. በአፍ መፍቻ ቋንቋ መጠቀም፡-** ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በመማር ሂደት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መናገርን የሚመርጡበት ሁኔታ በተደጋጋሚ ያጋጥማል፡፡ ችግሩን ለማስወገድ ተማሪዎቹ በታላሚ ቋንቋ ሲናገሩ የሚፈጥሩትን ስህተት መቀበል፣ ማበረታታት፣ በጥንድና በቡድን ልምምድ ጊዜ ተገቢውን ክትትል ማድረግ እና በቋንቋውም እንዲናገሩ መገፋፋት ያስፈልጋል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች ለማስወገድ እና የመማሩን ዓላማ ለማሳካት የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅመው ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ከስልቶቹ መካከል (Harmer 1996፡129) እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

- የንግግር ክንውኖችን ማሠራት ፤
- ርዕሠ ጉዳዩን የሚቀርቡበት ቋንቋ ማቅለል፤
- ግልጽ የአሠራር መመሪያ መስጠት፤
- አነሳሽ ወይም አበረታች ክንውኖች መምረጥ፤
- በታላሚው ቋንቋ እንዲጠቀሙ ማድረግ ወዘተ፡፡

## 2.11. በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የመምህሩ ሚና

የአብዛኛውን ምሁራን አላማ ቋንቋውን በማስተማር ረገድ ትክክለኛውን ዘዴ መፈለግ ነው። ስለሆነም መምህራን ከዘመኑ የቋንቋ ማስተማር አቀራረብ ጋር ይበልጥ ዝምድና ሊኖራቸው ይገባል። የንግግር ክሂልን ስለማስተማር Nunan (1995:5) መምህራን ንግግር ከፅሁፍ ክሂል ጋር ያለውን ልዩነት እያነፃፀሩ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ትኩረት ሰጥተው ማመልከት እንዳለባቸው ገልፀዋል፤

- ተስማሚ የሆነውን የንግግር ቋንቋ የማስተማር ቅርፅ ወይም ሞዴል የትኛው ነው?
- የንግግርና የፅሁፍ ቋንቋ ልዩነቶች በግልፅ መቀመጣቸው? በአጠቃላይ መምህሩ የሚከተሉትን ነጥቦች ማከናወን እንዳለበት ምሁራኑ ያስረዳ፤
- የንግግር ክሂልን ትምህርቱ ካከናወነ በኋላ ከተማሪዎች ምግበ መረጃ ለማግኘት የተለያዩ መጠይቆችን በማዘጋጀት ማስሞላት፤
- ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ሂደት ውስጥ ስህተትን አንድ የመማሪያ መንገድ መሆኑን ተረድተው በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ነፃ ሆነው እንዲናገሩ ማበረታታት፤
- በቡድን ወይም በተናጠል ስራ ውስጥ መምህሩ እየዞረ በመከታተል ማበረታታት፣ ወዘተ. መምህራን በክፍል ውስጥ ንግግርን በሚያስተምሩበት ጊዜ ተግባራዊ ሊያደርጉባቸው የሚገቡ ተጋባራት አሉ። እነዚህም፡-
- የተማሪዎችን አቀማመጥ ለንግግር ተግባራት አመቺ እንዲሆን ማድረግ፤
- ለንግግሩ ተግባር የተማሪዎችን ትኩረት መሳብ የሚችል መግቢያ/ ፍንጭ መስጠት፤
- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በራሳቸው መንገድ እንዲገልፁ ማበረታታት፤
- ለንግግር ምሳሌ/ሞዴል የሚሆኑ ሰዎችን ወደ ክፍል መጋበዝ፣ወዘተ…

(በድሉ፣1996፡67-68)።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የጥናቱ ክንዋኔ

በምዕራፍ አንድ ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማርያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር መፈተሽ ነው። ጥናቱ የተከተለው ዓይነታዊ ምርምር (Qualitative Research) ሲሆን፣ አቀራረቡም ገለጻዊ (Descriptive) ነው። በዚህም መሠረት ጥናቱ ይዞት ከተነሳው ግብ አኳያ አሠራሩም እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

## 3.2. የተጠኚዎች ናሙና አመራረጥ

### 3.2.1. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በአፋር ክልል፣ በዞን አንድ አራት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ላይ ነው። ከክልሉ መስተዳድር የትምህርት ቢሮ በተገኘ መረጃ መሠረት ካሉት 24 አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ በታላሚ ናሙና በመጠቀም ሦስት የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል። እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡበት ምክንያት፡-

- በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ዞኖች በርካታ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙበት ዞን በመሆኑ፣
- የተመረጡት ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸው ቦታዎች ርቀት ተቀራራቢ በመሆኑ ጥናቱን በታቀደው ጊዜ ለማጠናቀቅ ስለሚያግዝ ነው።

ለጥናቱ የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም ከዚህ ቀጥሎ በሠንጠረዥ መልክ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 1፦ የትምህርት ቤቶች ስም፣ የሚገኙበት ወረዳና ከተማ መግለጫ

| ተ.ቁ | የት/ት ቤቶች ስም | የሚገኙበት ወረዳ | የሚገኙበት ከተማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሎጊያ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ዱብቲ | ሎጊያ |
| 2 | ሚግሎኪቦ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ዱብቲ | ሠመራ |
| 3 | ፐላንቴሽን አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ዱብቲ | ዱብቲ |

## 3.2.2. የተጠኚ ተማሪዎች የክፍል ደረጃና የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ

### 3.2.2.1 የተጠኚ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

የሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት የሚካተቱት የክፍል ደረጃዎች 5ኛ፣6ኛ፣7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች ናቸው፡፡ ከነዚህ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ 8ኛ ክፍል በታላሚ ናሙና አመራረጥ ዘዴ የጥናቱ ተተኳሪ ሆኖ ተመርጠዋል፡፡ ለዚህም ዋና ምክንያቱ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለንግግር ክሂል ትምህርት ተመርጠው የቀረቡት ይዘቶች ከሌሎች የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ክፍሎች ይልቅ ቁጥራቸው በርከት ብሎ በመገኘቱ ሲሆን፣ ይህም ለጥናቱ መካሄድ በቂ ናሙና ሆነው ስለሚያገለግሉ መረጃው አስተማማኝ እንዲሆን ያደርጉታል ከሚል እምነት የተነሳ ነው፡፡

### 3.2.2.2 የመማሪያ ክፍል ናሙና አመራረጥ

የክፍሎች አመራረጥን በተመለከተም ተተኳሪ መምህራን ከሚገቡባቸው አምስት ክፍሎች ውስጥ ከያንዳንዱ ትምህርት ቤት አንድ አንድ ምድብ በድምሩ ሦስት ምድቦች በእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል፡፡ ምክንያቱም ትምህርት ቤቶቹ የጥዋት ፈረቃ ክፍለ ጊዜ ብቻ በመሆናቸው ለክፍል ደረጃው የሚያስተምሩ መምህራን ለምልከታው አመቺ ሆነው በመገኘታቸው ነው፡፡

### 3.2.3. የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

#### 3.2.3.1. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በንሲብ ናሙና በተመረጡ ሦስት ትምህርት ቤቶች የሚገኙት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቁጥራቸው ዘጠኝ ሲሆን ሁሉም የጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። በሂደቱም ሁሉም መምህራን መጠይቁን እንዲሞሉ ሲደረግ የምልከታውን መረጃ ለመሰብሰብ ግን፣ ከጊዜ፣ ከገንዘብና ከሰው ኃይል አኳያ ታይቶ ካሉት መምህራን ውስጥ የተወሰኑትን ብቻ መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። አመራረጡም በኢላማዊ ናሙና አማካኝነት ሲሆን ለጥናቱ ጠቃሚ የሆነ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የሚታሰቡ መምህራን በናሙናነት ተጠኚ እንዲሆኑ ተደርገዋል። በዚህ ጊዜ ታሳቢ የተደረገው የአገልግሎት ዘመን፣ ጾታንና የእፍ መፍቻ ቋንቋን ነው። የተጠኚ መምህራን ዳራዊ ሁኔታ በአጠቃላይ መረጃ መሠረት በማድረግ በየትምህርት ቤቱ ረዘም ያለ የማስተማር ልምድ ያላቸውና የቅርብ ጊዜ ምሩቃን የሆኑትን በሉጊያ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት ሁለት መምህራን የተወሰዱ ሲሆን፣ በሚግሉኪቦና በፕላንቴሽን አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ደግሞ በያንዳንዱ ትምህርት ቤት አንድ አንድ መምህር በጥናቱ እንዲታተፉ ተደርገዋል። በአጠቃላይ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ቁጥር አራት ነው።

#### 3.2.3.2. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በየትምህርት ቤቶቹ የሚገኙት ተማሪዎች በቁጥር የሚበላለጡ ከመሆናቸው በስተቀር ችሎታን መሠረት ባደረገ ምደባ የተደለደሉ አለመሆናቸው ከየትምህርት ቤቶቹ አስተዳደሮች በተገኘ መረጃ ተረጋግጧል።

ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ከተመረጡት አምስት ክፍሎች ውስጥ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል በአማካኝ 65-75 ተማሪዎች ይገኛሉ። የመነሻ ቁጥር በዕጣ ከተለየ ቡኃላ አንድ እልፎ አንድ በመውሰድ ከእያንዳንዱ ትምህርት ቤት 20 በአጠቃላይ 60 ተማሪዎች ተመርጠው የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል። ተማሪዎቹ የጽሑፍ መጠይቁን እንዲሞሉ የተደረጉት የክፍል ውስጥ ምልከታውን መሠረት በማድረግ ነው። የተማሪዎቹ ናሙና

አመራረጥ የየትምህርት ቤቶቹ ተማሪዎች ቁጥርም ሆነ በመምህራኑ የሚሸፍኑትን ምድቦች ብዛት ከግምት ውስጥ ያላስገባ ነው፡፡ ከተማሪዎቹ የሚሰበሰበው መረጃ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ያጠናክራል በሚል እሳቤ የተካሄደ ነው፡፡ የተማሪዎቹን አመራረጥ በተመለከተ መረጃው በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

ሠንጠረዥ 2፦ የተማሪዎቹንም ሆነ የመምህራኑን ናሙና አመራረጥ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ቤት ስም | የክፍል ብዛት | ለጥናቱ የተመረጡ ክፍሎች ብዛት | የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብዛት | | የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራን ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በት/ት ቤት | ናሙና | በት/ት ቤት | ለናሙና መጠይቅ | ለምልከታ |
| 1 | ሉጊያ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | 2 | 1 | 155 | 20 | 4 | 4 | 2 |
| 2 | ሚግሉኪዮ አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | 1 | 1 | 78 | 20 | 2 | 2 | 1 |
| 3 | ፕላንቴሽን አንደኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | 2 | 1 | 117 | 20 | 3 | 3 | 1 |
| | ድምር | 5 | 3 | 350 | 60 | 9 | 9 | 4 |

## 3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበርን መፈተሽ ነው። የጥናቱ አከባቢ፣ የትምህርት ቤቶቹ፣ የመምህራንና የተማሪዎች ናሙናዎች ከተመረጡ በኋላ መረጃ የመሰብሰቡ ሥራ ተከናውኗል። የሚሰበሰቡት መረጃዎች አስተማማኝ ይሆኑ ዘንድም በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝተዋል። በመሆኑም ለጥናቱ መረጃዎች ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

### 3.3.1 የማስተማሪያ መርጃ መሣሪያዎች

በመማር-ማስተማር ሂደት ዓላማ፣ ይዘት፣ ሥነ-ዘዴ እና ትንተና ተነጣጥለው የማይታዩ ናቸው። የመማሪያ መጽሐፉ ከመርሐ-ትምህርቱ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። በሌላም በኩል የማስተማር ሥነ-ዘዴው ትግበራ በመምህሩ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው በተመረጡ ይዘቶችና ክንውኖች ነው። በመሆኑም ጥናቱ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የማስተማር ዘዴ ትግበራ በተናጠል መገምገም ለጥናቱ መሳካት አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያሳድር በመገመት በማስተማሪያ መሣሪያዎች የቀረቡትን ክንውኖች፣ ዝርዝር ዓላማዎች፣ ይዘቶችና መልመጃዎችን እንዲሁም የአቀራረብ ዘዴዎችን ለመፈተሽ ሙከራ አድርጓል።

### 3.3.2. የክፍል ውስጥ ምልከታ (Classroom Observation)

በተጠኚ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚስተዋለው የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የመማር-ማስተማር ክንውን ለመታዘብ ምልከታ በመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያነት በጥቅም ላይ የዋለ ዋንኛው መሣሪያ ነው። ምልከታው በሦስቱም ናሙና ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩትን 4(44.44%) መምህራን አካትቷል።

የምልከታ መረጃ የተሰበሰበው ከሕዳር 7-24/2003 ዓ.ም. ባሉት ሦስት ተከታታይ ሳምንቶች ነው። የምልከታውን መረጃዎች የመሰብሰቡ ተግባር የተሳካ ለማድረግም በንግግር ክሂል ትምህርት ሂደት፣ የመምህራንና ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ባሕርያት ለመከታተል የሚያስችሉና አስቀድመው በተዘጋጁ ዝርዝር መከታተያ ቅጾች (Observation checklist) ከUr (1996:110-121) እና Brown & Youle (1987:17) የንግግር ክሂል ትምህርት ክንውን መርሖችና ከNunan (1996:115) የክፍል ውስጥ ምልከታ መከታተያ ቅጾች ሐሳብ በመውሰድ ለጥናቱ አመች እንዲሆን በማሻሻል ተከናውኗል። መከታተያ ነጥቦቹ በአማካሪዬ (ዶ/ር አረጋ ኃ/ሚካኤል) ከታየ በኋላ የማሻሻል ሥራ ተደርጎበት በሥራ ላይ ውሏል። ምልከታው የተካሄደው በተጠኚ ትምህርት ቤቶች በሚገኙ አራት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፊል ውስጥ ሲያስተምሩ በመታዘብ ነው።

የክፍል ውስጥ ምልከታው ደግሞ ቀደም ሲል ከመምህራኑ ጋር በተያዘው አመቺ የክፍለ ጊዜ ምልከታ መርሐ-ግብር በማዘጋጀትና ለረዳት ተመልካች በመከታተያ ቅጾች ላይ ስለተጠቀሱት ክንውኖችና መስፈርቶች እንዲሁም ስለአሞላሉ ግንዛቤ በማስጨበጥ የቅድመ-ምልከታ ተግባራት ተከናውኗል። ምልከታው በእያንዳንዱ ተጠኚ መምህር ላይ ሁለት (4X2=8) ጊዜ የተካሄደ ሲሆን ከረዳት ተመልካች ጋር በአንድነት በመሆን ተከናውኗል።

### 3.3.3. **የጽሑፍ መጠይቅ** (Questionnaires)

የክፍል ውስጥን የንግግር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር በሚመለከት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማሰባሰብ እንዲቻል ለመምህራንና ለተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ቀርበዋል። የጽሑፍ መጠይቁ መሠረታዊ ዓላማው በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታዎች የተገኘውን መረጃ ለማገናዘብ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ነው። ይህም መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበራቸው በተመለከተ ያላቸውን ግንዛቤና አቀራረባቸው ምን እንደሚመስል የሚጠይቁ ክፍሎች ያካተተ ነው።

የጽሑፍ መጠይቁ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ለተመሳሳይ ዓላማ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው። ይኸውም በሁለቱ የመጀመሪያው ክፍል በዳራዊ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩሩ ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በመማር-ማስተማር ሂደት የሚከናወኑ ተግባራትን ያካትታል። ለመምህራን የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ለተተኳሪዎቹ መምህራን ተበትኖ በቂ ጊዜ አግኝተው እንዲሞሉት ተደርገዋል። ለተማሪዎች የተዘጋጀ የጽሑፍ መጠይቅም፣ አጥኚው በየትምህርት ቤቶቹ በመገኘት የተመረጡትን ተማሪዎች ለብቻቸው በመለየትና ስለመጠይቁ አጠቃላይ ዓላማና አሞላል ማብራሪያ ከተሰጣቸው በኋላ፣ በየግላቸው እንዲሞሉት ተደርገዋል። የተበተኑት መጠይቆችም በሙሉ ተሞልተው ተመልሰዋል።

በጽሑፍ መጠይቆች ውስጥ የሚገኙት ዝርዝር ጥያቄዎች በትንተናው ጊዜ በሠንጠረዥ መልክ ቀርበው ይገኛሉ። በየሠንጠረዡ የሚገኙትም ፊደሎችና አኃዞች የየራሳቸው ውክልና ይኖራቸዋል።

## 3.4. የመረጃ አተናተን

በዚህ ጥናት ከማስተማሪያ መረጃ መግሪያዎች፣ ከምልከታ፣ ከመምህራንና ተማሪዎች መጠይቅ፣ ከተሰበሰቡ መረጃዎችና ውጤቶች በመነሳት በክፍል 1.2 ሥር ለቀረቡት የዓላማ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ትንተና ተደርጓል። ትንተናው በሁለት ንዑስ ምዕራፎች የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው ንዑስ ክፍል መረጃዎች የተተነተኑበት ነው። መረጃዎቹ በሚያነሱት ጉዳይ ተከፋፍለው በሠንጠረዥ ውስጥ በቁጥርና በመቶኛ (%) ቀርበዋል።

ሁለተኛው ንዑስ ምዕራፍ በመረጃ ትንተና የታየው ውጤት የተብራራበት ነው። ውጤቱንም ከሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች፣ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ከሚሰራቡት ስነ-ዘዴና ትግበራ፣ የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር በተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ሥር ከሠፈሩት ንድፈ ሐሳቦች ጋር መጣጣማቸውን ለመፈተሽና መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ እንዲሁም ከሥነ-ዘዴው ውጤታማነት አንጻር ለማብራራት ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተና

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው፣ የጥናቱ ዓላማ በ8ኛ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የንግግር ክሂል ለማዳበር ዘመናዊ የንግግር ማስተማር ደረጃዎችን ተከትለው የትምህርት ሂደቱን የማከናወን ግንዛቤያቸው ለመፈተሽ፣ ሂደቱን ተከትለው ማከናወን አለማከናወናቸውን ገምግሞ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በመግለጽ ደካማ ጎኑ እንዲሻሻል፣ ጠንካራ ጎኑ ደግሞ እንዲቀጥልና የመፍትሔ ሐሳብ ለመጠቆም ነው። በመሆኑም በምዕራፍ ሶስት እንደተገለጸው፣ የዚህ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ምልከታ፣ የጽሑፍ መጠይቅ፣ እንዲሁም መርሀ ትምህርቱ፣ መምሪያ መጽሐፉና የመምህሩ መምሪያ ናቸው። በእነዚህ መሣሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በዝርዝር እንደሚከተለው ተተንትነው ቀርበዋል።

## 4.1. የመረጃዎች ትንተና

### 4.1.1. ከማስተማሪያ መሣሪያዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያና መማሪያ የተዘጋጁት መሣሪያዎች፣ መርሀ ትምህርት፣ መማሪያ መጽሐፍና የመምህሩ መምሪያ የንግግር ክሂል በመማር-ማስተማር ሂደት እውን የሚሆኑ ዓላማዎችን፣ መልመጃዎችን ወይም ክንውኖችንና የትምህርት አቀራረብ ዘዴን ያካተቱ መሆናቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።

ሠንጠረዥ 3፦ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ የንግግር ክሂል መልመጃ ይዘቶች የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ዐበይት ዓላማዎች | የመልመጃ ይዘቶች | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | % |
| 1 | የማዳመጥ | 13 | 8.49 |
| 2 | የመናገር | 25 | 16.33 |
| 3 | የማንበብ | 30 | 19.6 |
| 4 | የመጻፍ | 35 | 22.87 |
| 5 | የሥነልሳን | 30 | 19.6 |
| 6 | የሥነጽሑፍ | 20 | 13 |
| | ድምር | 153 | 100 |

በሠንጠረዡ እንደሚታየው በመርሐ-ትምህርቱ የቀረቡ ዝርዝር ዓላማዎችና ይዘቶች ለተግባራዊ ልምምድ በቀረቡበት መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተለያየ የድግግሞሽ መጥን ቀርበዋል፡፡ በዚህ መሠረት የንግግር ክሂል መማሪያ ግብአቶች ማለትም የክሂልና የዕውቀት ዘርፍ ይዘቶች ከጠቅላላው ይዘቶች ውስጥ 11.46% በመያዝ የሶስተኛ ደረጃ ይዘዋል፡፡ የመጻፍ ክሂል በ26.75% አንደኛ ደረጃ ሲይዝ የማንበብና ስነ-ልሳን በ22.92% በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ሌሎችም ክሂሎችና የዕውቀት ዘርፎች በተወሰነ የድግግሞሽ መጠን ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

ሠንጠረዥ 4፦ በመርሐ-ትምህርቱ የቀረቡ የንግግር ክሂል ትምህርት ዝርዝር ዓላማዎች ይዘቶች፣ ክንውኖች፣ የግምገማ ነጥቦችን ብዛት የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | የትምህርት ጠቅላላ ዓላማዎች | ዝርዝር ዓላማዎች | | ዝርዝር ይዘቶች | | ክንውኖች | | ግምገማዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥ | በመቶኛ | በቁጥ | በመቶኛ |
| 1 | የማዳመጥ | 10 | 16.66 | 10 | 16.66 | 38 | 19.58 | 13 | 25 |
| 2 | የመናገር | 11 | 18.33 | 11 | 18.33 | 33 | 17 | 9 | 17.3 |
| 3 | የማንበብ | 12 | 20 | 12 | 20 | 42 | 21.64 | 8 | 15.3 |
| 4 | የመጻፍ | 12 | 20 | 12 | 20 | 53 | 27.31 | 12 | 23 |
| 5 | የስነልሳን | 8 | 13.33 | 8 | 13.33 | 20 | 10 | 6 | 11.5 |
| 6 | የስነ-ጽሑፍ | 7 | 11.66 | 7 | 11.66 | 8 | 4.12 | 4 | 7.69 |
| | ድምር | 60 | 100 | 60 | 100 | 194 | 100 | 52 | 100 |

ከሠንጠረዡ እንደተመለከተው የንግግር ክሂል ለደረጃው ከቀረቡት የዕውቀትና የክሂል ዘርፎች በጠቅላላው 18.33% ዝርዝር ዓላማዎች ተሰጥቶታል፡፡ ለትግበራ ከቀረቡት ጠቅላላ ክንውኖች 194 ውስጥ 17% በመያዝ በሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የግምገማ ነጥቦችን በሚመለከትም ከቀረቡት 52 ነጥቦች 15.33% ይዞ በሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

ለደረጃው በተዘጋጀው የመምህሩ መምሪያ ላይ በግልጽ እንደተጠቀሰው በተለይ ማዳመጥና መናገርን የክሂል ዘርፎች ለማስተማር በመምህሩ መምሪያ መታገዝ የግድ ነው ይላል፡፡ ነገር ግን የንግግር ትምህርት በሚለው ክፍል ውስጥ የቀረቡት አንዳንድ ዓላማዎች እና ይዘቶች የንባብ ክሂልን ለማዳበር እንዲያግዙ ሆነው የቀረቡበት ሁኔታ ታይቷል፡፡

ሠንተረዥ5፦ ከመምህሩ መምሪያ የተገኙ የንግግር ክሂል ትምህርትን አቀራረብ

የሚመለከቱ መረጃዎች መግለጫ

| ተ.ቁ | የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ |
|---|---|
| 1 | የተለያዩ ጥያቄዎችን እንደ ትእዛዙ በንግግር እንዲመልሱ ማድረግ፣ |
| 2 | ሥዕላዊ መግለጫውን ከምንባቡ ጋር በማገናዘብ ንግግር እንዲያደርጉና /እንደየአስፈላጊነቱ/ ፍንጭ ሰጭ ሐሳብን ማብራራት፣ |
| 3 | የንግግር ተግባራትን በጋራ እንዲሰሩ ማበረታታት፣ |
| 4 | በጥንድ/በቡድን ተገናኝተው ውይይት/ክርክር እንዲያደርጉ ማድረግ፣ |
| 5 | የተመረጡ ጥሩና ደካማ ተግባራትን ለክፍሉ በማቅረብ ድክመትና ጥንካሬያቸውን እንዲናገሩ ማድረግ፣<br>ሌሎች አመቺ ዘዴዎችን ሁሉ በመጠቀም ተማሪዎች የመናገር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማበረታታት (1991፡25)። |

ሠንጠረዥ 6፦ በመርሐ-ትምህርትና በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡትን የንግግር

ክሂል ትምህርት ይዘቶች ብዛትና ስርጭት የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | የንግግር ክሂል ትምህርት ግብአቶች/ይዘቶች | በመርሐ-ትምህርቱ | በመማሪያ መጽሐፉ |
|---|---|---|---|
| 1 | አንድን ሐሳብ በልዩ ልዩ አባባል መግለጽ፣ | ✓ | |
| 2 | የአንድን ንግግር ይዘት በራሳቸው አባባል መግለጽ፣ | ✓ | |
| 3 | አጫጭር ማብራሪያዎችን መስጠት፣ | ✓ | |
| 4 | በግል አስታየትና በዕውነታ መካከል ያለውን ልዩነት | | ✓ |
| 5 | አንድን የተሰጠ ሐሳብ ማሳጠር፣ | | ✓ |
| 6 | በአንድ ጉዳይ ላይ አስታየት መስጠት፣ | | ✓ |
| 7 | ሥዕሎች፣ ቅርጻ ቅርጾች፣ ወዘተ. በተለያዩ መንገዶች | ✓ | |
| 8 | የአንድን ነገር ድርጊት በራስ አባባል መግለጽ፣ | ✓ | ✓ |
| 9 | ትረካ በቅደም ተከተል መግለጽ፣ | ✓ | |
| 10 | ውጡን ታሪክ መጨረስ፣ | ✓ | ✓ |
| 11 | የድራማን ታሪክና ገጸ-ባህርያትን መናገር፣ | ✓ | ✓ |
| 12 | በአንድ ርእሰ-ጉዳይ ላይ ተዘጋጅቶ ንግግር ማድረግ፣ | ✓ | |
| 13 | ገለጻ ማድረግ፣ | ✓ | ✓ |

በሠንጠረዥ እንደተመለከተው፣ ንግግርን ለማስተማርና ሐሳብን በንግግር የመግለጽ ችሎታን ለማዳበር በመርሐ-ትምህርቱ የቀረቡት ይዘቶች በመጠኑ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተካትተዋል፡፡ የቀረቡት የክሂሉን ግብአቶች በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ የሚሆኑበት ሥነ-ዘዴ ወይም የይዘቶች አቀራረብና የክንውኖች አሠራር ቴክኒኮች በመምህሩ መምሪያ በየምዕራፎቹ መቅረባቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተገኙት መረጃዎች መሠረት በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተግባራዊ የሚሆኑት የመምህሩና የተማሪው ሚና በአብዛኛው ተራክቧዊ ዘዴን መሠረት ያደረገ ይመስላሉ፡፡ ለማስረጃ ያህል የሚከተሉትን ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል፤ መናገር በሚለው ክሂል ሥር ዝርዝር ዓላማና ይዘት ውስጥ የሚከተሉት ሰፍረዋል፡፡

- የቀረቡላቸውን ምንባቦች ዋና መልእክት በቃል ይገልጻሉ፡፡ ዓላማ
- የምንባቡን ዋናመልእክት በቃል መናገር፡፡ ይዘት

### 4.1.2. ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

#### 4.1.2.1. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ

እንደ Byrne (1976:35) አገላለጽ፣ ተማሪዎች ወደ ዋናው ተግባር ከመግባታቸው በፊት የማንቃቃት ስራ ትምህርት ለሁሉም የንግግር ክሂል ትምህርት ደረጃዎች እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡ በክፍል ውስጥ ምንም አይነት ተግባር ቢከናወን የተማሪዎችን ፍላጎት ከፍ ለማድረግና ለንግግሩ ተግባር ይበልጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማስቻል የማንቃቃት ስራ በጣም ወሳኝ ነው፡፡

የማንቃቃት ሥራ ተማሪዎች ወደ ዋናው ተግባር ከመግባታቸው በፊት ታስቦ የሚከናወን ከሆነ የተፈለገውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ዓይነተኛ መሣሪያ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ የተማሪዎቹን ፍላጎት በማነሳሳት ተግባቦታዊ ችሎታቸውን የሚያሳድግ፣ ገጠመኞቻቸው ከእለት ተእለት ሕይወታቸው ጋር አብረው የሚሄዱ ተግባራትን በመምረጥ እነሱን መሠረት በማድረግ ቀጣዩን ሥራቸው የሚያከናውኑበትን ሁኔታ በግልጽ ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ ተማሪዎች የንግግር ተግባራቱን እንዴት ማቅረብ እንዳለባቸው ሞዴል በመስጠትና በነጻነት እንዲናገሩ የመምህራን አስተዋጽኦ

ከፍተኛ ነው። ከዚህ አንጻር በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶችና የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋን የሚያስተምሩ ተተኳሪ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ እንዴት እንደሚተገብሩ ለማየት የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ምልከታዎች ተካሂደዋል። ምልከታውም የመምህራንን የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ባሕርያት ለመከታተል የሚያስችሉና አስቀድመው በተዘጋጁ ዝርዝር የምልከታ መከታተያ ቅጾች የታገዘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 7፦ መምህሩ የዕለቱን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተግባራትን አቀራረብ አስመልክቶ በምልከታ የተገኘ ውጤት የሚያሳይ ሠንጠረዥ፤

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሠረት የማድረጉ ሁኔታ፤ | - | - | 3 | 75 | 1 | 25 | - | | - | |
| 2 | የዕለቱን የንግግር ትምህርት በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎች የማነቃቃቱ ሁኔታ፤ | - | - | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | |
| 3 | የተወሰነና ግልጽ ዓላማ ይዞ የመግባቱ ሁኔታ፤ | - | - | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - |
| 4 | የዕለቱን የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ የራስ ፈጠራና የማስተማሪያ መሣሪያዎች የመጠቀሙ ሁኔታ፤ | - | - | - | - | - | - | - | - | 4 | 100 |

ከሠንጠረዡ መረዳት የሚቻለው፣ በትምህርት ቤቶቹ አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ በሚገኙ የ8ኛ ክፍል መምህራን በተካሄዱት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተከታታይ ምልከታዎች ውስጥ የተማሪዎችን ችሎታ ለማዳበር የተለያዩ የንግግር ተግባራትን ወደ ክፍል በማምጣት የዕለቱን ትምህርት ለማቅረብ የሞከረው 1(25%)

መምህር ብቻ ነው፡፡ 3(75%)ቱ መምህራን የዕለቱን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ለደረጃው በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ በመጠቀም አስተምረዋል፡፡ ይህም በመሆኑ አብዛኛዎቹ መምህራን የተወሰነና ግልጽ ዓላማ ይዘው እንዳይገቡ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሮባቸዋል፡፡ ስለዚህም የተወሰነና ግልጽ ዓላማን በማስገኘት ላይ ያተኮረ የንግግር ተግባር ልምምድ በማቅረብ ረገድ በሌሎች መምህራን የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሳ ነው፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ካስተማሩ ተተኳሪ መምህራን መካከል 2(50%) መምህራን በመጠኑ ወደ ዋናው ተግባር ሲገቡ የዕለቱን ትምህርት በበቂ ሁኔታ ይስማመዱ ዘንድ የማነቃቂያ ሥራ መሥራታቸውን ማስተዋል ተችሏል፡፡ 2(50%) መምህራን ደግሞ ምንም ዓይነት የማነቃቂያ ሥራ ሳይሠሩ በቀጥታ ወደ ዋናው ተግባር ገብቷል፡፡ መምህራኑ የዕለቱን የንግግር ትምህርት የጀመሩት ከዚህ በፊት ለተማሪዎቻቸው የተሰጣቸውን መልመጃ በማስቀደም ደብተራቸውን እንዲያወጡ ከአዘዙ ቡኋላ በጥያቄና መልስ መልክ ጥያቄዎችን ለመሥራት ሞክረዋል፡፡

በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ተግባራትን በምን ዓይነት ደረጃ እንደሚቀርቡ በማያሻማ ሁኔታ አውቆ የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት እንዲሁም ዕድሜና የትምህርት ደረጃ ሊመጥኑ የሚችሉ የተለያዩ ሞዴሎችን በማምጣት ወደ ዋናው ሥራ የማስገባት ሁኔታ ከማንኛውም የቋንቋ መምህር የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡ በክፍል ምልከታው የተከናወነውን ተግባር ስንመለከት ተጠኚ መምህራን ተማሪዎች ወደ ዋናው ሥራ እንዲገቡ ለማነቃቃት ባለመሞከራቸው የተሰጣቸውን ሥራ ለመጀመር ብዙ ደቂቃዎችን አጥፍቷል፤ በተለይ በሁለተኛው የክፍል ምልከታ ትምህርቱ ከተጀመረ ቡኋላ በዕለቱ "ትዳር" በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ በቡድን በመሆን ውይይትና ክርክር እንዲያደርጉ የታዘዙት ተማሪዎች በቀጥታ ወደ ሥራው እንዲገቡ በመደረጋቸው እርስ በርስ መደማመጥ የሌለበትና ሥርዓቱን ያልጠበቀ ክንውን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህም መምህራን የማነቃቃት ስራ ባለመሥራታቸው፣ ውይይትና ክርክር መድረክ ላይ እንዴት እንደሚያቀርቡ እና ምን ምን ነገሮች እንደሚያስፈልጉ መምሪያዎችና ሞዴል

ተግባራት ባለመቅረባቸው ተማሪዎች ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዳይናገሩ መሰናክል ፈጥሮባቸዋል።

የቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባራት በተገቢውና በተፈለገው ሁኔታ ያከናወኑ ዘንድ ግልጽ ዓላማ ይዘው የመግባታቸው ሁኔታ፣ የሚጠቀሙባቸው የማስተማሪያ መሣሪያዎች ከሳይንሱ፣ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ስነ-ልቦና ፣ ከትምህርት ደረጃ፣ ከተማሪዎቹ ማንነትና ይዘውት ከመጡት ባህል፣ ወግና ልማድ ጋር ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል። የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ተማሪዎቹን የሚያነሳሱ፣ የሚያሳትፉ እንዲሁም ለውይይትና ክርክር የሚጋብዙ ርእሶችን በቂ ጊዜ ወስዶ መምረጥና ማዘጋጀት ጠቀሜታው የጎላ ነው።

ከፍ ሲል በሠንጠረዥ 3 እንደተጠቀሰው፣ በክፍል ውስጥ በተደረጉ ተከታታይ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፣ አብዛኞዎቹ መምህራን የዕለቱን የንግግር ትምህርት አቀራረብ የራስ ፈጠራን የተለያዩ የማስተማሪያ መሣሪያዎች የመጠቀሙ ሁኔታ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ነው። ይኸውም 4(100%) መምህራን ምልከታ በተደረገባቸው ጊዜያት ምንም አይነት የማስተማሪያ መሣሪያዎች አለመጠቀማቸውን ነው።

## 4.1.2.2.የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ልምምድ

እንደ Byrne (1986:34) ገለጻ፣ በልምምድ ወቅት የሚከናወኑት ተግባራት አስቀድሞ በቀረበው የትምህርት ዐውድ መሠረት በቋንቋው ተጠቅመው የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ነው። ስለዚህ መምህሩ አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ሊያመቻችላቸው ይገባል። በክፍል ምልከታው ወቅት የተገኙት መረጃዎች በሠንጠረዥ መልክ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 8፡- የመምህሩ የዕለቱ የንግግር ትምህርት ልምምድ አቀራረብ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 5 | የዕለቱን ትምህርት ሞዴል በማቅረብ ትርጉም ያላቸው ተግባራት እንዲያከናውኑ አድርጎ ነበር? | - | - | - | - | 2 | 50 | 2 | 50 | - | - |
| 6 | በልምምድ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ | - | - | 1 | 25 | - | - | 3 | 75 | - | - |
| 7 | በዕለቱ የቀረበውን ተግባር ተማሪዎችን ወደ ልምምድ እንዲገቡ የማድረጉ ብቃት | - | - | 2 | 50 | - | - | 2 | 50 | - | - |
| 8 | ልምምዱ ለማድረግ የተጠቀመበት የመማር-ማስተማር ተራክቦ | 2 | 50 | 1 | 25 | 1 | 25 | - | - | - | - |
| | • በጥንድ/በቡድን | - | - | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | - | - |
| 9 | የንግግር ተግባሩን ለመለማመድ በቂ ጊዜ የመስጠቱ ሁኔታ | - | - | 2 | 50 | - | - | 2 | 50 | - | - |

በትድመ ንግግር ትምህርት ወቅት አጭር መልስ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን በምልልስ መልክ መምህሩ ቢያቀርብ ተመራጭነት እንዳለውና ለማስተማሪያነት የሚጠቀምበትንም ሞዴል ተግባር በቴፕ ቀድቶ በማምጣት ወይም ራሱ በማስመሰል ሊያቀርብላቸው እንደሚገባ Byrne (1986:34) ይገልጻሉ፡፡

ከሠንጠረዥ አምስት መረዳት የሚቻለው፣ ሞዴል ተግባሩን በመጠነኛ ሁኔታ ማቅረብ የሞከሩት ሁለት መምህራን ሲሆኑ ሌሎቹ መምህራን ግን ተግባራዊ አላደረጉትም፡፡ በዚህ ምክንያት በሚቀርበው የንግግር ትምህርት ላይ ይበልጥ ተማሪዎችን የማሳተፍ

ስልት ከአንዱ መምህር በስተቀር የሌሎቹ መምህራን የማሳተፍ ብቃት ደካማ ሆኖ ተገኝቷል።

እንደ Byrne (1986:34) አገላለጽ በልምምድ ወቅት የሚቀርቡ ይዘቶች ተማሪዎች በተሰጣቸው ሞዴል መሠረት ተለማምደው ቀጣዩ የንግግር ትምህርት ልምምዶች እንዲፈጽሙ፣ አቀራረቡ ከተማሪዎች ፍላጎት ጋር አብሮ የሚሄድ፣ ጊዜ የማይወስድ፣ አጭርና ገንቢ መሆን ይኖርበታል ይላሉ። ነገር ግን የምልከታውን መረጃ እንደሚጠቁመው ከሁለት መምህራን በስተቀር ንግግር እንዴት እንደሚያደርጉ ለተማሪዎች ገለጻ በመስጠት ብዙ ጊዜ አጥፍቷል። በዚህም ምክንያት ተማሪዎች የሚሠሩትን ሥራ በአግባቡ ሳይረዱ በቀጥታ ወደ ልምምዱ ተግባር የገቡበት ሁኔታ ተስተውሏል።

አብዛኞቹ ምሁራን እንደሚያስረዱት የክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት በቡድን ሥራ ቢታገዝ ከዘመናዊው የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ጋር ከመያያዙም ባሻገር መምህር-መር የሆነውን የትምህርት አሰጣጥ እንዲቀንስ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው። እንደ Ur(1996:121) አገላለጽ፣ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን ችግር ለማስወገድ የቡድን ሥራው በአግባቡ ከተከናወነና የተማሪዎችን ፍላጎት በሚያሟላ ዐውድ ላይ ከተመሠረተ የተማሪዎችን ትኩረት በተሰጣቸው ሥራ ላይ ብቻ እንዲያውሉ ማድረግ ይቻላል።

በመማር-ማስተማሩ ሂደት የጥንድና የቡድን ተራክቦ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የንግግር ተግባራትን ለማለማመድ የሚያስችሉ ተግባራት በምልከታው ወቅት የቀረቡ ምዕራፎች የተካተቱ ቢሆኑም በክፍል ውስጥ ተማሪዎች በተግባር ሲለማመዱ አልታየም።

መምህራኑ ለትምህርት የተመደበውን ጊዜ ለማነቃቂያ፣ ለማስተዋወቂያ፣ ለማለማመጃ፣ ለማጠናከሪያና ለመገምገሚያ ወይም ማጠቃለያ ከፋፍለው በዕለት ዕቅዳቸው ላይ ቢያስፍሩም 2(50%) በተግባር ላይ እንዳላዋሉት ለመገንዘብ ተችሏል።

ከሠንጠረዥ ስምንት ማስተዋል የሚቻለው፣ አብዛኛዎቹ መምህራን ልምምዱን ለማድረግ የተጠቀሙበት የመማር-ማስተማር ተራክቦ በግል ሲሆን ይኸውም ለንግግር ተብሎ የቀረበው ትምህርት ከዚህ በፊት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ካነበቡት ምንባብ

"ትዳር" ከሚለው የወጡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች በደረቁ በጥያቄና መልስ መልክ መግለጫ በመስጠት የማስተማሩ ሂደትም ለተወሰኑ ተማሪዎች ዕድል በመስጠት ጥያቄውን እንዲመልሱ ያደርጉ ነበር፡፡ የተጠየቁ ተማሪዎች የማይመልሱት ከሆነ መምህሩ በራሳቸው መግለጫ ይሰጣሉ እንጂ መልሰው ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን እንዲወያዩበት የማበረታታቱ ሁኔታ ከአንድ መምህር በስተቀር በሌሎች መምህራን ዘንድ አልታየም፡፡ ይህንን አስመልክቶ Ur (1996:121) ሲገልጹ፣ ለንግግር ትምህርት የተመደበለት የጊዜ መጠን በተቻለ ሁኔታ ተማሪዎች ከቀደመ እውቀታቸው በመነሳትና ገጠመኞቻቸው መሠረት በማድረግ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን በራሳቸው ቋንቋ ሀሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የንግግር ትምህርት የልምምድ ተግባራት የመምህሩ ሚና ምን እንደሚመስል በተከታታይ ምልከታዎች የተገኙት መረጃዎች እንደሚከተለው በሠንጠረዥ መልክ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 9፡- የንግግር ትምህርት በልምምድ ተግባር ወቅት የመምህሩ ሚና

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘይው ትግበራ | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 10 | መምህሩ በንግግር ተግባራት ጣልቃ በመግባት ማብራሪያ የመስጠቱ ሁኔታ፤ | - | - | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 | - | - |
| 11 | ተማሪዎች በቂ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ልምምድ እንዲያደርጉ የተለያዩ ዘይዎችን ተጠቅሟል? | | | | | | | | | | |
| | • ፍንጭ በመስጠት | - | | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 | - | - |
| | • በመደጋገም | - | | - | | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - |
| | • በማስመሰል | - | | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - |
| 12 | በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች የመቆጣጠር ሁኔታ፤ | - | | 1 | 25 | - | - | 1 | 25 | 2 | 50 |
| 13 | በልምምድ ተግባራት ሁሉንም ተማሪዎች የማሳተፍ ሁኔታ፤ | - | | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - |
| 14 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ፤ | - | | - | - | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 |
| 15 | ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የማድረጉ ሁኔታ፤ | - | | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - |
| 16 | ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ የተረዱት መሆኑን የመገንዘብ የመቆጣጠር ሁኔታ፤ | - | | - | - | 1 | 25 | 3 | 75 | - | - |
| 17 | በአፈ-ተ-ክነት (fluency) ላይ ያተኮረ የንግግር ትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ፤ | - | - | 1 | 25 | 1 | 25 | 2 | 50 | - | - |

ምሁራኑ እንደሚሉት መምህሩ በክፍል ውስጥ በሚቀርበው ተግባር ላይ ልምምድ በሚደረግበት ወቅት ጣልቃ በመግባት እርማት ለመስጠት መሞከር ቀጣይ የሆነውን የመማር-ማስተማር ተግባር እንደመግታት የሚቆጠር በመሆኑ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፤ አላስፈላጊ እርማትን በመስጠት ተማሪዎችን ማሸማቀቅ የለበትም፡፡ መምህራን ለማረም ቢሞክሩም ተማሪዎች በቀጥታ በማያውቁት መንገድ በተለየ ስልት ለማስተካከል ሙከራ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

የተካሄዱትን ምልከታዎች ውጤት ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው፣ ከ1(25%) መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን በተማሪዎች የንግግር ልምምድ ጣልቃ መግባትና ንግግርን እንዴት ሊያከናውኑ እንደሚችሉ ማብራሪያ በመስጠት ላይ ያተኮሩ እንደነበር ነው፡፡ መምህራኑ በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት ማብራሪያ ከመስጠታቸው በተጨማሪ የተማሪዎችንም ስህተት በቀጥታ ለማረም ሲሞክሩ ተስተውሏል፡፡ በተለይ አንደኛውን መምህር ተማሪዎቹ በሚያደርጉት ንግግር ጣልቃ በመግባት ቁጣ በታከለበት አነጋገር "ምንም አትችሉም በቃ እንደሱ አይደለም" በማለት የተናገረበት ሁኔታ ተከስቷል፡፡ አንዱ መምህር ግን በዚህ ጉዳይ ለየት ያለ አቀራረብ ታይቶበታል፡፡ የተሰጣቸውን ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ተማሪዎች በቀረበው ርእሰጉዳይ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ካደረገ ቡኋላ የተዘጋጀውን ክርክር እንዲመለከቱ ሁኔታዎችን አመቻችተዋል፡፡ ክርክሩ በሚቀርብበት ወቅት ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያለምንም ጣልቃ ገብነት እንዲከናወን አድርጓል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በቀረበው ክርክር ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ አድርጓል፡፡ ይህም ሁሉንም ተማሪዎች የማሳተፉ ሁኔታ ከፍ እንዲልና ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ በማድረግ ከሌሎች መምህራን በተለየ መንገድ እንዲያከናውን አግዞታል፡፡ በሌሎች መምህራን የንግግር ክሂልን በመማር-ማስተማር ሂደት ላይ ብዙ ችግሮች ታይተዋል፡፡ በተማሪዎች ዘንድ የተመጣጠነ ተሳትፎ አለመኖርና ተሳትፎው በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ ሲያዝ ምንም ዓይነት ጥረት ሲያደርጉ አልታዩም፡፡ ይህንን በተመለከተ Byrne (1987:55) ሲገልጹ፣ "በክፍል ውስጥ በሚደረገው የንግግር ትምህርት ተግባራት ተሳትፎው በተወሰኑ ተማሪዎች እንዳይያዝ መምህራን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል፡፡" ይላሉ፡፡ ለምሳሌ በአንድ ክፍል የተደረገውን ምልከታ ብንመለከት እድል

የተሰጠው አንድ ተማሪ ብዙ ደቂቃ በመውሰድ የዓረፋ በዓል እንዴት እንዳሳለፈው ለመናገር ሞክሯል። በዚህ ሁኔታ ሌሎች ተማሪዎች በእሱ ንግግር መርዘም ምክንያት የየግላቸውን ወሬ እንዲያወሩና የክፍሉ ጸጥታ እንዳይከበር አድርጎታል።

ስለዚህም ተማሪዎቹን መቆጣጠርና ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ ተሳትፎ ለማድረግ መምህራን ባለመጣራቸው በክፍል ውስጥ ንግግርን በማስተማር ረገድ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። በተጨማሪም መምህራን በጥንድ ወይም በቡድን ሥራ ወቅት ተማሪዎች በትኩረት የሚሰሩትን ሥራ ማበረታታትና የተረዱት መሆኑን ትኩረት መስጠት አለባቸው።

የምልከታው መረጃ እንደሚያስረዳው ግን ከ1 (25%) መምህር በስተቀር በሌሎቹ መምህራን ይህ ሁኔታ ተግባራዊ አለመሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህም የመምህራን ጣልቃ ገብነት ሳይኖር የንግግር ተግባሩን የሚማሩበት አውድ በመፍጠር ሀሳባቸውን እንዲገልጹ የማበረታታቱ ሁኔታ በመምህራን ዘንድ ትኩረት እንዳልተሰጠው መረዳት ተችሏል።

በሌላም በኩል 1(25%) መምህር፣ ተማሪዎች በቂ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ልምምድ እንዲያደርጉ ከራሱ ገጠመኝም ሆነ ካለው ልምድ ተነሥቶ ለሚደረገው የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ሞዴሎችን በማቅረብ፣ ለሚሠሩት ሥራ ፍንጭ በመስጠትና በክፍል ውስጥ ጓደኞቻቸው ያቀረቡትን በማስመሰልና በመደጋገም ሥራ እንዲሠሩ አድርጓል። ይህ በመደረጉም ተማሪዎች በነጻነት ሐሳባቸውን እንዲገልጹ አድርጓል። ሌሎች መምህራን ግን ይህንን ክንውን ተግባራዊ ባለማድረጋቸው ተማሪዎች በነጻነት ሀሳባቸው እንዳይገልጹ የተገደበበት ሁኔታ ይታይ ነበር።

እንደ Ur (1996:120) አገላለጽ፣ የአፈ-ተክነት (fluency) ተግባር በክፍል ውስጥ እንዲቀርብ መደረጉ ተማሪዎች በንግግር ሐሳባቸውን የመግለጽ ችሎታቸው እንዲያዳብሩ የሚያደርግ በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። ይህ ሁኔታም በአብዛኛው ተማሪዎች በጥንድና በቡድን የሚማሩበትን የንግግር ትምህርት ስሕተት እየሰሩም ቢሆን በነጻነት እንዲጠቀሙበት የሚያበረታታና የሚያግባባ ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የምልከታውን መረጃ ስንመለከት፣ ምልከታ ከተካሄደባቸው መምህራን መካከል ከ2(50%)ቱ መምህራን በስተቀር ሌሎች መምህራን ተማሪዎች በሚሳሳቱበት ወቅት ጣልቃ በመግባት ስህተቶችን ለማስተካከል ሲሞክሩ ተስተውሏል። ተግባሩን ካከናወኑ 2(50%) መምህራን በተለይ አንደኛው መምህር ተማሪዎች በቀረበው ርእሰጉዳይ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ካደረገ በኃላ የተዘጋጀውን ክርክር እንዲከታተሉ ሁኔታዎችን አመቻችቷል። ክርክሩ በሚካሄድበትም ወቅት ሐሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ያለምንም ጣልቃ ገብነት እንዲከናወን አድርጓል።

መምህራን የንግግር ክሂል ትምህርትን ተግባራት በሚያስተምሩበት ጊዜ ተግባራቱ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ችሎታቸውን የሚያሳድጉና ሐሳባቸውን በነጻ የሚገልጹባቸው መሆን እንዳለባቸው Byrne (1986:55) ይገልጻሉ።

እንደ Berhanu (1994:217) ገለጻ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ሰፋ ያለ ንግግር እንዲያደርጉና ተግባቦታዊ ችሎታውን ለማዳበር የሥነ-ጽሑፍ ስራዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አላቸው። የንግግር ተግባራት ዋና አላማ ተማሪዎችን የሚያነሳሱ አውዶች መፍጠር ሲሆን የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ስራዎችን በማምጣት በጥንድ ወይም በቡድን ነጻ የሆነ ውይይት እንዲያካሂዱ ተማሪዎችን ማነቃቃትና ማበረታታት ይቻላል። መምህራን የልምምዱን ተግባር ሲያከናውኑ በምን ዓይነት ስልቶች እንደተጠቀሙና በልምምዱ ወቅት የነበራቸውን ሚና በሚቀጥለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 10፡- ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ መምህሩ ያመቻቸበት ሁኔታ

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 18 | የልምምዱን ተግባር የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን በማምጣትና ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎችን እንዲመልሱ የማድረጉ ሁኔታ፤ | - | - | 2 | 50 | - | - | - | - | 2 | 50 |
| 19 | ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻች ነበር? | - | - | 1 | 25 | - | - | 3 | 75 | - | - |
| 20 | ውይይቶችንና ክርክሮችን በማዘጋጀት የንግግር ተግባር እንዲያከናውኑ የማድረጉ ሁኔታ፤ | - | - | 1 | 50 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 |
| 21 | የሚቀርቡ ተግባራት ተግባቦታዊ ችሎታቸውን ሊያዳብሩ የሚችሉ ናቸው? | - | - | - | - | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 |
| 22 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት ሊያግባባ የሚችል አውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው። | - | - | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | 1 | 25 |
| 23 | ተማሪዎች ቋንቋቸውን ተጠቅመው በራሳቸው መንገድ ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ ያበረታታ ነበር። | 1 | 25 | 1 | 25 | - | - | 2 | 50 | - | - |
| 24 | ሥዕሎችንና ሌሎች የሚታዩ ነገሮችን ሰጥቶ እንዲተረጉሟቸው ያደርግ ነበር። | - | - | - | - | | - | - | - | 4 | 100 |

ከሠንጠረዥ 10 ማየት እንደመሚቻለው፤ ለንግግር ትምህርት በክፍል ውስጥ ለልምምዱ ተብለው የቀረቡት ጥያቄዎች የወጡት ለክፍሉ ደረጃ በተዘጋጀው መጽሐፍ ነው። አንዳንዶቹ መምህራን የቀረበውን ምንባብ መጽሐፉ በሚያዘው መሠረት ወደ ክርክር በመቀየር የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር ሲሞክሩ ሌሎቹ ግን ከመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በጥያቄና መልስ ያሰሩ እንደነበር በሁሉም ክፍል የተካሄደው የምልከታ መረጃ ያመለክታል። 1(25%) መምህር "በከፍተኛ ሁኔታ" 1(25%) መምህር ደግሞ "በመጠነኛ ሁኔታ" በልምምዱ ተግባር

ዙሪያ ላይ ፍንጭ በመስጠት በጥያቄና መልስ መልኩ ተማሪዎች እንዲመልሱ አድርጓል። አንደኛው መምህር "ታታሪው አርብቶ አደር" በሚል ርእስ የተጠየቅ ተጠየቅ ሙግት ከመቅረቡ በፊት ስለሚከናወነው ክርክር ክርእሱ በመነሣት እንዴት ክርክር እንዲያደርጉ ሲያደርግ ሁለተኛዋ መምህር ደግሞ ስለ "ዓረፋ በዓል አከባበር ሁኔታ" ተማሪዎች ንግግር ለማድረግ እንዲያስችላቸው ምሳሌ ለመስጠት ጥረት አድርጋለች። ይህ ሁኔታ ተማሪዎች የሚናገሩትን ነገር እንዳያጡና ተሳትፏቸው እንዲጎላ ከማድረጉም በተጨማሪ ለንግግር ትግበራው እንዲነሳሱ በከፍተኛ ሁኔታ ያስችላዋል። ሌሎች 2(50%) መምህራን ግን ለደረጃው በተዘጋጀው መጽሐፍ የወጥቱን ጥያቄዎች በቀጥታ ለማሠራት ሞክሯል።

እንደ Harmer (1991፡105) ገለጻ፣ ንግግርን ለማስተማር ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው በተመረጡ ርእስጉዳዮች ተማሪዎች አስቀድመው ተዘጋጅተው ወይም ተለማምደው ውይይት ወይም ክርክር በማድረግ ሁሉም ተማሪዎች በሚያሳትፍ መልኩ ሲቀርብ ነው። ተማሪዎች በተሰጣቸው ርእስጉዳይ ላይ እንዲወያዩ፣ እንዲለማመዱና በቋንቋው ተጠቅመው ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ መምህራን እንዲያበረታቱ ይመረጣል።

ነገር ግን በክፍል ውስጥ በተደረገው የምልከታ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ 1(25%) መምህር በ "ከፍተኛ" ሁኔታ በክፍል ውስጥ ተግባራዊ አድርጓል። ይኸውም "ታታሪው አርብቶ አደር" በሚል ክርክር የተሳተፉትን የተለያዩ ቡድኖች ክርክሩን ያከናወኑበት ሁኔታ እንዲገመግሙ ለተማሪዎች እድል በመስጠት ያላቸውን ድክመትና ጥንካሬ ምን እንደሚመስል ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ አበረታቷል። ከዚህ ጋር በተያያዘም ይህ መምህር ተማሪዎች የተሰጣቸውን ስራ በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ በመጠኑም ቢሆን ተግባራዊ ሲያደርግ ሌሎች መምህራን ግን ይህን ዓይነት ተግባር ትኩረት እንዳልሰጡ ለማወቅ ተችሏል።

Harmer (1991:105) ተማሪዎች በቋንቋቸው ተጠቅመው ስለሚያከናውኑት ተግባር በቀላሉና በነጻነት ሊያግባባ የሚችል አውድ እንዲኖር መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ነገር ግን በመማር-ማስተማር ሂደት የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው ለማለት አያስችልም። የክፍል ውስጥ የምልከታው መረጃ

እንደሚያመለክተው 1(25%) መምህር ብቻ ይህን ሁኔታ ተግባራዊ እንዳደረገ ለመገንዘብ ተችሏል። በዚሁም ተማሪዎች ቋንቋቸውን ተጠቅመው በራሳቸው መንገድ ሐሳባቸውን በነጻ የሚገልጹበት ሁኔታ ሲያመቻች ተስተውሏል። በሌሎች መምህራን የቀረቡ የንግግር ተግባራት ግን በአብዛኛው የተማሪዎች ተግባቦታዊ ችሎታን፣ በጋራ የመስራት ሁኔታን፣ ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ እንደነበር ከምልከታው መረጃ መረዳት ተችሏል።

በመማር-ማስተማሩ ሂደት በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በሚቀርብበት ጊዜ ሥዕሎችን፣ ቅርጻ ቅርጾችንና ሌሎች የሚታዩ የሚታዩ ነገሮችን ሰጥቶ ተማሪዎች እንዲተረጉሟቸው የማድረጉ ሁኔታ አንድም መምህር እንደሌለ ከሠንጠረዡ መረዳት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 11፡- የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የመማር-ማስተማር ሂደት ተራክቦ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴው ትግበራ | አማራጮች | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | | ሠ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 25 | መምህሩ የተማሪዎችን ስሕተት የሚርምበት ሁኔታ፣ • በቀጥታ | 2 | 50 | 1 | 25 | - | - | 1 | 25 | - | - |
| | • በተዘዋዋሪ | - | - | - | - | - | - | - | - | 3 | 75 |
| 26 | የመምህሩ የክፍል ውስጥ ምጋቤ-ምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ፣ • በመምህሩ | 3 | 75 | 1 | 25 | - | - | - | - | - | - |
| | • በተማሪ | - | - | 1 | 25 | - | - | 1 | 25 | 2 | 50 |

ከላይ በቀረበው የምልከታው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው፣ ከ1(25%) መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን ተማሪዎች ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት ስሕተታቸውን የሚያርሙት በቀጥታ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ለምሳሌ በሁለት ክፍል (sections) የተካሄደውን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ብንመለከት ሁለት መምህራን በአፋር ባህል (አዳ) መሠረት የአፋር የጋብቻ ሁኔታ እንዴት እንደሚፈጸም ተናገሩ ብለው ከጠየቁ በኋላ ተማሪዎች ተወያይተው መመለስ ሲገባቸው መምህራኑ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥቷል። ስሕተታቸውም የሚታረመው በቀጥታ በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት እንደነበር ነው። ነገር ግን በክፍሉ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የተለያዩ የህይወት ገጠመኝ ያላቸው በመሆኑ በቡድን ሐሳብ ለሐሳብ እርስ በራሳቸው የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸው ነበር።

በአጠቃላይ መምህራን በክፍል ውስጥ የምጋቤ-ምላሽ አሰጣጥ ትኩረት ያልተሰጠበት ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ Celce-Murcia (1991:147) ሲገልጹ፣ በክፍል ውስጥ የምጋቤ-ምላሽ (feedback) አሰጣጥ በተለያዩ መንገዶች ሊሰጥ እንደሚችልና ከነዚህ ውስጥም፣ ተማሪው ልምምድ ወይም ንግግር በሚያካሄድበት ጊዜ በገሉ ራሱን ስሕተቱን የሚያወጣበት መንገድ ማመቻቸት፣ ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን የየራሳቸውን ስህተት እንዲያርሙ ማድረግ ሲሆን፣ ሌላው ስሕተቶች በተደጋጋሚ በብዙ ተማሪዎች ከፍ ያለ ስሕተት ሲሰራ የመምህሩ ምጋቤ-ምላሽ ሲኖር እርግጥ የተማሪዎችን ተግባቦታዊ ተግባር ማደናቀፍ እንደሌለበት ምሁሩ ይገልጻሉ።

ሠንጠረዥ 12፡ ለትግበራ የቀረቡ መልመጃዎችን ምንጭ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | የመማር-ማስተማሩ ሂደት የቀረቡ ግብአቶች ምንጭ | የተጠቀሙ መምህራን | | ያልተጠቀሙ መምህራን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | መማሪያ መጽሐፉ | 4 | 100 | - | - |
| 2 | በመምህሩ የተመረጡ ርእሰ-ጉዳዮች | - | - | 4 | 100 |
| 3 | በተማሪዎች የተመረጡ ርእሰ-ጉዳዮች | - | - | 4 | 100 |
| 4 | ሌሎች ማጣቀሻ ጽሑፎች | - | - | 4 | 100 |

በሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው፣ ምልከታ የተካሄደባቸው ጊዜያት ተጠኚ መምህራኑ በሙሉ የንግግር ክሂል ትምህርት ግብአቶችን ያቀረቡበት ለደረጃው የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፍ በመጠቀም ነው።

## 4.1.3. ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች

### 4.1.3.1. ከመምህራን የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት ትኩረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የመምህራን የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር ሂደት መምህራኑ የሚኖራቸውን ሚና መሠረት ያደረገ ነው። በመጠይቁ ውስጥ ጥናቱን ለማከናወን የተመረጡት የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው። ለዚህም በተከታታይ ምልከታዎች የተገኙ መረጃዎች የትንተና ውጤቶች የሚያሳዩት ተተኳሪዎቹ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴና አተገባበራቸው ሲታይ በአብዛኛው ተገቢ እንዳልነበሩ ያጠቁማሉ። ምክንያቱም ተገቢ ወይም ዘመናዊ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ አለመሆናቸው ነው። ከዚህ አንጻር መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርቱን በሚያቀርቡበት ጊዜ አተገባበራቸው ተገቢውን መንገድ ያልተከተሉበት ምክንያት ምን እንደሆነ ለመፈተሽ ሲባል ለተተኳሪዎቹ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸዋል። የመጀመሪያው ክፍል አጠቃላይ መረጃን ለማወቅ የቀረቡ ጥያቄዎች የተካተቱበት ሲሆን እንደሚከተለው በሠንጠረዥ መልክ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 13፡- የተተኳሪ መምህራን ዳራዊ መግለጫ

| የትምህርት ቤት ስም | መምህር | ጾታ | ዕድሜ | የት/ት ደረጃ | የትምህርት መስክ | | በተቋማት ያገኙት ስልጠና | | በስራ ላይ እያሉ ስልጠና | | የማስተማር ልምድ | የአፍ መፍቻ ቋንቋ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ዐቢይ | ንዑስ | ነበር | አልነበረም | ነበር | አልነበረም | | |
| ሉጊያ 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ሀ | ሴት | 32 | 12+2 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 13 | አማርኛ |
| | ለ | ወንድ | 27 | 12+2 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 5 | አማርኛ |
| | ሐ | ሴት | 30 | 12+3 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 1o | አማርኛ |
| | መ | ወንድ | 27 | ዲፕሎማ | እንግሊዝኛ | አማርኛ | ✓ | | | | 7 | አፋርኛ |
| ሚገሉሲቦ 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ሀ | ወንድ | 30 | 12+2 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 11 | አማርኛ |
| | ለ | ሴት | 26 | ዲፕሎማ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | | ✓ | | 3 | አፋርኛ |
| ፕላንቴሽን 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | ሀ | ወንድ | 26 | 10+3 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 10 | አፋርኛ |
| | ለ | ሴት | 26 | 10+3 | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 8 | አማርኛ |
| | ሐ | ወንድ | 34 | ዲፕሎማ | አማርኛ | እንግሊዝኛ | | ✓ | | ✓ | 15 | አፋርኛ |

ከቀረበው ሠንጠረዥ መመልከት እንደሚቻለው፣ ተተኳሪ መምህራን፣ ከአንዱ መምህር በስተቀር፣ ከሠለጠኑባቸው ኮሌጆች በአማርኛ ቋንቋ የትምህርት መስክ ሠልጥነው የወጡ መሆናቸው ነው። ከዜጠኙ ተተኳሪ መምህራን መካከልም ሦስቱ ዲፕሎማ፣ ስድስቱ ደግሞ ሰርተፊኬት ያላቸው ናቸው። ከትምህርት ደረጃቸው አንጻር ሲታይም ለስምንተኛ ክፍል ቋንቋን ለማስተማር ብቃት ያላቸው ሦስት መምህራን ብቻ እንደሆኑ እንረዳለን።

ዱሬዊ መግለጫው በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ከአራቱ መምህራን በስተቀር አምስት መምህራን ከአስር ዓመት በላይ በማስተማር ተሰማርተው የቆዩ ናቸው። ይህ ሆኖ ሳለም ተተኳሪዎቹ መምህራን ሠልጥነው ከወጡበት ኮሌጅ ወይም ተቋም የንግግር ክሂል ትምህርትን በዘመናዊ የማስተማሪያ ዘዴ ለማስተማር የሚያስችል የወሰዱት ሥልጠና እንዳልነበረ ስምንቱ መምህራን ምላሽ ሲሰጡ፣ አንድ መምህር ግን ሥልጠና እንደወሰዱ ገልጸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ስምንቱ መምህራን በስራ ቆይታ ጊዜያቸው ምንም አይነት ሥልጠና ወስደው እንደማያውቁ መልስ ሲሰጡ አንዱ ግን በአንድ ወቅት ሥልጠና እንደወሰደና ከዚያም ለቋንቋ ክሂሎች ትምህርት ለማስተማር ግንዛቤ ማግኘቱን ጠቁሟል። ከግማሽ በላይ የሚሆኑ መምህራን እድሜያቸው ከ30 በላይ ነው።

ስለዚህ አብዛኛዎቹ ተተኳሪ መምህራን በጽሑፍ ከሰጧቸው መልስ መረዳት የሚቻለው ከ2 መምህር በስተቀር በተቋማቱ ቆይታቸውም ሆነ በሥራ ከተሰማሩ በኃላ ግንዛቤያቸውን ሊያሰፉ የሚችል ስልጠና አለማግኘታቸው ነው። ስለሆነም መምህራኑ ዘመናዊ ትወራን መሠረት ያደረገ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ለተማሪዎቻቸው ለማቅረብ የሚያሳድሩት ተጽእኖ ቀላል እንዳልሆነ መገመት ይቻላል።

በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት የመምህራን ግንዛቤ መኖር ወሳኝ ሚና አለው። ስለሆነም የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ምርጫና አተገባበር መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ ለመመርመር ለመምህራኑ የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡትን መልስ በሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት።

ሠንጠረዥ 14፦ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ

በተመለከተ መምህራን ያላቸውን ግንዛቤ የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | የመላሾች ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ክሂሎች በክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴን በዘመናዊ መንገድ በተማርከበት/ሽበት ተቋም ተምርሃል/ሻል? | 2 | 22.22 | 2 | 22.22 | 4 | 44.44 | 1 | 11.11 |
| 2 | መልስም "ሀ"ወይም "ለ" ከሆነ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ምን ያህል አግዞውታል? | 1 | 25 | 2 | 50 | 1 | 25 | - | - |
| 3 | የጥንድ ወይም የቡድን ስራን ያበረታታሉ? | 1 | 11.11 | 8 | 88.88 | - | - | - | |

ከመምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ 1(11.11%) መምህር ክሂሎችን በክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴን በዘመናዊው መንገድ እንደተማረና የንግግር ክሂልንም ለማስተማር እንዳገዘው ገልጿል። የምልከታው መረጃም እንደሚያመለክተው ይህ መምህር የትምህርት አቀራረቡን፣ ልምምዱንና ተግባሩን በአንጻራዊነት መልኩ ከሌሎች መምህራን በተሻለ መንገድ ለማከናወን ችሏል። 2(22.22%) መምህራን በአብዛኛው በተማሩበት ተቋም ዕውቀቱን እንደቀሰሙ ገልጸው ሁለቱ በአብዛኛው ንግግርን ለማስተማር ከፍተኛ እገዛ እንዳደረገላቸው ሲያመለክቱ፣ 1(11.11%) ደግሞ በመጠኑ ያገዘው መሆኑን አስፍረዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ 4(44.44%) መምህራን በመካከለኛ ደረጃ እንደተማሩት ሲናገሩ 1(11.11%) መምህር ደግሞ በአብዛኛው በስልጠና ሂደት ያልወሰደ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል።

በሌላም በኩል የቡድን ወይም የጥንድ ሥራን እንደሚያበረታቱ መምህራን ተጠይቀው ሲመልሱ፣ 1(11.11%) መምህር "ሁል ጊዜ"፣ 8(88.88%) መምህራን ደግሞ "በአብዛኛው" እንደሚጠቀሙ ገልጸዋል። ነገር ግን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ የመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የቡድን ሥራ በከፍተኛ ሁኔታ ተግባራዊ ያደረገው አንድ መምህር ብቻ ነው።

ሠንጠረዥ 15፡- የንግግር ክሂል ትምህርት እንደሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች እየተሰጠው ያለውን ትኩረት የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 4 | የንግግር ክሂል ትምህርት ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች እኩል ተመጣጥኖ በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ። | - | - | 1 | 11.11 | 5 | 55.55 | 3 | 33.33 |
| 5 | የንግግር ትምህርት ተግባራት ከሌሎች የክሂል ትምህርቶች ጋር ተጣጥመው በክፍል ውስጥ አቀርባለሁ። | - | - | 5 | 55.55 | 4 | 44.44 | - | - |

የክሂል ትምህርቱ ከሌሎች ትምህርቶች እኩል ተመጣጥኖ ስለመቅረቡ መምህራን ተጠይቀው፣ 1(11.11%) "በከፍተኛ ሁኔታ" እየቀረበ እንደሆነ ሲገልጹ፣ 5(55.55%) የሚሆኑት ደግሞ የክሂል ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች "በመጠኑ" እኩል እየተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል። ቀሪዎቹ 3(33.33%) የሚሆኑት መምህራን "በዝቅተኛ ሁኔታ" የሚሰጥ መሆኑን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

ከዚሁ ጋር በተቀራራቢ ለቀረበው ጥያቄ የንግግር ትምህርት ተግባራት ከሌሎች የክሂል ትምህርቶች ጋር ተጣጥመው በክፍል ውስጥ መቅረቡን ተጠይቀው 5(55.55%)

የሚሆኑ መምህራን "ከፍተኛ" የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆን 4(44.44%) የሚሆኑት ደግሞ "በመጠኑ" ተጣጥሞ ይቀርባሉ ብለዋል።

የተሰጠው ምላሽ በአጠቃላይ ስንመለከት፣ የክሂል ትምህርቱ ከሌሎች የቋንቋ ትምህርቶች እኩል ተመጣጥኖ በክፍል ውስጥ ከሌሎች የክሂል ዘርፎች ጋር ተጣጥሞ ስለመቅረቡ በደረጃው የሚያስተምሩት መምህራን ደፍረው ለመናገር የተቸገሩ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ሠንጠረዥ 16፦ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂልን ትምህርት አቀራረብ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 6 | የንግግር ትምህርትን ከምንባብ በሥዕሉ መልመጃዎች አማካኝነት በጥያቄ እና መልስ መልክ እስተምራለሁ። | 4 | 44.44 | 2 | 22.22 | 2 | 22.22 | 1 | 11.11 |
| 7 | ከንግግር ትምህርት በፊት ስለንግግር አቀራረብ ተማሪዎቼ እንዲያውቁ አደርጋለሁ። | 2 | 22.22 | 2 | 22.22 | - | - | 5 | 55.55 |
| 8 | ወደ ዋናው የንግግር ተግባር ከመግባቴ በፊት የሚነቃቃት ሥራ (motivation) እከናውናለሁ። | 3 | 33.33 | 5 | 55.55 | 1 | 11.11 | - | - |
| 9 | የንግግር ተግባሩን ከመለማመዳቸው በፊት አጋዥ መርጃ መማሪያዎችን በመጠቀም በግልጽና በማይረሳ መልኩ ሞዴሎችን /ምሳሌዎችን/ አጠር ባለ መልኩ አቀርባለሁ። | 3 | 33.33 | 5 | 55.55 | 1 | 11.11 | - | - |
| 10 | ተማሪዎች በቀረበላቸው ሞዴል የንግግር ተግባር መሰረት የማስመሰል እና የመደጋገም ሥራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ። | 4 | 44.44 | 3 | 33.33 | 2 | 22.22 | - | - |

በሠንጠረዡ እንደተጠቀሰው በተተኳሪው የክፍል ደረጃ ላይ ከ2 (22.22%) ተ፡ መምህራን በስተቀር ለንግግር ትምህርት የሚሆኑ ግብአቶችን የሚያቀርቡበት መማሪያ መጽሐፉን መሠረት በማድረግ ነው። ይህ የሚያሳየው ደግሞ የተማሪውን የንግግር

ችሎታ ለማዳበር በቂ ጊዜ ወስደው የሚያነቃቁ፣ የሚያሳትፉና ለውይይት የሚጋብዙ ርእሰጉዳዮች በመምረጥ ረገድ መምህራን ያላቸው ተነሳሽነት ደካማ መሆኑን ነው። ከዚህ በፊት በተከታታይ ምልከታ በተተኳሪ መምህራን ላይ በተደረገው መረጃ ትንተና፣ ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ያዳብርባቸዋል ተብለው ከመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የወጡት መልመጃዎች የተማሪዎችን ፍላጎት ከግምት ውስጥ ያላስገቡ በመሆናቸው ተማሪዎች እንዲሰለቹ አድርጓቸዋል።

እንደ Ur (1996:50) አገላለጽ፣ ተማሪዎች በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ፣ በአካባቢያቸው ያላቸውን ባህል፣ ልምድና እውቀት መነሻ በማድረግ የተለያዩ ርእሰ ጉዳዮችን መርጠው የሐሳብ ልውውጥ ቢያደርጉ መልካም ውጤት ሊገኝ ይችላል። መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 4(44.44%) መምህራን "ሁል ጊዜ" ለክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርእሰጉዳዮች ተማሪዎች ከራሳቸው ገጠመኝ ተነስተው እንዲመርጡና እንዲለማመዱ እንደሚያደርጉ ሲመልሱ፣ 3(33.33%) መምህራን ደግሞ 'በአብዛኛው' እንደሚተገበሩት ምላሽ ሰጥቷል። 2(22.22%) መምህራን ግን ይህንን ተግባር 'አንዳንድ ጊዜ " እንደሚያከናውኑት ገልጸዋል። ይህንን ሁኔታ በተተኳሪ መምህራን በተደረገው ተከታታይ ምልከታ መረጃ ጋር በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰል ነው። ምክንያቱም ለጥናቱ ከተመረጡ መምህራን ሁለት መምህራን በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በራሳቸው ገጠመኝ ዙሪያና ከመጽሐፉ ውጭ በተዘጋጁ ጥያቄው እንዲናገሩ የተደረገበት ሁኔታ ነበር።

በሌላም በኩል መምህራን ወደ ዋና የክፍል ውስጥ የንግግር ተግባር ከመግባታቸው በፊት የማነቃቃት ሥራ ማከናወናቸውና አለማከናወናቸው ተጠይቀው ሲመልሱ፣ 3(33.33%) መምህራን "ሁል ጊዜ" እናከናውናለን ሲሉ 5(55.55%)ቱ "አብዛኛው ጊዜ" 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" በተግባር ላይ እንደሚያውሉት ገልጸዋል። ነገር ግን የምልከታው መረጃ ጋር ሲነጻጸር ሁለት መምህራን ብቻ በመጠኑ እንደሚያከናውኑት ለመረዳት ተችሏል። ሌሎች መምህራን ግን ወደ ዋናው ስራ እንዲገቡ ምንም ዓይነት የማነቃቂያ ሥራ አለመስራታቸው ነው።

አብዛኛዎቹ መምህራን እንደሚገልጹት፣ በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተማሪዎችን በማነቃቃት የተለያዩ ሞዴል ተግባራትን በመስጠት አጋዥ መረጃ

መሣሪያዎችን ተጠቅሞ የማስመሰልና የመደጋገም ተግባራትን እንዲያከናውኑ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በሠንጠረዡ ላይ እንደሚታየው በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ 3(33.33%) መምህራን "ሁል ጊዜ" ፣ 4(44.44%)ቱ መምህራን "አብዛኛው ጊዜ" 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" የቅድመ ንግግር ትምህርት እንደሚያከናውኑ ሲገልጹ፣ 1(11.11%) መምህር ደግሞ "ጨርሶ" ተግባሩን እንደማይፈጽመው አመልክቷል።

በተጨማሪም የንግግር ተግባሩ ከመስማመዳቸው በፊት አጋዥ መረጃ መሣሪያዎችን፣ ሞዴል ተግባራትን በመጠቀምና በግልጽና በማይረሳ መልኩ የማስመሰልና የመደጋገም ስራዎች እንደሚያከናውኑ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን አብዛኛዎቹ ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ገልጿል። ነገር ግን በተተኳሪ መምህራን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን እንዲህ ዓይነቱ ሥራ በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ሲመረጽም እንዳልሞከሩ መረጃው ያሳያል።

ሠንጠረዥ 17፦ ተማሪዎች የንግግር ተግባራትን እንዲለማመዱ የመምህሩን ሚና የሚያመላክት መገለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 11 | በራሳቸው የሰዋስው ዕውቀት ተጠቅመው ሐሳባቸውን የሚገልጹበትን መንገድ አመቻቻለሁ። | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 2 | 22.22 | - | - |
| 12 | አብዛኛውን ጊዜ ለመናገር የሚያደፋፍሩና ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሚያዳግታቸውን ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን አመቻቻለሁ። | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 1 | 11.11 | 1 | 11.11 |
| 13 | ተማሪዎች የንግግርን ትምህርት ሲማሩ በአፈ-ተክነት (Fluency) ላይ እንዲያተኩሩ አደርጋለሁ። | - | - | 5 | 55.55 | 2 | 22.22 | 2 | 22.22 |
| 14 | የንግግር ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተምራለሁ። | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 2 | 22.22 | - | - |
| 15 | በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ እጋብዛለሁ። | 3 | 33.33 | 4 | 44.44 | 1 | 11.11 | 1 | 11.11 |
| 16 | የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚረዱ ነገሮችን ሥዕል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ካርታ፣ ሠንጠረዥ፣ ወዘተ. በመስጠት እንዲናገሩ አበረታታለሁ። | - | - | 1 | 11.11 | 8 | 88.88 | - | - |

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ በመማር-ማስተማር ሂደት የመምህሩ ሚና ተማሪዎች በራሳቸው የቃላትና የሰዋስው ዕውቀት ተጠቅመው ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ 3(33.33%) መምህራን "ሁልጊዜ" 4(44.44%) "አብዛኛው ጊዜ" 2(22.22%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" ሁኔታውን እንደሚያመቻቹ መልስ ሰጥቷል። ተማሪዎቹ በቋንቋው

ተጠቅመው ያለምንም ጫልቃ ገብነት ሐሳባቸውን በነጻ መግለጽ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት የሆኖረትና የፍርሀት ስሜታቸው እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ በራሳቸው እንዲተማመኑ መንገድ እንደሚከፍት Harmer (1991:124) ይገልጻሉ።

በሠንጠረዡ እንደሚታየው፣ የጽሑፍ መጠይቁ ከሞሉት መምህራን መካከል 3(33.33%) "ሁል ጊዜ" 4(44.44%) "አብዛኛውን ጊዜ" 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" ለመናገር የማይደፍሩና ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሚቸገሩ ተማሪዎች በነጻ እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶች እንደሚያመቻቹ ሲገልጹ፣ 1(11.11%) መምህር "ጨርሶ" እንደማይተገበረው ለመረዳት ተችሏል።

አብዛኞቹ ምሁራን የሚስማሙበት በክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማር ሂደት ብዙ ተማሪዎች በሚኖሩበት ክፍል ውስጥ በግል ከሚደረገው የመማር-ማስተማር በጥንቃቄ የሚደረግ የቡድን ሥራ በበለጠ መልኩ በክፍል ውስጥ ለመናገር የማይደፍሩትን የሚያበረታታ፣ ሐሳባቸውን ለመግለጽ ቃላት የሚያጥራቸውን እንዲናገሩ የሚያነሳሳና አብዛኛውንም ተማሪ በእኩል ሊያሳትፍ የሚችል መሆኑን ተመራጭ ነው።

እንደ Harmer (1996:124) ገለጻ፣ በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ተማሪዎች ለመናገር በሚሞክሩበት ጊዜ ስሕተት እፈጽማለሁ ብለው እንዳይሸማቀቁ ከትክክለኛነት(accuracy) ይልቅ በአፈ-ተክነት (fluency) ላይ እንዲያተኩሩ እና በራሳቸው እንዲተማመኑ መምህሩ ከፍተኛ እገዛ ማድረግ እንዳለበት ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም መምህራን ተጠይቀው 5(55.55%) መምህራን "በአብዛኛው" በአፈ-ተክነት (fluency) ላይ ትኩረት ሰጥተው እንደሚያስተምሩ ሲመልሱ፣ 2(22.22%) "አንዳንድ ጊዜ" የተቀሩት 2(22.22%) ደግሞ "ጨርሶ" ትኩረት እንደማይሰጡት ለመረዳት ተችሏል።

እንደ አለም (1995:25) ገለጻ፣ ክሂሉችን አቀናጅቶ ማስተማር ተፈጥሮአዊውን የቋንቋ አጠቃቀም እንደሚያሳውቅ ሁሉንም ተማሪዎች እንደሚያሳትፍ እና ከአንድ ክሂል በላይ የመማር እድል እንደሚፈጥር ይገልጻሉ። ይህንን በተመለከተ መምህራን ምን ያህል ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ተጠይቀው፣ 3(33.33%) መምህራን "ሁልጊዜ" 4(44.44%)

"አብዛኛውን ጊዜ" 2(22.22%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

በሌላ በኩል ከክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት በተጨማሪ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ሰዎችን ጠይቀው ወይም ምልከታ አድርገው እና የተለያዩ ጽሑፎችን አንብበው በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ ማድረጋቸውን ተጠይቀው 2(22.22%) "ሁል ጊዜ"፣ 5(55.55%) "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 2(22.22%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያከናውኑት ለማወቅ ተችሏል።

በሠንጠረዥ 17 እንደሚታየው፣ ተማሪዎች በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ ላይ ንግግር በማድረግ የንግግር ክሂላቸውን ለማዳበር በማድረጉ በኩል መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ 3(33.33%) "ሁል ጊዜ"፣ 4(44.44%) "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚጠቀሙበት ሲገልጹ፣ 1(11.11%) ግን 'ጨርሶ' በክፍል ውስጥ በንግግር ተግባር ላይ እንደማይተገብረው ለመረዳት ተችሏል።

ከዚህ በተጨማሪ የተማሪዎችን የንግግር ክሂሎት ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ሥዕል፣ ትርጃትርጃ፣ ካርታ፣ ሠንጠረዥ፣ ወዘተ. ተጠቅሞ የንግግር ክሂልን ማስተማር ከፍተኛ ውጤት እንዳለው እየታወቀ 1(11.11%) መምህር "አብዛኛውን ጊዜ" 8(88.88%) መምህራን "አልፎ አልፎ" እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል። ሆኖም ግን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ ይህ ተግባር አንድም መምህር ተግባራዊ ሲያደርገው አልታየም።

ሠንጠረዥ 18፡- ተማሪዎች ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ የመምህሩ ሚና የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ዝርዝር ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 4 | | 3 | | 2 | | 1 | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 17 | በንግግር ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት ስሕተታቸውን እንዲያርሙ አደርጋለሁ። | 3 | 33.33 | 5 | 55.55 | 1 | 11.11 | - | - |
| 18 | ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕሠ ጉዳይ ላይ ንግግር ካደረጉ በኋላ በነጻነት አስተያየት እንዲሰጡ አበረታታለሁ። | 6 | 66.66 | 1 | 11.11 | 1 | 11.11 | 1 | 11.11 |
| 19 | ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ሐሳብ ለሐሳብ እንዲለዋወጡ አደርጋለሁ። | - | - | 2 | 22.22 | 7 | 77.77 | - | - |
| 20 | ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ አበረታታለሁ። | 4 | 44.44 | 2 | 22.22 | 2 | 22.22 | 1 | 11.11 |

ከላይ በቀረበው የሠንጠረዡ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ 3(33.33%) መምህራን "ሁል ጊዜ" በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት ስህተታቸውን እንደሚያርሙ ሲገልጹ፣ 5(55.55%) "በአብዛኛውን ጊዜ" 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ጠቁሟል። አብዛኛዎቹ መምህራን ተማሪዎች ስህተታቸውን እርስ በራሳቸውን እንዲተራረሙ ከማድረጋቸው ይልቅ በሌምምዱ ጣልቃ በመግባት ተማሪዎች በነጻነት እንዳይናገሩ ያደርጉ እንደነበር ለማስተዋል ተችሏል።

በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የሚቀርበውን የልምምድ ተግባር መሠረት በማድረግ ተማሪዎች በራሳቸው የቋንቋ ዕውቀት በመጠቀም ሐሳባቸውን አፍልቀው የሚገልጹበትን መንገድ መምህሩ ማመቻቸት እንዳለበት አብዛኞቹ ምሁራን የሚስማሙበት ጉዳይ ነው። ከዚህ አንጻር መምህራን ተጠይቀው 6(66.66%) "ሁል ጊዜ" 1(11.11%) "አብዛኛውን ጊዜ" 1(11.11%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ሲገልጹ፣ 1(11.11%) ግን "ጭራሽ" ይህንን ተግባራዊ እንደማያደርግ ገልጸዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ Byrne (1986:75) ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል የንግግር ተግባር ላይ ተመስርተው፣ውይይቶችንና ክርክሮችን በማዘጋጀት ሐሳባቸውን የሚገልጹበትን መንገድ መምህራን ማመቻቸት እንዳለባቸው ይገልጻሉ። ሠንጠረዥ የሚያሳየው ግን በአብዛኛው መምህራን ለዚህ ጉዳይ ትኩረት አለመስጠታቸውን ነው። 2(22.22%) መምህራን "በአብዛኛው" 7(77.77%) ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚተገብሩት ተመልክቷል። ይሁን እንጂ የተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ እንደሚያመለክተው ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን ተግባራዊ ሲያደርጉት አልታየም።

### 4.1.3.2. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቆች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

ለተማሪዎች የተዘጋጀው የጽሑፍ መጠይቅ ሁለት ክፍል ሲኖሩት፣ በክፍል አንድ የተማሪዎችን ዳራዊ መረጃ ለማወቅ የተዘጋጁ ጥያቄዎች ሲሆኑ፣ በክፍል ሁለት ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ያሉ ክንውኖች ምን እንደሚመስሉ የያዘ ነው። መጠይቁን እንዲሞሉ የተመረጡ ተማሪዎች ከአንድ ትምህርት ቤት 20 ሲሆኑ በድምሩ 60 ናቸው። ሁሉም ተማሪዎች መጠይቁን ሞልተው መልሰዋል። የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው በሠንጠረዥ መልክ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 19፡- የተማሪዎችን ናሙና አመራረጥ የሚያመላክት መግለጫ

| ዕድሜ | የትምህርት ቤት ስም | | | | | | | | | አጠቃላይ ድምር | የአፍ መፍቻ ቋንቋ | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሎጊያ 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | | | ሜግሊኪቦ 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | | | ፕላንቴሽን 1ኛ ደረጃ 2ኛ እርከን ትምህርት ቤት | | | | አፋርኛ | አማርኛ | ትግርኛ | ሌሎች |
| | ጾታ | | | ጾታ | | | ጾታ | | | | | | | |
| | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | | | | | |
| 12 | - | 1 | 1 | - | - | - | - | 1 | 1 | 2 | 2 | - | - | - |
| 13 | 2 | - | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | - | 1 | 6 | 4 | 1 | 1 | - |
| 14 | 1 | 1 | 2 | - | - | - | 1 | - | 1 | 3 | 2 | - | 1 | - |
| 15 | 2 | 3 | 5 | 1 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 13 | 11 | 2 | - | - |
| 16 | 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 5 | 11 | 9 | 2 | - | - |
| 17 | 1 | 1 | 2 | - | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 6 | 5 | 1 | - | - |
| 18 | 2 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 1 | 1 | 2 | 8 | 7 | - | 1 | - |
| 19 | 1 | - | 1 | 2 | 1 | 3 | - | - | - | 4 | 2 | 2 | - | - |
| 20 | - | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 3 | 7 | 7 | - | - | - |
| ድምር | 10 | 11 | 21 | 9 | 10 | 19 | 10 | 10 | 20 | 60 | 49 | 8 | 3 | - |

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ የክፍል አንድ መጠይቅ የተማሪዎችን ጾታና ዕድሜ የሚመለከት ነው። ለመጠይቆቹ የተሟላ መልስ ሁሉም ተማሪዎች ሰጥቷል። በመረጃው መሠረት 31(51.66%) ወንዶች 29(48.33%) ሴቶች ናቸው። የተማሪዎቹ አማካይ ዕድሜ 15 ዓመት ነው። ቀጥሎ ክፍል ሁለት በሠንጠረዥ መልክ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 20፦ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል የመማር ፍላጎት የሚያሳይ መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በአማረኛ ቋንቋ በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ወቅት የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ፣ | 33 | 55 | 16 | 26.6 | 7 | 11.66 | 4 | 6.66 |

የተማሪዎች በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የመማር ፍላጎት 47 (81%) አዎንታዊ ሲሆን አሉታዊ ምላሽ የሰጡ 4(6.66%) ናቸው። ፍላጎታቸውን መወሰን ያልቻሉ ደግሞ 5(8.33%) ሆኗል። ፍላጎት የለኝም ያሉት 4(6.66%) ተማሪዎች ፍላጎት ያጡበት ምክንያት እንደሚከተለው በሠንጠረዥ መልክ ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ ፦20.1

2. በተራ ቁጥር "1" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ ፍላጎት የለኝም የሚል ከሆነ ምክንያቱን ምንድነው?

| አማራጮች | የመላሶች ብዛት | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ. መምህሩ በአግባቡ ስለማያስተምሩኝ ነው። | 3 | 75 |
| ለ. ንግግርን በመማሬ የማገኘው ጥቅም የለም ብየስለማስብ ነው። | - | - |
| ሐ. ስለምፈራና ስለማፍር ነው። | 1 | 25 |
| መ. ተናጋሪ (Orater) የመሆን ፍላጎት ስለሌለኝ ነው። | - | - |

መምህራን በአግባቡ ስለማያስተምሯቸው መሆኑን 3(75%)፣ 1(25%) ደግሞ ተናጋሪ የመሆን ፍላጎት ስለሌለው መሆኑን አመልክቷል።

ሠንጠረዥ 21፦

3. በንግግር ክሂል ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍል ሁኔታ ምን ይመስላል?

| አማራጮች | የመላሶች ብዛት | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ. በጣም ሥርዓት ያለው ነው። | 45 | 75 |
| ለ. በመጠኑ ስርአት ያለው ነው። | 10 | 16.66 |
| ሐ. በጣም ቀልድ የበዛበት኏ና ረብሻ ያለው ነው። | 5 | 8.33 |
| መ. ሌላ ካለ | - | - |

በሠንጠረዥ እንደተመለከተው በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍሉ ሁኔታ በሚመለከት መጠይቁን ከመለሱት መካከል 45(75%) ክፍሉ በጣም ስርአት ያለው መሆኑን ሲገልጹ፣ 10(16.66%) ደግሞ በመጠኑ ስርአት ያለው መሆኑን አስቀምጧል። በሌላ በኩል 5(8.33%) የሚሆኑት ተማሪዎች በጣም ቀልድ የበዛበትና ረብሻ መሆኑን ጠቁሟል። የምልከታው መረጃ ይህን ያጠናክራል።

በመማር-ማስተማር ሂደት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የተማሪዎችንና የመምህራንን መስተጋብር በሚመለከት ከተማሪዎቹ የተገኙ መረጃዎች ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 22፦ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት የመምህሩና የተማሪዎች መስተጋብር (Interaction) የሚያመለክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 4 | መምህሩ የንግግር ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ያነቃቃል? | - | - | - | - | 51 | 85 | 9 | 15 |
| 5 | አንተ/ቺ በክፍል ውስጥ ምን ያህል ጊዜ በንግግር ወቅት ትሳተፋለህ/ሽ | 20 | 33.33 | 22 | 36.66 | 16 | 26.66 | 2 | 3.33 |
| 6 | መምህሩ የንግግሩን ትምህርት በሚያከናውንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እኩል እድል ይሰጣል? | 9 | 15 | 15 | 25 | 12 | 20 | 24 | 40 |
| 7 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲናገሩ የማበረታታቱ ሁኔታ እንዴት ነው? | 31 | 51.66 | 14 | 23.33 | 9 | 15 | 6 | 10 |

ከላይ በሠንጠረዥ እንደተገለጸው፣ የሚማሩበትን መማሪያ መጽሐፍ የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር ስላለው ብቃት ተጠይቀው 45(75%) ተማሪዎች "በጣም ይጠቅማል" በሚል ሲያስረዱ 10(16.66%)፣ "በመጠኑ ይጠቅማል" 5(8.33%) ደግሞ "ምንም አይጠቅምም" የሚል ምላሽ ሰጥቷል።

በመግባባት ሂደት ተማሪዎችን በማንቃት በእለቱ የቀረበው የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት እንዲያከናውኑ ፍላጎታቸው ማነሳሳት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህን ጉዳይ በሚመለከት የቀረበው መጠይቅ 51(85%) የሚሆኑት ተማሪዎች በመግባባት ሂደት ክሂሉን በተግባራዊ ልምምድ ለማዳበር ትምህርቱ ከመጀመሩ በፊት መምህራን "አንዳንድ ጊዜ" ተማሪዎችን እንደሚያነቃቁ ሲገልጹ፣ 9(15%) የሚሆኑት ደግሞ "በፍጹም" ይህንን ተግባር እንደማይፈጽሙት አመልክቷል።

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት ተማሪዎች መካከል 20(33.33%) በተደጋጋሚ በክፍል ውስጥ በንግግር ትምህርት ወቅት የሚሳተፉ መሆኑን ሲያመለክቱ፣ 22(36.66%) ደግሞ አንዳንድ ጊዜ ተሳትፎ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል። በክፍል ውስጥ በንግግር ተግባራት ወቅት 16(26.66%) መምህሩ ሲጠይቃቸው ብቻ እንደሚሳተፉ ሲገልጹ፣ 2(3.33%) ደግሞ ምንም እንደማይሳተፉ መልስ ሰጪዎች ጠቁመዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ በመግባባት ሂደት መምህሩ በክፍል ውስጥ ትግበራ ለሁሉም ተማሪዎች እኩል እድል የመስጠቱ ሁኔታ ተጠይቀው ሲመልሱ፣ 9(15%) "ሁል ጊዜ ይሰጣል"፣ 15(25%) "አብዛኛውን ጊዜ ይሰጣል"፣ 12(20%) "አንዳንድ ጊዜ ይሰጣል"፣ 24(40%) ደግሞ "ምንም አይሰጥም" ብለዋል። ይህም በተደረገው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ጋር ሲነጻጸር ተቀራራቢነት አለው። ምክንያቱም በምልከታው ወቅት ለተማሪዎች በመጠነኛ ሁኔታ አብዛኛውን ተማሪ ለማሳተፍ የሞከረው አንድ መምህር ብቻ ነው።

ከዚህ ጎን ለጎን በክፍል ውስጥ ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ የመምህሩ አስተዋጽኦ 31(51.66%) "በጣም ጥሩ" 14(23.33%) ደግሞ "መካከለኛ" መሆኑን ምላሽ ሲሰጡ 9(15%) "ዝቅተኛ" 6(10%) ደግሞ "በጣም ዝቅተኛ" እንደሆነ አረጋግጠዋል። ይህን ጉዳይ ከተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ተቀራራቢነት የለውም። ምክንያቱም ከአንድ መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን እነዚህን ያላጠሙ ተማሪዎችን እንዲናገሩ አላበረታቱም።

ሠንጠረዥ 23፦ የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል የመማር-ማስተማር ትግበራ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 8 | በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የንግግር ተግባር መምህሩ ግልፅ እና የሚያደርስ መመሪያ ይሰጣል? | 24 | 40 | 26 | 43.33 | 10 | 16.66 | - | - |
| 9 | ቀናውን የንግግር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊት ሞዴል (ምሳሌ የሚሆኑ) ተግባራትን ያቀርባሉ? | 5 | 8.33 | 11 | 18.33 | 20 | 33.33 | 24 | 40 |
| 10 | የንግግር ተግባር ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መለማመድ | 45 | 75 | 15 | 25 | - | - | - | - |
| 11 | መምህሩ በጥንድ ወይም በቡድን እንድትወያዩ እና የንግግር ችሎታችሁን እንድታዳብሩ የሚያደርገው ጥረት እንዴት ነው? | 4 | 6.66 | 18 | 30 | 15 | 25 | 23 | 38.33 |
| 12 | መምህሩ በክፍል ውስጥ የንግግሩን ተግባር በተገቢው መንገድ እዲለማመድ የሚያደርግ ሁኔታ እንዴት ነው? | 17 | 28.33 | 10 | 16.66 | 20 | 33.33 | 13 | 21.66 |
| 13 | የተለማመዳችሁትን የንግግር ተግባር በጥሩ ሐሳባችሁን እንድትገልጹ ያደርጋል? | 30 | 50 | 14 | 23.33 | 11 | 18.33 | 5 | 8.33 |

በሠንጠረዥ እንደተገለጸው፣ በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የንግግር ተግባር መምህሩ ግልጽና የማያሻማ መመሪያ የመስጠቱ ሁኔታ ተጠይቀው ሲመልሱ 24(40%) "በተገቢው መንገድ ይሰጣል"፣ 26(43.33%) "በመጠኑ ይሰጣል"፣ 10(16.66%) ደግሞ "በፍጹም አይሰጥም" በማለት ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ በንግግር ትምህርት አቀራረብ ደረጃ መምህራን የተለያዩ ሞዴል ተግባራትን በክፍል ውስጥ ስለማቅረባቸው ተጠይቀው 5(8.33%) "ሁል ጊዜ ያቀርባሉ"፣ 11(18.33%) "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 20(33.33%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ "አንዳንድ ጊዜ" እንደሚያቀርቡ ሲያመለክቱ፣ 24(40%) ግን "በፍጹም" እንደማያቀርቡ ገልጸዋል። ይህ ቀደም ሲል በተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ከሰፈረው ጋር ተመሳሳይነት አለው። ምክንያቱም በንግግር ትምህርት የተለያዩ ሞዴል ተግባራት በመጠነኛ ሁኔታ የተጠቀሙ ሁለት መምህራን ብቻ እንደሆኑ መረጃው ያመለክታል።

በመግባቢያ ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን ለማዳበር የንግግር ትግበራ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መለማመድ ጠቀሜታ እንዳለው 45(75%) የሚሆኑ ተማሪዎች ምላሽ ሲሰጡ 15(25%) ደግሞ በመጠኑ እንደሚጠቅም ገልጸዋል።

ይህን ትግበራ በክፍል ውስጥ በጥንድ ወይም በቡድን ተግባራዊ እንዲያደርጉት የመምህሩ ጥረት ምን ያህል እንደሆነ ተጠይቀው 4(16%) "ከፍተኛ" ፣ 18(30%) "መካከለኛ"፣ 15(25%) "ዝቅተኛ"፣ 23(38.33%) ደግሞ "ምንም ጥረት አያደርግም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። ነገር ግን በተተኳሪ መምህራን በተደረገው ተከታታይ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ የሚያሳየው ከአንድ መምህር በስተቀር ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እርስ በርስ ሐሳብ ሊለዋወጡ እንዲለዋወጡ ያበረታታ መምህር እንደሌለ ነው። አንድ መምህር "ልብስ ሰፊና ተማሪ" የሚለው ክርክር ሲያሰራ ሌሎች ይህን አይነቱ ትግበራ ለማከናወን ጥረት አላደረጉም።

በሠንጠረዡ እንደሚታየው መምህሩ በክፍል ውስጥ የንግግሩ ተግባር በተገቢው መንገድ የሚለማመዱበትን ሁኔታ በማመቻቸት ደረጃ 17(28.33%) "በጣም ጥሩ"፣ 10(16.66%) ደግሞ "መካከለኛ" በሆነ ደረጃ ልምምድ እንዲያደርጉ መምህሩ እንደሚያመቻቹ ሲገልጹ፣ 20(33.33%) "ዝቅተኛ" ቀሪዎቹ 13(21.66%) የሚሆኑት

ደግሞ " እንደማያበረታቱ" ምላሽ ሰጥተዋል። ይህም ከምልከታ ውጤት ጋር ሲነጻጸር በአብዛኛው የሚያሳየው ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎች በቂ የሆነ ልምምድ እዲያደርጉ ምቹ ሁኔታን አለመፍጠራቸው ተመሳሳይነት ያለው ነው።

ተማሪዎች የንግግር ትምህርት በተለያየ መንገድ የቀረቡላቸውን ተግባራት በጥንድና በቡድን ከተለማመዱ በኋላ የራሳቸውን የቋንቋ ዕውቀት ተጠቅመውና ሐሳብ አፍልቀው በጻኑነት የሚገልጹበትን መንገድ መምህሩ ስለማመቻቸቱ ሁኔታ ተጠይቀው 30(50%) "ሁል ጊዜ"፣ 14(23.33%) "አብዛኛውን ጊዜ"፣ 11(18.33%) የሚሆኑ ደግሞ "አልፎ አልፎ" እንደሚያደርጉ ምላሽ ሰጥተዋል። በሌላም በኩል 5(8.33%) የሚሆኑ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ሐሳባቸውን በጻኑነት እንዲገልጹ እንደማያደርጉ ገልጸዋል። የመጠይቁ መረጃ አብዛኛውን መምህራን ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ቢገልጹም የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ምልከታ የሚያሳየው ግን ከአንዱ መምህር በስተቀር ሌሎች መምህራን ተማሪዎችን ካለማመዱ በኋላ ከመጽሐፍ የወጡ መልመጃዎች እንዲሠሩ በማድረግ የንግግር ትምህርቱን ይዘሉታል።

ሠንጠረዥ 24፡- በክፍል ውስጥ የመምህሩ ትምህርት መረጃ መሣሪያዎች አጠቃቀም የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 14 | መምህሩ የተለያዩ ሥዕሎችን፣ ፎቶ ግራፎች እና ቅርጹ ቅርጾችን በመጣሪያ ክፍል በግምባት ተማሪዎችን እንዲናገሩ ያደርጋል? | 9 | 15 | 15 | 25 | 16 | 26.66 | 20 | 33.33 |
| 15 | ንግግርን ለማስተማር የሥነጹሑፍ ስራዎችን/ልቦለድ፣ ስንቃል፣ ግጥም ወዘተ. የመጠቀሙ ሁኔታ እንዴት ነው? | 3 | 5 | 5 | 8.33 | 25 | 41.66 | 27 | 45 |

ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው፣ በመማር-ማስተማር ሂደት ላይ መምህሩን የተለያዩ ቁሳዊ የትምህርት መረጃዎችን፣ ፎቶግራፎችን፣ ሥዕልን፣ ወዘተ.፣ ወደ ክፍል ውስጥ በማምጣት ተማሪዎችን እንዲናገሩ የማድረጋቸውን ሁኔታ ተጠይቀው 9 (15%) "በጣም ጥሩ"፣ 15(25%) "መካከለኛ"፣ 16(26.66%) "ዝቅተኛ" 20(33.33%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ "ምንም ጥረት አያደርጉም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ እንደ Harmer (1991:95) አገላለጽ፣ በመማር-ማስተማር ሂደት የተለያዩ ቁሳዊ የትምህርት መረጃዎችን፣ ፎቶግራፎችን፣ ሥዕሎችን፣ ወዘተ. በመስጠት ተማሪዎች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ተመልክተው ሐሳባቸውን እንዲገልጹ ማበረታታት እንደሚቻል ነው፡፡ ነገር ግን በተተኳሪ መምህራን ፣ ተማሪዎችን እንዲሁም የምልከታው መረጃ በግልጽ የሚያመለክቱት ተግባሩ በሥራ ላይ አለመዋሉን ነው፡፡

የሥነ-ጽሑፍ ሥራ ሳቢነት ያለው በመሆኑ የተማሪዎችን ትኩረት ለመሰብሰብ በእጅጉ የሚያግዝ በመሆኑ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በራሳቸው ቋንቋ እንዲገልጹ እንደሚያስችላቸው Berhanu (1994:217) ይገልጻሉ። ይህን በተመለከተ መምህሩ የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎችን መሠረት በማድረግ የንግግር ክሂልን ስለማስተማሩ ተማሪዎች ሲመልሱ 3(5%) "በጣም ጥሩ ነው" ሲሉ፣ 5(8.33%) የሚሆኑት ደግሞ "መካከለኛ ደረጃ " እንደሚጠቀም አመልክተዋል። ይህን የሚያሳየው መምህራን የስነ-ጽሑፍ ስራዎችን በክፍል ውስጥ በማምጣት ተግባራዊ እንደማያደርጉት ነው።

ሠንጠረዥ 25፦ በክፍል ውስጥ የመምህሩ ምጋቤ-ምላስ አሰጣጥ የሚያመላክት መግለጫ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | | ለ | | ሐ | | መ | |
| | | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ |
| 16 | በምትናገሩበት ጊዜ ብትሳሳቱ መምህሩ ወዲያውኑ እንድታስተካክሉ ያደርጋል? | 43 | 71.66 | 12 | 20 | 3 | 5 | 2 | 3.33 |
| 17 | መምህሩ የተማሪዎችን የንግግር ስሕተት | 16 | 2 | 35 | 58.33 | 7 | 11.66 | 2 | 3.33 |
| 18 | በዚህ የክፍል ደረጃ የንግግር ችሎታዬ ተሻሽሏል ብለህ/ሽ ታምናለህ/ናለሽ? | 12 | 20 | 25 | 41.66 | 13 | 21.66 | 10 | 16.66 |

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ የተማሪዎችን ስሕተት ወዲያውኑ በተደጋጋሚ የማስተካከል ተግባር እንደሚፈጽሙ 43(71.66%) የሚሆኑ ተማሪዎች ሲገልጹ፣ ስሕተታቸውም የማረሚያ መንገዱም በቀጥታ እንደሆነ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት ውስጥ 35(58.33%) የሚሆኑት አመልክተዋል።

በሌላም በኩል 3(5%) መምህሩ ወዲያውኑ የተማሪዎችን ስሕተት "አንዳንድ ጊዜ እንዲያስተካክሉ" እንደሚያደርጉ ሲገልጹ፣ 2(3.33%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ ስሕተቶችን "አያስተካክልም" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የንግግር ትምህርት የንግግር ችሎታቸውን 12(20%) "በጣም ተሻሽለዋል"፣ 25(41.66%) "በመጠኑ ተሻሽሏል"፣ 13(21.66%) የሚሆኑ ተማሪዎች ደግሞ "ምንም አልተሻሻለም" ሲሉ 10(16.66%) ግን "በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል" የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

ሠንጠረዥ 26፡-

19፡- ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የመምህሩ ድርሻ ምንድን ነው?

| አማራጮች | የመላሾች ብዛት | |
|---|---|---|
| | በቁጥር | በመቶኛ |
| ሀ ፊት ለፊት ቆመው ስለንግግር እና እንዴት ንግግር ማድረግ እንደሚቻል ገለጻ መስጠት ነው። | 30 | 50 |
| ለ ስለሚነገረው የንግግር ተግባር አስረድተው ሞዴል ንግግር በምሳሌነት መስጠት ነው። | 13 | 21.66 |
| ሐ የንግግር ተግባሩን ሰጥተው መቀመጥ ነው። | 11 | 18.33 |
| መ የንግግር ተግባሩን ከሰጡ በኋላ በቡድን እርስ በርሳችን እየተወያየን | 6 | 10 |

በሠንጠረዡ እንደተመለከተው፣ ተማሪዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ የመምህሩ ድርሻ ምን እንደሆነ ተጠይቀው 30(50%) መምህሩ ፊት ለፊት ቆመው ስለንግግር እና ንግግር እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ገለጻ እንደሚያደርጉ፣ 13(21.66%) ስለሚከናወነው የንግግር ተግባር አስረድተው ምሳሌ እንደሚሰጡ ሲጠቁሙ 6(10%) ደግሞ የንግግር ተግባሩን ከሰጡ በኋላ በቡድን እርስ በርሳችን እየተወያየን እንድንሰራ እየተዘዋወሩ ያበረታቱናል ብለዋል። በተጨማሪም 11(18.33%) መምህሩ የንግግር ተግባሩን ሰጥተው እንደሚቀመጡ ምላሽ ሰጥተዋል።

## 4.2. የመረጃዎቹ ትንተና ማብራሪያ

### 4.2.1. ንግግርን ለማስተማር የቀረቡ ይዘቶችና ክንውኖች

የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚቀርቡት ይዘቶችና ክንውኖች በአብዛኛው ማስተማሪያ መግሪያዎችን መሠረት ያደረጉ ናቸው። በማስተማሪያ መግሪያዎቹ፣ በመርሐ-ትምህርቱ፣ በመምሪያ መጽሐፉና በማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከጽሁፈት ክሂል ቀጥሎ ለንግግር ክሂል ትኩረት ተሰጥቶት እናገኛለን። በክፍል ውስጥ የሚቀርቡ ይዘቶችና ክንውኖች ብቻቸውን በንግግር ሐሳብን የመግለጽ ችሎታንና ተግባቦት የመፍጠር ብቃትን ወደ ማዳበር የማያደርሱ መሆናቸውን ጥናቱ በሰበሰባቸው መረጃዎች አማካይነት ደርሶበታል።

ከዚህ አንጻር የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋን መጽሐፍ ስንመለከት በመርሐ-ትምህርቱ የተካተቱት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው በውስጡ እንደማይገኙ ተስተውሏል (በገጽ 36 ሠንጠረዥ 6ን ይመልከቱ)። በሁለቱ መሣሪያዎች መካከል በተወሰነ ደረጃ አለመጣጣም፣ የትኩረት ልዩነትና በአንደኛው ውስጥ የሌለው በሌላው ውስጥ በመገኘት መካተቱ ምክንያት በመምህራን የክፍል ውስጥ የማስተማር ሥነ ዘዴ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሯል። ከዚህ በተጨማሪ በመማሪያ መጽሐፉ የንግግር ክሂል ያዳብራሉ ተብለው የቀረቡ መልመጃዎች የአንብቦ መረዳትን ችሎታ ከፍ ለማድረግ የሚያግዙ ሆነው ተገኝተዋል። የሚቀርቡት መልመጃዎች እንደመነሻና ለንግግር ክሂል ትምህርት ግብአቶች ለመለማመጃነት ሊያገለግሉ ቢችሉም በቋንቋው ተጠቅመው ሐሳብን የመግለጽና ተግባቦት የመፍጠር ብቃትን ሊያዳብሩ የሚችሉ እንዳልሆኑ መገንዘብ ተችሏል።

### 4.2.2. የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ

የቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማ ተማሪዎች በአራቱ የቋንቋ ክሂሎች በአግባቡ መጠቀም እንዲችሉ ማድረግ ነው። ከነዚህ ክሂሎች አንዱ ደግሞ ንግግር መሆኑ ቀደም ብሎ ተገልጿዋል። ይህም በክፍል ውስጥ የመማር-ማስተማር ሂደት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት ሊጓበር ይገባል። ስለዚህ በንግግር ክሂል ትምህርት የአቀራረቡን፣የልምምዱን እና የአፍልቶት ሂደቱን በተግባር ላይ ሊውሉ የሚያስችሉ ምንባቦችንም ሆነ መልመጃዎችን በበቂ ሁኔታ መመረጥና መደራጀት አለባቸው።

ከማስተማሪያ መማሪያዎች ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለይዘቶች አቀራረብና ለክንውኖች አሠራር በአብዛኛው ተራክቧዊ ተግባቦታዊ የሆነ የማስተማሪያ ዘዴ ቀርቧል። የተገኘው መረጃ የሚያሳየው ግን አብዛኛዎቹ መምህራን ንግግርን በክፍል ውስጥ ለማስተማር የሞከሩበት ለደረጃው የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፍ መሠረት በማድረግ ነው። ይዘቶችና ክንውኖች በክፍል ውስጥ በመምህራኑ የሚቀርቡበትና በተማሪዎች የሚሠሩበት ዘዴ ንግግርን በተግባር በመለማመድ መማር የሚያስችል፣ የተማሪውን የመማር ተነሳሽነት የሚያነቃቃና ክሂሉን ለማዳበር የሚረዳ ነው ለማለት አያስደፍርም። ይህን ተግባር ግልጽና ማራኪ በሆነ መንገድ ባለማቅረባቸው ተማሪዎች እንዲሰላቹ፣ የክፍሉ ጸጥታ እንዲደፈርስ፣ መፀተ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለዚህም መምህራን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡት ያሰቡትን የንግግር ትምህርት ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በአግባቡ በማዘጋጀት ተማሪዎች ወደ ክርክር ወይም ውይይት የሚያስገቡ፣ ገለጻ እንዲያደርጉና እንዲተረጉሙ የሚያበረታቱ መሆን አለባቸው።

የመማር-ማስተማሩ ሂደት የትምህርቱ አቀራረብ መምህሩ ወደ ዋናው ተግባር ከመግባቱ በፊት የተማሪዎች ትኩረት ለመሳብና ውስጣዊ ፍላጎታቸውን ለማነሳሳት የማነቃቃት ተግባር መፈጸም ይገባዋል። ይህን በማድረጉም በቋንቋው ተጠቅመው ሐሳባቸውን በንግግር እንዲገልጹ ከማበረታታቱም ባሻገር የመማር-ማስተማሩ ሂደትም ውጤታማ ይሆናል። የማነቃቃት ሥራ ትምህርት ለመጀመር ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የንግግር

ማስተማር ደረጃዎች እጅግ ጠቃሚ መሆኑን አብዛኞቹ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከክፍል ውስጥ ምልከታና ከተማሪዎች መጠይቅ በተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ለዚሁ ተግባር ብዙም ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን ነው፡፡

የንግግር ትምህርትን የመማር-ማስተማር ሂደት በሚመለከት ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ የመማር-ማስተማሩ ሂደት ገለጻዊና የመምህር-ተማሪ ተራክቦ የሰፈነበት፣ መምህሩ የበላይነት የሚመራውን በአብዛኛው ከመጽሐፍ ያገኘውን ዕውቀት የሚያስተላልፍበት መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው፡፡ ንግግርን በተግባር በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እንዲለማመዱ፣ በቀረበው ርእሰጉዳይ ላይ ቋንቋውን ተጠቅመው ሐሳባቸውን በነጻ እንዲያንሸራሽሩና ተግባቦታዊ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ረገድ ከአንድ መምህር በስተቀር የተሰጠው ትኩረት በጣም አናሳ መሆኑን ከተሰበሰቡት መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተለይም የተማሪዎች ቁጥር በበዛበት የመማሪያ ክፍል በጥንድ ወይም በቡድን የመማር-ማስተማሩ ስልት የመምህሩ ጊዜ በመቆጠብ መማርን ለማመቻቸትና ለመከታተል እንዲሁም የሚናገሩትን በማጣት ለሚፐኑና ለሚፈሩ ተማሪዎች በቡድን ሥራ መጠቀም ችግሮችን ለማስወገድ ካለው ጠቀሜታ አኳያ ከአንዱ መምህር በስተቀር ቡድን መስርተው እያንዳንዱ ተማሪ ሐሳብ ሊለዋወጥ እንዲለዋወጥ ያደረጉት ጥረት በጣም ደካማ መሆኑን ከክፍል ውስጥ ምልከታ፣ ከመምህራንና ተማሪዎች መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡

ተግባቦታዊ አቀራረብ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው በተለያዩ ማሕበራዊ ርእሰጉዳዮች ውስጥ ሐሳባቸውን በመግለጽ በቂ ልምምድ የሚደረግበት ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች መስተጋብር እንዲጨምር ፍንጭ ሰጪ ሐሳብና የተለያዩ ሥዕሎች፣ ፎቶግራፎች፣ ወዘተ. በተጨባጭ በክፍል ውስጥ በማምጣት ተነሳሽነታቸውንና ፍላጎታቸውን ባገናዘበ መንገድ ተማሪዎች እንዲናገሩና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ መምህራን ያደረጉት ጥረት ደካማ እንደሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ መምህራን አልፎ አልፎ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ንግግርን የሚለማመዱበት ክንውን የሚሰጡ ቢሆኑም ተማሪዎቹ በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን እርስ በራሳቸው ሐሳብ ሊለዋወጡ፣ ሌሎች የሚያስተላልፉትን ሐሳብ መረዳት እንዲችሉ፣

እንዲከራከሩ፣ እንዲወያዩ፣ ወዘተ. የማድረግ ሁኔታ ከአንድ መምህር በስተቀር በሌሎች ሲሠራበት አይታይም።

የምልከታው መረጃ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ችሎታቸውንና ተግባቦታዊ ብቃታቸውን ለማዳበር የሚያስችላቸውን በተግባር የሚለማመዱበትን ሁኔታ የተመቻቸላቸው አይመስልም፡፡ በክፍል ውስጥ የሚታየው በአብዛኛው ሲናገሩ ሳይሆን የመምህሩን ገለጻ ወይም የመልመጃ መልሶች ሲጽፉ ነው፡፡ በተጨማሪም በልምምዱ ወቅትም በተወሰኑ ተማሪዎች ላይ ብቻ በማተኮር፣ በንግግራቸው ወቅት ጣልቃ በመግባት፣ ወዘተ. የመማር-ማስተማሩ ሂደት በተገቢው መንገድ እንዳይከናወን እንቅፋት መፍጠራቸውን መረጃዎቹ ያሳያሉ፡፡ መምህራኑ ከውትታዊ ግኝቶች ጋር የሚተዋወቁበትን የሥልጠና ዕድል አለማግኘታቸውንና በመማር-ማስተማሩ ሂደት ተማሪው ሐሳቡን በንግግር መግለጽ የሚችልበትን፣ በጥንድ ወይም በቡድን ንግግርን በመናገር (በተግባር) የሚማሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ሚና በአብዛኛው እንዳልተጨወቱ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በተሰበሰቡት መረጃዎች መሠረት አብዛኛዎቹ መምህራን የሠለጠኑበትና ያገለገሉበትን ዘመን ረጅም ነው፤ በዚህ ጊዜ ውስጥ ከአዳዲስ የማስተማር ዘዴዎች ጋር ለመተዋወቅ የወሰዱት ሥልጠናም የለም፡፡ ይህ ሁኔታ በማስተማሪያ ሥነ-ዘዴው ምርጫና ትግበራ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድርባቸው እንደሚችል ይገመታል።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

በምዕራፍ አንድ እንደተገለጸው አጥኚው ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሳው መሠረታዊ ጉዳይ መንግሥታዊ በሆኑ አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች የሚገኙ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የማስተማር ዘዴ ምርጫና አተገባበር በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግና አለማድረጋቸውን ለመፈተሽ ነው፡፡ በዚህም መሠረት የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ደረጃዎች፣ የማስተማሪያ ስልቶች፣ በንግግር ክሂል ትምህርት አቀራረብ፣ የመምህሩ ሚና እና ግንዛቤ ምን እንደሚመስል ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ለመመርመርም የማስተማሪያ መሣሪያዎችን፣ የክፍል ውስጥ ምልከታን፣ በተተኳሪዎቹ መምህራንና ተማሪዎች በሚሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች መረጃዎችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ መረጃዎቹን በመተንተን ጥናቱ የሚከተሉትን ውጤቶች ወይም ግኝቶች አግኝቷል፤

## 5.1. ማጠቃለያ

የመማር-ማስተማሩ ሂደት በተማሪዎች ችሎታና ውጤት ላይ ካለው ተጽእኖ አኳያ በየወቅቱ ከሚፈጠሩ ትውረቶች፣ ግኝቶችና ሥነ-ዘዴዎች ጋር አብሮ ሊሄድ፣ ሊሻሻልና ሊለወጥ ይገባዋል፡፡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ከሚደረገው የሥርዓተ ትምህርትን የትምህርት ፍልስፍና ለውጥ፣ ከሚዘጋጁት የማስተማሪያ መሣሪያዎች ጋር ለመምህራኑ ሥልጠና ትኩረት መስጠቱ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ውጤታማነት ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ የመማር-ማስተማር ሂደት የትምህርቱን ዓላማ ለማስገኘት ካለው ቁልፍ ሚና አኳያ በየጊዜው መገምገምና በየወቅቱ ጥናት ሊደረግበት ይገባል፡፡

በመማር-ማስተማሩ ሂደት የሚቀርቡት ክንውኖች እና ይዘቶች በአብዛኛው ከመምሪያ መጽሐፉ ነው። በመጽሐፉና በመርሐ-ትምህርቱ የቀረቡት የንግግር ክሂል ትምህርት ይዘቶች በተወሰነ ደረጃ ልዩነት ቢታይባቸውም ለክሂሉ የተሰጠውን ትኩረት ከፍተኛ መሆኑና መጻሕፍቶቹ በመፈተሽ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በክፍል ውስጥ የንግግር የመማር-ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ትርጉም ባለው መንገድ ችሎታቸው እንዲዳብር ዓይነት ምንገዶችን መጠቀም እንዳለበት እያንዳንዱ መምህር ራሱን በመጠየቅና በመዘጋጀት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል። መምህሩ ጥሩ የመማር-ማስተማር ሁኔታን በክፍል ውስጥ ካልፈጠረና ትምህርቱንም በተገቢው መንገድ እንዲካሄድ ትኩረት የሚሰጥ፣ ከተማሪዎች የእለተ እለት ሕይወታቸው ጋር የተገናኘ ርእሰጉዳዮችን ካላቀረበ የመስላቸትና ትምህርቱን የመጥላት አዝማሚያ በተማሪዎች ላይ መታየቱ አይቀርም። የመረጃው ውጤት እንደሚያሳየው ከአንድ ምልከታ በስተቀር በክፍል ውስጥ የቀረቡት ሌሎች ይዘቶችና ክንውኖች መምህሩ ፈጠራ ላይ ያልተመሠረቱና መማሪያ መጽሐፍን ተመርኩዘው የቀረቡ መሆናቸው የተማሪዎቹን ተሳትፎ በእጅጉ ቀንሰውታል።

የማስተማሪያ መረጃ መማሪያዎች የሚያቀርቧቸው ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ክሂሉችን በክፍል ውስጥ ለማስተማር በተማሪዎች የመናገር ችሎታ መዳበር ላይ አዎንታዊ ሚና መጫወት ይኖርባቸዋል።

መምህራን ከአዲስ የማስተማሪያ ዘድ ጋር እንዲተዋወቁ ምቹ ሁኔታ ባለመፍጠራቸው እና ረዘም ያለ ጊዜ አገልግሎት ያለምንም ስልጠና መቀመጣቸው በክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት ሂደት ውስጥ በአሁኑ ዘመን ተቀባይነት እያገኘ የመጣውን ተግባቦታዊ የማስተማር ዘድ ተግባራዊ ለማድረግ አልሞከሩም። በዚህም ምክንያት በክፍል ውስጥ ያለው መስተጋብር መምህር-መራሽ የሆነ የማስተማር ዘዴ በጎላ ሁኔታ ተንጸባርቆበታል። በንግግር ክሂል ትምህርት ወቅት በጥንድ ወይም በቡድን ሐሳብ ለሐሳብ የመለዋወጥ፣ የመወያየትና እርስ በርስ የመተራረም ተግባራት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሲፈጽሙ አልታዩም።

የጥናቱ ውጤት በአጠቃላይ እንደሚያመለክተው፣ ለክፍሉ ደረጃ የቀረቡት መረጃ መግሪያዎች በውስጣቸው ያካተቷቸው ይዘቶችና መልመጃዎች ተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ችሎታቸውን የማያዳብሩ እንዲሁም በተማሪዎች መካከል የእርስ በርስ መስተጋብር ለመፍጠር የማያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል። የቀረቡት የንግግር ተግባራት የሚከናወንበት ሥነ-ዘዴ የክፍል ውስጥ ትግበራ ቀስ በቀስ ነጻ ሆነው እንዲናገሩ የማያበረታቱ ሆነው ተገኝቷል። ይህም የሚያመለክተን የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ ለማዳበር መምህራን በቂ ጊዜ ወስደው ያላዘጋጁለት፣ የተወሰነና ግልጽ ግላጭ ይዘው ሥራውን ያላከናወኑት መሆኑን ነው።

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

በዚህ ጥናት ውጤት የተመለከቱት በስምንተኛ ክፍል የንግግር ክሂል ትምህርትን የመማር-ማስተማር ሂደት ችግሮች የአጠቃላዩ የትምህርት ሂደት ችግሮች በመሆናቸው ተማሪዎች ንግግርን በተሻለ ሁኔታ የሚማሩበትና ሐሳባቸውን በንግግር የመግለጽ አቅጣጫ ለማመልከት ከጥናቱ ውጤቶች በመነሳት የሚከተሉት የመፍትሔ ሐሳቦች ቀርበዋል፤

- በሥርዓተ-ትምህርቱና በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ይዘቶችም ሆኑ መልመጃዎች የክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርትን በተገቢው ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችሉ፣ የእርስ በርስ ተግባቦትን የሚያበረታቱ፣ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሱ ሆነው ቢቀረጹና ቢዘጋጁ፤
- መምህራኑ ራሳቸውን ከአዳዲስ ትውራቶች፣ ሥነ-ዘዴውችና ገጠመኞች ጋር በማስተዋወቅ ለተሻለ አሠራር ራሳቸውን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።
- የንግግር ክሂል ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲከናወን አቀራረቡ መምህር-መራሽ ሳይሆን ተማሪ-መራሽ መሆን እንደሚገባው መምህራኑ ሊያውቁት ይገባል። ምክንያቱም ተማሪዎቹ በመማር-ማስተማር ሂደት ንቁ ተሳታፊ በመሆን የሚፈለገውን የቋንቋ ችሎታ ለማዳበር ስለሚያስችላቸው ነው።

ስለዚህ ደግሞ መምህራኑ ተማሪዎቻቸውን በማበረታታቱና በማነሳሳት ሂደት ድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል። ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት አብዛኛዎቹ መምህራን ይህን ተግባር ሲያከናውኑ እንዳልታዩ በጥናቱ ማጠቃለያ ላይ ተገልጿል። ስለዚህ የመማር- ማስተማርን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ በቅድመ-መምህርነት ሥልጠና ስለንግግር ማስተማሪያ ዘዴና ስለንግግር ክሂል ሰፊ ዕውቀት ለማስጨበጥ የሚያስችል ሥልጠና ሚሰጥበትን መንገድ መምህራንን የሚያሠለጥኑ ተቋማት ትኩረት ሊሰጡ ይገባል።

- በድኅረ-መምህርነት ሥልጠና መምህራንን እየተለወጠና እየተሻሻለ ከሚሄደው የቋንቋ ትምህርትና ከቋንቋ ማስተማር መስክ፣ በመስኩ ከሚፈጠሩት አዳዲስ ግኝቶችና ስነ-ዘዴዎች ጋር ለማስተዋወቅ ተከታታይ የአጭር ጊዜ ሥልጠና የሚሰጥበት መርሐ-ግብር በሥርዓተ-ትምህርት መምሪያ፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት መነደፍና ተግባራዊ መሆን አለበት።

## ሙዳዩ ቃላት

ከመገኛ ቋንቋቸው ተተርጉመው የአማርኛ ፍቺ የተሰጣቸው ቃላት በጥናቱ ውስጥ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ስለሚውሉ እና ለአንባቢ የሚያስተላልፉት ሐሳብ ግልጽ ይሆን ዘንድ ሥያሜ ቃላቱን ከእንግሊዝኛ አቻቸው ጋር በፊደል ተራ እንደሚከተለው እንዲቀርቡ ተደርገዋል፤

| | |
|---|---|
| ልምምድ | Practice |
| ሐሳብ ማመንጨት | Brainstorming |
| መላ ፈጠራ | Improvisation |
| መስተጋብር | Interaction |
| ሚና ነጠቃ | Role play |
| ንበት | Pronunciation |
| ትክክለኛነት | Accuracy |
| አፍልቆት | Production |
| አፈተክነት | Fluency |
| የማስመሰል ሥራ | Imitation |
| የምልከታ ክንውን | Observation activities |

## ዋቢ ጽሑፎች


መንግስቱ ታደሰ። 1997። "በአዲስ አበባ መስተዳድር የ9ኛ ክፍል የንግግር ክሂል የማስተማሪያ ዘዴ አተገባበር ግምገማ።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ያልታተመ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

ማረው ዓለሙ። 1996። *በጎልማሶች ድርሠት ማስተማሪያ*፡ አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

__________። 1998። *የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ*። አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት።

ሰፋ መኮ።1995። "የጉመር ጉራግኛ አፈፌት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ሲናገሩ የሚጠቀሙባቸው ተግባቦታዊ ብልሀቶች ትንተና።" ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ያልታተመ ጥናት። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ።

በድሉ ዋቅጅራ። 1996። *በስነፅሁፍ ቋንቋን ማስተማር*፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

በቦን ማሞ።1985። "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎችን የሚያዳብሩ ናቸው?" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ያልታተመ ጥናት።

ተስፋዬ ሸዋዬ። 1991። "ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)።

አለም እሸቱ። 1995። "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መማሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀት እና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር።" አዲስ አበባ፤ ለ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢ። ለሰሚናር ጥናት የቀረበ።

እቴነሽ ተገኝ።1986። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ግብር ትምህርት ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች" ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት።

ፈቀደ አዘዘ። 1982። "አንዳንድ ነጥቦች ስለ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ሌሎች አማር ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ፣ ስለ ሥርዓተ ትምህርቶች ስለ መማሪያ መጽሐፍትና ስለ ሥነ ጽሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት።" ለሥርዓተ ትምህርት ሲምፖዚየም የቀረበ ጽሑፍ።

Anderson, A. and T. Lynch. 1988. *Listening*. Oxford: Oxford University Press.

Brehanu, Matthewos. 1994. English Poetry in Ethiopia: The Prevalence of Stylistics in an EFL Context, Ph.D. Thesis. Addis Ababa University.

Brown, Gillian and Gorge Yule. 1983. *Teaching The Spoken Language*. New York: Cambridge University Press.

Byrne, Donn. 1976. *Teaching Oral English*. London; Longman. Group UK Limited.

________.1987. *Teaching for Classroom Interaction*. London; Longman. Group UK Limited.

Celce, Murcia, M. (ed).1991. *Teaching English as a Second or Foreign Language*. 2nd ed. Boston: Heinlein and Heinlein Publisher.

Harmer, J. 1995. *The Principle of English Language Teaching*. London; Longman.

Lazar,G. 1993. Literature and Language Teaching. A Guide for Teachers and Trainers.

Malay,A. and Alan Duff.1978. Drama Techniques in Language Learning: Cambridge: Cambridge University Press.

Mc Donough, Jo. And Christopher Shaw. 1993. *Materials and Method in ELT*. Oxford: Blackwell Publisher.

Morley, J, .1991. "Listening Comprehension in Sound /Foreign Language Instruction" in M. Celce-Murcia 9 ed). *Teaching English as a Second or Foreign Language.* (2nd ed) Boston: Heinsa publishers.

Nunan, D. 1981. *Tasks for the Communicative Classroom*. Sydney: Cambridge University Press.

________.1989. *Designing Tasks for the Communicative Classroom*. Cambridge: Cambridge University Press.

________.1991. *Language Teaching Methodology*. London: Prentice- Hall.

Richards, J. C. and S.T, Rogers. 1986. *Approaches and Methods in Language Teaching*. Cambridge: Cambridge University Press.

Ur, P. 1996. *A Course in Language Teaching*; Practices and Theory. Cambridge: Cambridge University Press.

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

## የክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ክንውን ምልከታ መከታተያ ተተኳሪ ሠንጠረዥ

የትምህርት ቤቱ ስም ____________
ምልከታ የተካሄደበት ክፍልና ሴክሽን____________
ቀን____________
ፈረቃ ____________
ክ/ጊዜ ____________
ሠዓት ____________

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴ ትግበራ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪውን መማሪያ መጽሐፍ መሠረት የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 2 | በትምህርቱ አቀራረብ የራስ ፈጠራና የማስተማሪያ መማሪያዎች የመጠቀሙ ሁኔታ | | | | | |
| 3 | የትምህርቱ ይዘት የተማሪዎቹ እድሜና የትምህርት ደረጃ የማገናዘብ ሁኔታ | | | | | |
| 4 | የተወሰነና ግልጽ ዓላማ ይዞ የመግባቱ ሁኔታ | | | | | |
| 5 | የትምህርቱ ይዘት አመራረጥ ሁኔታ | | | | | |
| | ሀ. በመምህሩ የተመረጡ ይዘቶች | | | | | |
| | ለ. በተማሪዎች የተመረጡ ይዘቶች | | | | | |
| 6 | ግልጽ የሆነ መምሪያ የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 7 | የንግግር ትምህርቱን በበቂ ሁኔታ ይለማመዱ ዘንድ ተማሪዎች የማንቃታት ሁኔታ | | | | | |
| 8 | ትርጉም ያላቸው የንግግር ተግባራት እንዲያከናውኑ አድርጎ ነበር? | | | | | |
| 9 | በልምምዱ ወቅት የተማሪዎች ተሳትፎ | | | | | |
| 10 | ተማሪዎች ወደ ልምምድ ተግባር እንዲገቡ የማድረጉ ብቃት | | | | | |
| 11 | ተግባሩን ለመለማመድ በቂ ጊዜ የመስጠቱ ሁኔታ | | | | | |
| 12 | በቋንቋው ተጠቅመው ተግባቦታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ፍንጮችን የመስጠት ሁኔታ | | | | | |
| 13 | ተማሪዎች እንዲለማመዱ የማበረታታቱ ሁኔታ | | | | | |

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴ ትግበራ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ልምምዱን ለማድረግ የተጠቀመበት የመማር ማስተማር ተራክቦ<br>ሀ. በግል | | | | | |
| | ለ. በጥንድ | | | | | |
| 15 | በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች የመቆጣጠር ሁኔታ | | | | | |
| 16 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 17 | ልምምዱ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲያሳትፍ ጥረት የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 18 | ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 19 | ተማሪዎች በቂ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ልምምድ እንዲያደርጉ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል?<br>• ፍንጭ በመስጠት | | | | | |
| | • በመደጋገም/ ድግግሞሽ | | | | | |
| | • በማስመሰል | | | | | |
| 20 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎችን ለማረም ጣልቃ ይገባ ነበር? | | | | | |
| 21 | ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ የተረዱት መሆኑን የመገንዘብ ሁኔታ | | | | | |
| 22 | የልምምዱን ተግባር ተማሪዎች የሚመልሱት የሚያደርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነበር? | | | | | |
| 23 | ተማሪዎች በጥያቄና መልስ ልምምዳቸው እንዲያዳብሩ ያደርግ ነበር? | | | | | |
| 24 | ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታታ ነበር። | | | | | |
| 25 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው። | | | | | |

| ተ.ቁ | የማስተማር ዘዴ ትግበራ | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መጠነኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | ልምምዱን ለማድረግ የተጠቀመበት የመማር ማስተማር ተራክቦ<br>ሀ. በግል | | | | | |
| | ለ. በጥንድ | | | | | |
| 15 | በልምምድ ጊዜ ተማሪዎች የመቆጣጠር ሁኔታ | | | | | |
| 16 | ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲለማመዱ የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 17 | ልምምዱ ሁሉንም ተማሪዎች እንዲያሳትፍ ጥረት የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 18 | ልምምዱ በተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዳይያዝ የማድረጉ ሁኔታ | | | | | |
| 19 | ተማሪዎች በቂ ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ልምምድ እንዲያደርጉ የተለያዩ ዘዴዎችን ተጠቅሟል?<br>• ፍንጭ በመስጠት | | | | | |
| | • በመደጋገም/ ድግግሞሽ | | | | | |
| | • በማስመሰል | | | | | |
| 20 | በልምምድ ወቅት ተማሪዎችን ለማረም ጣልቃ ይገባ ነበር? | | | | | |
| 21 | ተማሪዎች የሚሰሩትን ስራ የተረዱት መሆኑን የመገንዘብ ሁኔታ | | | | | |
| 22 | የልምምዱን ተግባር ተማሪዎች የሚመልሱት የሚያደርገው የተዘጋጁ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ነበር? | | | | | |
| 23 | ተማሪዎች በጥያቄና መልስ ልምምዳቸው እንዲያዳብሩ ያደርግ ነበር? | | | | | |
| 24 | ተማሪዎች እርስ በርስ በመወያየት ልምምድ እንዲያደርጉ ያበረታታ ነበር፡፡ | | | | | |
| 25 | የንግግር ተግባራቱ ተማሪዎችን በቀላሉና በነጻነት ሊያግባባ የሚችል ዐውድ በመፍጠር የተከናወኑ ናቸው፡፡ | | | | | |

አባሪ ሁለት

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
## በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

ውድ የ________________ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የዚህ መጠይቅ ዓላማ በአፋር ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የማስተማሪያ መጣሪያዎች/የመማሪያ መጸሀፍት፣ የመምህሩ መምሪያና መርሀ ትምህርቱ በቀረቡት የንግግር ትምህርት የዘቶችና መልመጃዎች የማስተማሪያ ዘዴ ትግበራ ላይ ጥናት ለማከሄድ የሚያግዙ ተጨማሪ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው፡፡ በጥናቱ የሚደረስበት ውጤት በስምንተኛ ክፍል ንግግርን ለመማር-ማስተማር ዘዴ ውጤታማነት እና ለተማሪዎች የንግግር ክሂል መዳበር ከፍኛ ጠቀሚታ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ከመጠይቁ የሚገኘው ምላሽም ለተጀመረው ጥናት መሳከት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታሰባል፡፡ጥናቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድም የሙያው ባለቤቶችን ድጋፍ የሚጠይቅ ስለሆነ እርስዎ ይህን መጠይቅ በሞሙላት የበኩሉን ሙያዊ ድጋፍ ያደርጉልኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡
በመጨረሻም እጅግ ውድ የሆነው ጊዜዎን ሰውተው መጠይቁን ለሞሙላት ለሚያደርጉት ትብብር ምስጋናዬ ይድረስዎ፡፡

ማሳሰቢያ፡- በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም፡፡

ክፍል አንድ

አጠቃላይ መረጃ

ከዚህ በታች ለቀረቡት መረጃዎች ትክክለኛውን መረጃ በተተወው ባዶ ቦታዎች ይሞሉ፡፡

1. ጾታ________________
2. ዕድሜ________________
3. የትምህርት ደረጃ________________
4. የአፍ መፍቻ ቋንቋ________________
5. የሠለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ

ዐቢይ__________

ንዑስ__________

6. የአገልግሎት ዘመን ______________________

7. የንግግር ክሂል ትምህርት የሚመለከት በቅድመ ስራና በስራ ላይ እያሉ ስልጠና ላይ ተሳትፈው ያውቃሉ?አዎ አይደለም

8. መልስዎ «አዎ» ከሆነ የስልጠናው አይነትና ሁኔታ ዘርዘር በማድረግ ቢገልጹት:_______________________________________________
_______________________________________________
_______________________________________________

ክፍል ሁለት

የግንዛቤ ጥያቄዎች

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በትክክል ያመኑበትን/ባቸውን መልስዎ በመክበብ ያሳዩ።
የተለየ ሀሳብ ካለዎትም በተሠጠው ክፍት ቦታ ላይ በመጻፍ መልስ/መልሺ።

1. ክሂሎች በክፍል ውስጥ የማስተማር ዘዴን በዘመናዊው መንገድ በተማርክበት/ሽበት ተቋም ተምርሃል/ሻል?

   ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ ሐ/ በመከከለኛ ደረጃ

   ለ/ በአብዛኛው ወስጃለሁ መ/ በአብዛኛው አልወሰድኩም ሠ/____________

2. መልስዎ ሀ ወይም ለ ከሆነ የንግግር ክሂልን ለማስተማር ምን ያህል አግዞውታል?

   ሀ/ በከፍተኛ ደረጃ ሐ/ በመጠኑ

   ለ/ በአብዛኛው መ/ ፍጹም አላገዘኝም

3. የቡድን ወይም የጥንድ ስራን ያበረታታሉ?

   ሀ/ ሁል ጊዜ ሐ/ በአብዛኛው

   ለ/ በመጠኑ መ/ በፍጹም አላበረታታም ሠ/____________

## ክፍል ሦስት

### የክፍል ውስጥ ትግበራን በተመለከተ የቀረቡ ዝርዝር መከታተያ ቅጾች

ከዚህ ቀጥሎ በስጠረኝ ለቀረቡት ዝርዝር መጠይቆች መልስ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡ አራት አማራጮች ተሰጥተዋል። እነዚህ በቁጥር የተወከሉ ሲሆን፦

4 = ሁልጊዜ

3 = አብዛኛውን ጊዜ

2 = አንዳንድ ጊዜ

1 = ጨርሶ የሚሉ የውሳኔ ሀሳቦችን የያዙ ናቸው። እርስዎም በጥያቄዎቹ ትይዩ የሚሰጡትን መልስ የ "X" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 4 | ለክፍል ውስጥ የንግግር ክሂል ትምህርት የሚሆኑ ርዕስ ጉዳዮች ተማሪዎች ከራሳቸው ገጠመኝ ዙሪያ እንዲለማመዱ አደርጋለሁ። | | | | |
| 5 | ከንግግር ትምህርት በፊት ስለንግግር አቀራረብ ተማሪዎቹ እንዲያውቁ አደርጋለሁ። | | | | |
| 6 | ወደዋናው የንግግር ተግባር ከመግባቴ በፊት የማነቃቃት ሥራ (motivation) እከናውናለሁ። | | | | |
| 7 | የንግግር ትምህርት ርዕስ በጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ በቀጥታ ወደዋናው ተግባር እገባለሁ። | | | | |
| 8 | የንግግር ተግባሩን ከመለማመዳቸው በፊት አጋዥ መርጃ መግሪያዎችን በመጠቀም በግልጽና በማይረሳ መልኩ ሞዴሎችን (ምሳሌዎችን) አጠር ባለ መልኩ አቀርባለሁ። | | | | |
| 9 | ተማሪዎች በቀረበላቸው ሞዴል የንግግር ተግባር መሰረት የማስመሰል እና የመደጋገም ስራዎችን እንዲያከናውኑ አደርጋለሁ። | | | | |
| 10 | የቅድመ ንግግር ትምህርት አስተማራለሁ። | | | | |
| 11 | የንግግር ተግባሩ ከቀረበና በዚህ ላይ ከተለማመዱ በኃላ ሐሳባቸውን በነጻ እንዲገልጹ አደርጋለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | በራሳቸው የሰዋሰው ዕውቀት ተጠቅመው ሐሳባቸውን የሚገልጹበትን መንገድ እመቻቻለሁ። | | | | |
| 13 | በተማሪዎች ቁጥር መብዛት ምክንያት በተናጠል እንዲናገሩ አደርጋለሁ። | | | | |
| 14 | በተማሪዎች ቁጥር መብዛት ምክንያት በቡድን /በሕብረት/ ተወያይተው ሐሳባቸውን እንዲገልጹ አበረታታለሁ። | | | | |
| 15 | ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ሰዎን ጠይቀው ወይም ምልከታ አድርገው እና የተለያዩ ጹሑፎችን አንብበው በክፍል ውስጥ እንዲናገሩ አደርጋለሁ። | | | | |
| 16 | አብዛኛውን ጊዜ ለመናገር የማይደፍሩና ሐሳባቸውን ለመግለጽ የሚያዳግታቸውን ተማሪዎች እንዲናገሩ የተለያዩ መንገዶችን እመቻቻለሁ። | | | | |
| 17 | የንግግር ትምህርትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር በማቀናጀት አስተማራለሁ። | | | | |
| 18 | የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ለማዳበር የሚታዩ ነገሮችን ሥዕል፣ ቅርጻቅርጽ፣ ካርታ፣ ሠንጠረዥ፣ ወዘተ. በመስጠት እንዲናገሩ አበረታታለሁ። | | | | |
| 19 | በንግግር ትምህርት ወቅት በተማሪዎች ንግግር ጣልቃ በመግባት ስሕተታቸውን እንዲያርሙ አደርጋለሁ። | | | | |
| 20 | ተማሪዎችን በቡድን በመከፋፈል ሐሳብ ለሐሳብ እንዲለዋወጡ አደርጋለሁ። | | | | |
| 21 | ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕሠ ጉዳይ ላይ ንግግር ካደረጉ በኋላ በነጻነት አስተያየት እንዲሰጡ አበረታታለሁ። | | | | |
| 22 | ስህተትን እንደ አንድ የመማሪያ መንገድ አድርገው እንዲቆጥሩ እጋብዛለሁ። | | | | |
| 23 | በራሳቸው ጥሩና መጥፎ ገጠመኝ ዙሪያ ላይ ንግግር እንዲያደርጉ እጋብዛለሁ። | | | | |
| 24 | ተማሪዎች የንግግርን ትምህርት ሲማሩ በአፈተክነት (Fluency) ላይ እንዲያተኩሩ አደርጋለሁ። | | | | |

| ተ.ቁ | ዝርዝር መጠይቆች | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ተማሪዎች ስክተታቸውን እርስ በርሳቸው እንዲተራረሙ አበረታታለሁ። | | | | |
| 26 | የንግግር ትምህርቱ ከማለቁ በፊት ተማሪዎች ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ አበረታታለሁ። | | | | |
| 27 | በቀረበው የንግግር ትምህርት /በተማሪዎች የንግግር ተግባር ላይ/ ማሻሻያ ሐሳብ እሰጣለሁ። | | | | |
| 28 | የንግግር ትምህርት ግብአቶችን የማቀርበው ለደረጃው የተዘጋጀውን መፅሐፍ በመጠቀም ነው | | | | |
| 29 | ለንግግር ትምህርት የሚሆኑ ግብአቶችን በግል ተዘጋጅቼ በመምጣት አስተምራለሁ። | | | | |
| 30 | ለንግግር ትምህርት የሚሆኑ ርእስ ጉዳዮችን ተማሪዎች እንዲመርጡ አደርጋለሁ። | | | | |

አባሪ ሦስት

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የድኅረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

## በስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች የዚህ መጠይቅ ዋና ዓላማ በክልሉ በተዘጋጁት የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ለንግግር ትምህርት የቀረቡትን ይዘቶችንና ክንውኖች፣የማስተማሪያ ዘዴ የክፍል ውስጥ ትግበራ ችግሮች ከሉ የመፍትሔ ሀሳብ ለመፈለግ እና ለተጀመረው ጥናት ተጨማሪ መረጃ ማሰባሰብ ነው።

ከመጠይቁ የሚገኘው ውጤት ለተጀመረው ጥናት መሳካት ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው ይገመታል። ለጥናቱ ግብ መምታት ትክክል መረጃ ማሰባሰብ አስፈላጊ በመሆኑ የቀረቡትን ጥያቄዎ በጥሞና አንብበው ትክክል ነው/ናቸው ብለው የሚገምቱትን/አቸውን መልስ/ኦች እንዲሰጡኝ ስጠይቅዎት መጠይቁን ሞልተው በመመለስ ለሚያደርጉልኝ ትብብር ልባዊ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው።

<u>ማሳሰቢያ፣</u>

1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም።
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር በመወያየት መሙላት በሚሰበሰበው መረጃ ላይ ተጽእኖ ስለሚያሳድር ክልክል ነው።

<u>መመሪያ አንድ፣</u> ቀጥሎ ለቀረቡት ክፍል ቦታዎች ትክክለኛውን መረጃ በመሙላት እንድትተባበረኝ/ሪኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ሀ. ፆታህ/ሽ________________

ለ. እድሜህ/ሽ________________

ሐ. የአፍ መፍቻ ቋንቋህ/ሽ______________

መ. ሁለተኛ ቋንቋ የምታውቁ ከሆነ ስሙ ይጠቀስ

መመሪያ ሁለት፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሚያመላክቱትን ሆሄያት በመክበብ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፤

1. በአማርኛ ቋንቋ በክፍል ውስጥ የንግግር ትምህርት ወቅት የመከታተል ፍላጎትህ/ሽ

ሀ. በጣም ከፍተኛ ነው::　　ሐ. መወሰን አልችልም::

ለ. ከፍተኛ ነው::　　መ. ፍላጎት የለኝም::

2. በተራ ቁጥር "1" ለቀረበው ጥያቄ መልስህ/ሽ ፍላጎት የለኝም የሚል ከሆነ ምክንያቱን ምንድነው?

ሀ. መምህሩ በአግባቡ ስለማያስተምሩኝ ነው::

ለ. ንግግርን በመማሬ የማገኘው ጥቅም የለም ብየ ስለማስብ ነው::

ሐ. ስለምፈራና ስለማፍር ነው::

መ. ተናጋሪ (Orater) የመሆን ፍላጎት ስለሌለኝ ነው::

3. የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የንግግር ክሂልን ለማዳበር፣

ሀ. በጣም ይጠቅማል::　　ሐ. ምንም አይጠቅምም::

ለ. በመጠኑ ይጠቅማል::　　መ. ሌላ ካለ____________________

4. መምህሩ የንግግር ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ተማሪዎችን ያነቃቃል?

ሀ. ሁልጊዜ ያነቃቃል::　　ሐ. አብዛኛውን ጊዜ ያነቃቃል::

ለ. አንዳንድ ጊዜ ያነቃቃል::　　መ. በፍጹም አያነቃቃም::

5. አንተ/ቺ በክፍል ውስጥ ምን ያህል ጊዜ በንግግር ወቅት ትሳተፋለህ/ሽ?

ሀ. በተደጋጋሚ　　ሐ. መምህሩ ሲጠይቁኝ

ለ. አንዳንድ ጊዜ　　መ. አልሳተፍም

6. መምህሩ የንግግሩን ትምህርት በሚያከናውንበት ጊዜ ለሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እኩል እድል ይሰጣሉ?

ሀ. ሁልጊዜ ይሰጣሉ::　　ሐ. አንዳንድ ጊዜ ይሰጣሉ::

ለ. አብዛኛው ጊዜ ይሰጣሉ::　　መ. ምንም አይሰጡም::

7. ዋናውን የንግግር ተግባር ተማሪዎች ከማከናወናቸው በፊት ሞዴል (ምሳሌ የሚሆኑ) ተግባሮችን ያቀርባሉ?

ሀ.ሁልጊዜ ያቀርባሉ ::　　ሐ. አልፎ አልፎ ያቀርባሉ::

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ያቀርባሉ::　　መ. በፍጹም አያቀርቡም::

8. ለመናገር የማይደፍሩ ተማሪዎችን እንዲናገሩ የማበረታታቱ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው::　　ሐ. ዝቅተኛ ነው ::

ለ. መካከለኛ ነው::　　መ. በጣም ዝቅተኛ ነው::

9. በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የንግግር ተግባር መምህሩ ግልፅ እና የማይረሳ መመሪያ ይሰጣል?

ሀ. በተገቢው መንገድ ይሰጣል።      ሐ. በፍፁም አይሰጥም።

ለ. በመጠኑ ይሰጣል።      መ. ሌላ ካለ-------------------------

10. የንግግር የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የክፍሉ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ስርዓት ያለው ነው።      ሐ. በጣም ቀልድ የበዛበትና ረብሻ ነው።

ለ. በመጠኑ ስርዓት ነው።      መ. ሌላ ካለ -------------------------

11. መምህሩ በጥንድ ወይም በቡድን እንድትወያዩ እና የንግግር ችሎታችሁን እንድታዳብሩ የሚያደርገው ጥረት እንዴት ነው?

ሀ. ከፍተኛ ነው።      ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው።      መ. ምንም ጥርት አያደርግም።

12. የንግግር ተግባር ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መለማመድ

ሀ. ጠቀሜታ አለው።      ሐ. አይጠቅምም።

ለ. በመጠኑ ይጠቅማል።      መ. ሌላ ካለ -------------------------

13. መምህሩ በክፍል ውስጥ የንግግሩን ተግባር በተገቢው መንገድ እዲለማመድ የማድረግ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው።      ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው።      መ. አያበረታታም።

14. የተለማመዳችሁትን የንግግር ተግባር በነፃነት ሐሳባችሁን እንድትገልጹ ያደርጋል?

ሀ. ሁልጊዜ ያደርጋል።      ሐ. አልፎ አልፎ ደርጋል።

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋል።      መ. አብዛኛውን ጊዜ አያደርግም።

15. መምህሩ የተለያዩ ሥዕሎች፣ ፎቶ ግራፎች እና ቅርጻ-ቅርጾችን በመማሪያ ክፍል በማምጣት ተማሪዎችን እንዲናገሩ ያደርጋል?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው።      ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው።      መ. ምንም ጥረት አያደርግም።

16. ንግግርን ለማስተማር የሥነጹሑፍ ስራዎችን/ልቦለድ፣ ስነቃል፣ ግጥም ወዘተ. የመጠቀሙ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው።      ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው።      መ. አይጠቅምም።

9. በክፍል ውስጥ ለሚደረገው የንግግር ተግባር መምህሩ ግልፅ እና የማይረሳ መመሪያ ይሰጣል?

ሀ. በተገቢው መንገድ ይሰጣል። ሐ. በፍፁም አይሰጥም።

ለ. በመጠኑ ይሰጣል። መ. ሌላ ካለ------------------------

10. የንግግር የክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት የክፍሉ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ስርዓት ያለው ነው። ሐ. በጣም ቀልድ የበዛበትና ረብሻ ነው።

ለ. በመጠኑ ስርዓት ነው። መ. ሌላ ካለ ------------------------

11. መምህሩ በጥንድ ወይም በቡድን እንድትወያዩ እና የንግግር ችሎታችሁን እንድታዳብሩ የሚያደርገው ጥረት እንዴት ነው?

ሀ. ከፍተኛ ነው። ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው። መ. ምንም ጥርት አያደርግም።

12. የንግግር ተግባር ከሌሎች ተማሪዎች ጋር መለማመድ

ሀ. ጠቀሜታ አለው። ሐ. አይጠቅምም።

ለ. በመጠኑ ይጠቅማል። መ. ሌላ ካለ ------------------------

13. መምህሩ በክፍል ውስጥ የንግግሩን ተግባር በተገቢው መንገድ እዲለማመድ የማድረግ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው። ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው። መ. አያበረታታም።

14. የተለማመዳችሁትን የንግግር ተግባር በነፃነት ሐሳባችሁን እንድትገልጹ ያደርጋል?

ሀ. ሁልጊዜ ያደርጋል። ሐ. አልፎ አልፎ ደርጋል።

ለ. አብዛኛውን ጊዜ ያደርጋል። መ. አብዛኛውን ጊዜ አያደርግም።

15. መምህሩ የተለያዩ ሥዕሎች፣ ፎቶ ግራፎች እና ቅርጻ-ቅርጾችን በመማሪያ ክፍል በማምጣት ተማሪዎችን እንዲናገሩ ያደርጋል?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው። ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው። መ. ምንም ጥረት አያደርግም።

16. ንግግርን ለማስተማር የሥነጹሑፍ ስራዎችን/ልቦለድ፣ ስነቃል፣ ግጥም ወዘተ. የመጠቀሙ ሁኔታ እንዴት ነው?

ሀ. በጣም ጥሩ ነው። ሐ. ዝቅተኛ ነው።

ለ. መካከለኛ ነው። መ. አይጠቅምም።